# የእንስሳት ዕድር

## (አኒማል ፋርም)

ድርሰት ፤ ከጆርጅ ኦርዌል ።

ትርጉም ፤ በለማ ፈይሣ ጭቅሰየ

…EY / BROOKS FOUNDATION, INC.
… GREENVILLE AVE. ST. 810
…, TEXAS 75201, USA

…SLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
… N. GREENVILLE AVE. ST. 810
…, TEXAS 75201, USA

1983 ዓ.ም.

## መታሰቢያነቱ

ስሙ ሆኖ «ዕድገት በኅብረት...»
ከትምርት ማዕድ በመነሣት ፤
ፈልጋችሁ ፤ ወይ ሳትሹት ፤
ከናት ጓዳ ፤ ካባት ጉያ... ራቅ ብላችሁ በመለየት ፤
    ባምባ ፤ መስኩ ፤ በዱር ገደል ፤
    ቆላ ደጋ ፤ አቀብ ቁልቁል ፤
በመማሰን ከራርማችሁ ፤
እንደ ምንም ቤት ደርሳችሁ ፤
በማግሥቱ ለጠፉችሁ ፤
የሰው ወጉን ተነፍጋችሁ ፤
    ...ያለ ማዕረግ ፤ ያለ ቀብር ፤
    ያለ ልቅሦ ፤ በ«ቀይ ሽብር»
    በጐዳና ፤ ባደባባይ ፤ ያለ ድንኳን ፤ ያለ ወንበር ።
ተከርችሞ እግር ተወርች ፤
ለቀራችሁ ለእኔ ልጆች ፤
    ለመሠረት ፤ ለውባየሁ ፤ ከሆነና ከተስማማ ፤
    ተቀበሉኝ ካባት «ለማ»
    ለስማችሁ ቢሆን መጥሪያ ፤
    ማስታወሻ ፤ መታሰቢያ ።
ባጭር ቀርተው ለተቀጩት ፤
ለውባየሁ ፤ ለመሠረት ፤
ካባት ለልጅ ያው በረከት!


ዐማርኛው ትርጉም መብቶቹ ሁሉ
ለትርጓሚው የተጠበቁ ናቸው ።

የመጀመሪያ እትም ፤ መስከረም 1984 ዓ. ም.

የሽፋኑ ሥዕል ቦጋለ በላቸው

አዲስ አበባ ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ

# የእንስሳት ዕድር

## (ከአኒማል ፋርም)

ሚስተር ጆንስ ፣ የማኖር ዕርሻ ባለቤት ፣ ማታ የዶሮ ዎቹን ቤት መዝጊያ ቀረቀረ ። ሆኖም አለቅጥ ሰክሮ ስለነበረ ፣ መሿለኪያ ቀዳዳዎቹን የመድፈኑን ሥራ ረሳው ። በአንድ እጁ አንጠልጥሎት የነበረው ፋኖስ መብራት ከጐን ወደ ጐን እየተወ ለበለበ ፣ በግቢው መንገድ በመንገዳገድ ዐልፎ ከመኖሪያ ቤቱ ጓሮ ደረሰ ። የገበሬ መጫሚያውን ደጃፉ ላይ አውልቆ ገባ ። በጓዳ አንድ ብርጭቆ ቢራውን ተጐነጨና ሚስስ ጆንስ እያንኰራፉች ትገኝ ወደ ነበረችበት መኝታ ቤቱ አመራ ።

ወዲያው የመኝታ ቤቱ መብራት እንደ ጠፋ በዕርሻ ጣቢያው ቤቶች ሁሉ ውስጥ የትርምስና ግርግር ድምፅ ተፈጠረ ። ቀን አንድ ወሬ ተዛምቶ ነበር ፤ ሜጀር የተባለው ፣ በውድድር ተሸላሚው ፣ ነጩ ኮርማ ዐሣማ ፣ ባለፈው ሌሊት ያልተለመደ ሕልም አልሞ ስለነበረ ፣ ለሌሎች እንስሳት ሊያወጋቸው እንደ ሚፈልግ ተወርቶ ነበር ። ሚስተር ጆንስ ባካባቢው አለመኖሩ እንደተረጋገጠ ፣ በትልቁ የእህል መጋዘን ውስጥ ሁሉም እንዲሰ በሰቡ ተስማምተው ነበር ። አዛውንቱ ሜጀር (እየተባለ ነበር የሚጠራው ፤ ምንም እንኳ ለውድድር በሚቀርብበት ጊዜ ሁሉ ይታወቅ የነበረው የዊሊንግዶን ውበት በመባል ቢሆንም) በዕ ርሻ ጣቢያው ውስጥ ይሰጠው የነበረው ግምት ከፍተኛ ከመ ሆኑ የተነሣ ፣ ሊናገር የፈለገውን ለማዳመጥ ሁሉም የአንዳ ንድ ሰዓት እንቅልፋቸውን ለመሰዋት ፈቃደኞች ነበሩ ።

በእህል መጋዘኑ ባንዱ ጥግ ፣ እንደ መድረክ ብጤ ከፍ ብሎ በተሠራው ቦታ በገለባ ጉዝጓዝ ላይ ፣ ሜጀር ስፍራውን ይዞ፣ ከላይ አግዳሚው ላይ ከተንጠላጠለው ፋኖስ ሥር ጉብ ብሎ ይታያል ። ዕድሜው አሥራ ሁለት ዓመት ነው ። ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዘርጠጥ ብሏል ፤ ቢሆንም ምንም እንኳ ከራንቻዎቹ ተቈርጠው ባያውቁም ግርማ ሞገሥና የብልኅነትና የደግነት መልክ ያለው ዐሣማ ነው ። ከዚያም ፣ ብዙም ሳይዘገይ ፣ ሌሎች

እንስሳት እየመጡ እንደየባህላቸው አቀማመጥ ተደላድለው ቦታ ቦታቸውን ያዙ ። በመጀመሪያ ፣ ብሉቤል ፣ ጄሲ ፣ እና ፒንቸር የተባሉ ሦስቱ ውሾች መጡ ፤ ከዚያም ዐሣማዎች መጡና ከመድረኩ ቀጥሎ ባለው የገለባ ጉዝጓዝ ላይ ተኙ ። ዶሮዎቹ መጥተው በየመስኮቶቹ ጠርዝ ላይ ሠፈሩ ፤ ዕርግቦቹ በየከንቹ ላይ ሠፈሩ ፤ በጎችና ላሞቹ ከዐሣማዎቹ በስተጀርባ ተኙና ያመነዥኩ ጀመር ።

ሁለቱ ጋሪ ጎታች ፈረሶች ፣ ቦክሰርና ክሎቨር ፣ ዝግ ብለው እየተራመዱ መጥተው አብረው ገቡና ፣ በገለባው ሥር የተደበቁ አንዳንድ አነስተኛ እንስሳት ቢኖሩ በእንደ በጠጉራም ትላልቅ እግሮቻቸው እንዳይረገጡ ፣ በታላቅ ጥንቃቄ አጣጥፈው ተኙ ። ክሎቨር ፣ አራተኛ ግልገልዋን ከወለደች ወዲህ የቀድሞ ቅርፅዋ ከቶ ያልተመለሰላት ፣ ወደ መካከለኛ ዕድሜዋ የተቃረበች እናቲት ግዙፍ ባዝራ ነበረች ። ቦክሰር እጅግ ግዙፍ እንስሳ ነበር ፤ ቁመቱ ወደ ዓሥራ ስምንት እጅ (ስንዝር) ይደርሳል ፤ ደግሞ ጉልበቱ ከማንኛውም ተራ ፈረስ እጥፍ ይሆናል ። ከግንባሩ ወደ አፍንጫው የወረደው ነጭ መስመር ጅል አስመስሎታል ፤ እውነትም ላቅ ያለ የዕውቀት ተሰጦ አልነበረውም ፤ ሆኖም በሁሉም ዘንድ የሚያስከብረው የማያወላውል ጠባይና እጅግ ብርቱ የሥራ ኃይል ነበረው ። ከፈረሶቹ በኋላ ሙርየል የተባለችው ነጭ ፍየል ፣ ቀጥሎም አህያው ቤንጃሚን መጡ ። ቤንጃሚን በዕርሻ ጣቢያው ከነበሩት እንስሳት ሁሉ በዕድሜ ጠና ያለና ከሁሉም የባሰ ጠባይ ያለው እንስሳ ነበር።የሚናገረው አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው ፤ ከተናገረም ፣ እንደልማዱ ፣ ፍሬ—ፈርስኪ የሆነ ነገር ብቻ ነው ። ለምሳሌ ፣ እግዜር ጭራ የፈጠረለት ዝንቦችን ለማባረሪያ እንደ ሆነ ይናገራል ፤ ነገር ግን ከቅርብ ግዜ በኋላ ፣ ጭራም አይኖረኝ ፣ ዝንቦችም ይጠፋሉ ይላል ። በዕርሻ ጣቢያው ውስጥ ካሉት እንስሳት ሁሉ ምን ጊዜም የማይሥቀው እርሱ ብቻ ነው ። ለምን? ተብሎ ቢጠየቅ ፣ ምንም የሚያሥቅ ነገር አላየሁም ፤ ብሎ ይመልሳል ። የሆነ ሆኖ ፣ በይፋ ባያምንም ፣ ለቦክሰር የነበረው ፍቅር እጅግ የጠና ነው ፤ አብዛኛውን ጊዜ ፣ ሁለቱም የእሑድ ቀን ዕረፍት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ፣ ከፍራፍሬ ተክል ቦታ በስተኋላ በሚገኘው መስክ ላይ ፣ ጎን ለጎን በዝምታ እየጋጡ ነው ።

እናታቸው የጠፋችባቸው የዳከዬ ጫጩቶች ፣ ተግተል ትለው ወደ እህል መጋዘኑ በገቡ ጊዜ ፣ ሁለቱ ፈረሶች ተደላድለው ተኝተው ነበር ። ጺውጺውታቸውን እያ ሰሙ የማይረገጡበትን አስተማማኝ ስፍራ በመፈለግ ወዲያና ወዲህ ባዘኑ ። ክሎቨር የተባለችው ባዝራ በትልቁ የፊት እግርዋ እንደ ግድግዳ በከለለችው ቦታ ተሰብስበው በመኰል ኮል ወዲያው እንቅልፍ ወሰዳቸው ። በመጨረሻም ወቅት ፣ ሞሊ የተባለችው የሚስተር ጆንስ ጋሪ ጎታች የነበረችው ፣ ቂላ ቂልና ቆንጆዬ ነጭዋ ባዝራ ፣ እየተኩነሰነሰችና አንዲት የስኳር አንኳር እየቈረጣጠመች መጣች ። ከወደፊት ያለውን ቦታ በመ ያዝ ነጩን ጋማዋን እያብለጠለጠች ፣ ያጌጠችባቸውን ቀያይ የሐር ሪባኖች እዩልኝ እዩልኝ እንደማለት ተኩራራች ። ከሁሉ በኋላ የመጣችው ድመቲቱ ነበረች ። እርሷም ፣ እንደተለመ ደው ፣ ዙሪያውን ቃኘችና ሞቃት ስፍራ ፈልጋ በቦክሰርና በክ ሎቨር መኻል ተሸጕጣ ፣ እዚያው እንዳለች ተደላድላ ስታ ንኳርር ፣ የሜጀር ንግግር በሚካኼድበት ጊዜ ሁሉ አንዲት ቃል እንኳ ሳታዳምጥ ተኝታ አሳለፈች ። ከጓሮ በር መዝጊያ በላይ ሠፍሮ ያንቀላፋ ከነበረው ሞዝስ ከተባለው ለማዳው ቁራ በስ ተቀር አሁን እንስሳቱ ሁሉ ተኝተው ነበር ። ሁሉም ተደላድ ለው ተቀምጠው በጥሞና ለማዳመጥ እየተዘጋጁ መሆናቸውን እንደ ተመለከተ ፣ ሜጀር ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠራረገና እን ዲህ ሲል ንግግሩን ጀመረ ፤

«ጓዶች ፣ ባለፈው ሌሊት ስላየሁት ያልተለመደ ዓይነት ሕልም አስቀድሜ ሰምታችኋል ። ነገር ግን የሕልሙን ጉዳይ በኋላ እመለስበታለሁ ። በመጀመሪያ ላይ የምነግራችሁ ነገር አለኝ ። ጓዶች ፣ ከእንግዲህ ወዲያ እስከ ብዙ ወራት ከእና ንተ ጋር የምኖር አይመስለኝም ፤ ከመሞቴ በፊት ያካበትኩትን ጥበብ ለእናንተ የማስተላለፍ ግዴታ እንዳለብኝ ይሰማኛል ። ረጅም ዕድሜ ኖሬአለሁ ፤ በጋጣዬ ውስጥ ብቻዬን ለረጅም ጊዜ ተጋድሜ ለማሰላሰል ጊዜ አግኝቻለሁ ፤ ባሁኑ ጊዜ በሕይወት ያሉት ማንኛቸውም እንስሳት የሚያውቁትን ያህል ፣ በዚች ምድር ላይ ያለውን የሥነ ፍጥረት ኑሮ ሁኔታ ለመረዳት ብዙ ጊዜ አግ ኝቻለሁ ለማለት የምችል ይመስለኛል ። ልነግራችሁ የምፈል ገው ስለዚሁ ጉዳይ ነው ።

«እንግዲህ ጓዶች ፣ ይህ የእኛ ኑሮ ሁኔታ ምን ይመስላል? እስቲ አትኩረን እንመልከተው ፤ ኑሮአችን መከራና የሥራ ጫና የተሞላበትና የአጭር ጊዜ ኑሮ ነው ። እንወለዳለን ፤ ከመ ካከላችን ሥራ ለመሥራት ብቃት ያላቸው እንስሳት እስከ መጨ ረሻይቱ ሕዋሳቸው ጉልበት ፍጻሜ እንዲሠሩ ይገደዳሉ ። ከዚ ያም ፣ ጉልበታችን መሚጠጡ ሲታወቅ ፣ ወዲያው በሚያሰቅቅ ጭካኔ እንታረዳለን ። አንድ ዓመት ከሞላው በኋላ ፣ ከእንግሊዝ አገር የሚኖር እንስሳ ሁሉ ነጻ አይደለም ። የአንድ እንስሳ ኑሮ የመከራና የባርነት ኑሮ ነው ፤ ሐቁ ይኸው ነው ። ለመሆኑ የሥርዓቱ ኑሮ አንዱ ክፍል ነው ወይ? ይህች ምድራችን ይህን ያህል ድኀ በመሆንዋ ፣ በላይዋ ላይ ለሚኖሩት መጠነኛ ኑሮ ለመ ኖር የሚያስችል ሀብት ሳይኖራት ቀርቶ ነውን? አይደለም፤ጓዶች፣ ሺ ጊዜ አይደለም! የእንግሊዝ አገር መሬት ለም ነው ፤ የአየርዋ ጸባይ ጥሩ ነው ፤ አሁን ከሚኖሩባት እንስሳት ቁጥር እጅግ ለበዙ እንስሳት ምግብ ለማፍራት የምትችል ናት ። ይህች የእኛይቱ ዕርሻ ጣቢያ ብቻ አንድ ደርዘን ፈረሶችን ፣ ሃያ ላሞችን ፣ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ በጎችንና በአሁኑ ጊዜ ከቶ ልናስበው በማንችል ሁሉም በተደላደለና በክብር ልታኖር የምትችል ናት ። ታዲያ ለምንድን ነው በዚህ ዓይነት የችግርና የመከራ ሁናታ ኑሮዋ ችንን የምንገፋው? ምክንያቱም አብዛኛውን የልፋታችንን ፍሬ የሚሰርቀን የሰው ልጅ በመሆኑ ነው ። የችግራችን መፍ ትሔ ሁሉ የተመሠረተው እዚህ ላይ ነው ፣ ጓዶች ። ባንዲት ቃል ላይ የተጠቃለለ ነው ፡— በምድር ያለን እውነተኛ ጠላት ሰው ነው ። ሰውን ከቦታው ማስወገድ ፤ አለቀ ። የረሀብና የሥራ ጫና ምክንያትና መሠረቱ ለዘላለም ተወገደ ማለት ነው ።

«ሳያመርት የሚበላ ፣ ሰው የሚበላው ፍጡር ብቻ ነው»። ወተት አይታለብ ፣ ዕንቁላል አይጥል ፤ ማረሻ ለመጐተት በቂ ጉልበት የለው ፣ ጥንቸሎችን አባሮ ለመያዝ ፈጥኖ መሮጥ የማይ ችል ፍጡር ነው ። ግን የእንስሳት ሁሉ ገዢ ነው ። ያሠራቸ ዋል ፤ መልሶ የሚሰጣቸው ግን በችጋር እንዳይሞቱ የሚያበቃ ቸውን ያህል ብቻ ነው ፤ የተቀረውን ፣ ለራሱ ያውላል ። ሠርተን መሬትዋን እናርሳለን ፤ በእበታችን መሬትዋን እናዳብራለን ። ይሁን እንጂ ከእኛ መካከል ከቈዳው በስተቀር ሌላ ሀብት ያለው የለም ። እናንተ ፣ እዚህ ከፊቴ የማያችሁ ላሞች ፣ በዚህ ባለፈው ዓመት ውስጥ ስንት ሺ ጋሎን ወተት ታልባችኋል? ያን ያህሉስ

ወተት ስንት የጐለበቱ ጥጆችን ባሳደገ ነበር? እያንዳንድዋ ጠብታ በጠላቶቻችን ጉሮሮ ተንቈርቁራለች ። እናንተ ዶሮ ዎችስ፣ባለፈው ፣ዓመት ውስጥ ስንት ዕንቁላሎቻችሁ ናቸው ወደ ጫጩትነት ሊፈለፈሉ የበቁት? የተቀሩት ሁሉ ወደ ገበያ ተወ ስደው ለሚስተር ጆንስና ለእርሱ ሰዎች ገንዘብ ማካበቻ ሆነው ቀርተዋል ። አንቺስ ፣ክሎቨር እነዚያ ፣ በመጦሪያ ዕድሜሽ ጊዜ አጋርና መመኪያሽ ሊሆኑ ይችሉ የነበሩት ፣ የወለድሻቸው አራቱ ግልገሎችሽ የት አሉ? እያንዳንዱ በአንድ ዓመት ዕድ ሜው ተሸጠ ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ልታያቸው አትችይም ። ለአ ራት ጊዜ ወላጅነትሽና በዕርሻው ጣቢያ ለአበረከትሽው ሥራ ውለታ የተሰጠሽ ያችው የዕለት ድርሻና የማደሪያ ጋጣ በስተ ቀር ምን አለ?

«ይህም የመከራ ኑሮዋችን ከመደበኛው ዕድሜ እንኳን ሳይደርስ እንቀጫለን ። እኔ በበኩሌ አላጉረመርምም ፤ ምክን ያቱም ፣ ከዕድለኞቹ አንዱ ነኝ ፤ ዕድሜዬ አሥራ ሁለት ዓመት ሲሆን ፣ ከአራት መቶ ልጆች በላይ ወልጃለሁ ። የዐሣማ ተፈጥሮአዊ ኑሮ ይኸው ነው ። ነገር ግን ፣ ዞሮ ዞሮ ከጨካኙ ካራ የሚያመልጥ እንስሳ የለም ። እናንተ ፣ እዚህ እፊቴ የተቀ መጣችሁት ታዳጊ ዐሣማዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እያ ንዳንዳችሁ ሲጥ እየተደረጋችሁ ፣ በመታረድ ሞታችሁ ከዚሀች ዕርሻ ጣቢያ ትወገዳላችሁ ። ሁላችንም ማምራት ያለብን ወደ ዚሁ አስደንጋጭ አቅጣጫ ነው ።—ከብቶች ፣ ዐሣማዎች ፣ ዶሮ ዎች ፣ በጎች ፣ ሁሉም ፤ ፈረሶችና ውሾች እንኳን ሳይቀሩ የተሻለ ዕድል የላቸውም ። አንተ ፣ ቦክሰር ፣ እኒያ ኃይለኞች ጡንቻዎች የዛሉ ዕለት ፣ ጆንስ ለአራጁ ይሸጥህና አንገትህን ቈርጦ ከለቀ ቀህ በኋላ ፣ የአዳኝ ውሾች ምግብ ያደርግሃል ። አዳኝ ውሾችም ቢሆኑ አርጅተው ጥርሶቻቸው ስለረገፉ ፣ ጆንስ አንገታቸው ላይ ድንጋይ አሥሮ ካቅራቢያው በሚገኘው ኩሬ ውስጥ ያሰ ምጥና ይገድላቸዋል ።

«ታዲያስ ጓዶች ፣ የእኛ ሁሉ የጭቆና አስተዳደር ምንጩ የሰው ልጅ መሆኑ ቁልጭ ያለ ሐቅ አይደለምን? የድካማችን ፍሬ የራሳችን ሀብት እንዲሆን ለማድረግ ከፈለግን ፣ የሰውን ልጅ ማስወገድ ብቻ ነው ። በማግሥቱ ሀብታሞችና ነጻዎች ለመሆን በቻልን ነበር ። ታዲያ ምን ማድረግ አለብን? የሰውን

ዘር አገዛዝ ለመገልበጥ ሌት ተቀን በአካልና በመንፈስ መሥራት አለብን ጓዶች ፤ እኔ የማስተላልፍላችሁ መልእክት ይኸው ነው ፤ ዐመፅ ፤ ይህ ዐመፅ መቼ እንደሚሳካ አላውቅም ፤ ካንድ ሳምንት ወይም ከመቶ ዓመታት በኋላ ሊሆን ይችላል ። ዳሩ ግን ፤ እዚህ እግሮቼ ሥር እንደማያቸው ገለባዎች ያህል ግልጥ ብሎ ይታየኛል ። ውሎ ይደር እንጂ ፍትሕ ይገኛል ። ጓዶች ፤ በዚህች በቀረቻችሁ ባጭር ጊዜ ዕድሜያችሁ ትኩረታችሁን በዚህ ጉዳይ ላይ አውሉ ። ደግሞም ከሁሉም ይልቅ አደራ የምላችሁ ፤ ድል እስከንጐናጸፍ ድረስ ትግሉን እንዲቀጥል ፤ መልእክቱን ከእናንተ ለሚተካው ትውልድ እንድታስተላልፉ ነው ።

«ጓዶች ፤ ደግሞም አስታውሱ ፤ ውሳኔያችሁ ምንጊዜም ቢሆን ማወላወል የለበትም ። አንዳችም ክርክር ሊያዘነጋችሁ አይገባም ። ሰውና እንስሳት የጋራ ጥቅም አላቸው ፤ የአንዱ ብልጽግና የሌሎች ብልጽግና ነው ፤ ሲሉዋችሁ ከቶ አትስሙ ። ሐሰት ነው ። የሰው ልጅ ለራሱ ጥቅም እንጂ ለሌሎች ፍጡሮች ጥቅም አያስብም ። ደግሞም በእኛ በእንስሳት መካከል ፍጹም የሆነ የትግል አንድነት ፤ ፍጹም የሆነ የወዳጅነት መንፈስ ይኑር ። ሰዎች ሁሉ ጠላቶች ናቸው ። እንስሳት ሁሉ ጓዶች ናቸው ።»

በዚህ ጊዜ ኃይለኛ ጩኸት ተፈጠረ ። ሜጀር ንግግር በሚያሰማበት ጊዜ ፤ አራት ትላልቅ ዐይጦች ከጉድጓዳቸው ተሾልከው ወጥተው ፤ በኋላ እግሮቻቸው ቁጢጥ ብለው በመቀመጥ ፤ ንግግሩን ሲያዳምጡ ነበር ። ውሾቹ ድንገት አይተዋቸው ኖሮ ፤ ሕይወታቸውን ለማዳን የበቁት ቶሎ ብለው በየጉድጓዳቸው ገብተው በማምለጥ ነው ። ሜጀር ጸጥታውን ለማስከበር አንዱን የፊት እግሩን በማንሣት ምልክት ሰጠ ።

«ጓዶች» አለ ፤ «አንድ መወሰን ያለበት ጉዳይ አለ ፤ ዐይጦችና ጥንቸሎችን የመሳሰሉ አውሬ ፍጡሮች ፤— ወዳጆቻችን ናቸው ፤ ወይስ ጠላቶቻችን? እስቲ ድምፅ እንስጥበት ። እነሆ ይኸን ጥያቄ ቤቱ ድምፅ እንዲሰጥበት አቀርባለሁ ፤ «ዐይጦች ጓዶች ናቸው ወይ?» በጉዳዩ ላይ ወዲያው ድምፅ ተሰጠና በከፍተኛ የድምፅ ብልጫ ፤ ዐይጦች ጓዶች ናቸው ተብሎ ተወሰነ ። አራት ብቻ የተቃውሞ ድምፅ ነበር ፤ የሦስቱ ውሾችና የድመ

ትዋ ፤ እነርሱም ፣ በኋላ እንደተገለጸው ፣ በሁለቱም ወገን ድምፅ ሰጥተው ተገኝተዋል ። ከዚያም ሜጀር ቀጠለና ፣

«ከዚህ ወዲያ ብዙም የምናገረው የለኝም ። ደግሜ የማሳ ስባችሁ ግን ፣ በሰውና በአድራጐቶቹ ሁሉ ላይ ያላችሁን የጥላቻ ስሜት ምን ጊዜም ማርገብ እንደሌለባችሁ ነው ። በሁለት እግ ሮች የሚሄድ ጠላት ነው ። በአራት እግሮች የሚራመድ ወይም ክንፎች ያሉት ጓድ ነው ። ደግሞም አስታውሱ ፣ ከሰው ልጅ ጋር በምትታገሉበት ወቅት እርሱን መምሰል የለብንም ። ካሸ ነፋችሁትም በኋላ ቢሆን ፣ መጥፎ ልማዶቹን አትከተሉ ። ማን ኛቸውም እንስሳ በቤት ውስጥ መኖር ፣ ወይም በአልጋ ውስጥ መተኛት ፣ ወይም ልብስ መልበስ ፣ ወይም አልኮል መጠጣት ፣ ወይም ትንባሆ ማጨስ ፣ ወይም ገንዘብ መንካት ፣ ወይም በን ግድ ሥራ ላይ መሠማራት የለበትም ፣ የሰው ልጅ ልማዶች ሁሉ እኩይ ተግባሮች ናቸው ። ደግሞም ከሁሉም በላይ ፣ ማን ኛውም እንስሳ በራሱ ዝርያ ላይ የጭቆና ተግባር መፈጸም የለ በትም ። ደካሞች ሆኑ ወይም ኃይለኞች ፣ ጭምቶች ይሁኑ የዋሆች ፣ ሁላችንም ወንድማማቾች ነን ። ማንኛውም እንስሳ ሌላውን እንስሳ መግደል የለበትም ። እንስሳት ሁሉ እኩል ናቸው ።

«ጓዶች ፣ አሁን ደግሞ ፣ ባለፈው ሌሊት ስላየሁት ሕልም እነግራችኋለሁ ። ሕልሙን ተንትኜ ልነግራችሁ አልችልም ። የሰው ልጅ ከምድረ ገጽ ከጠፋ በኋላ ፣ ዓለም ምን እንደምትመ ስል የሚያሳይ ሕልም ነው ። ነገር ግን በነገሬ ላይ የረሳሁትን የድሮ ነገር አስታወስኩ ።

ከብዙ ዓመታት በፊት ፣ የዐማማ ግልገል ሳለሁ ፣ እናቴና ሌሎች ሴት ዐማሞች ይዘምሩት የነበረ የድሮ መዝሙር ነበረ ፣ እነሱም ያውቁት የነበረው ጣዕመ ዜማቸውንና የመጀመሪያ ዎቹን ሦስት ቃላት ብቻ ነበር ። በሕፃንነቴ ከእነ ጣዕመ ዜማው ዐውቀው ነበር ፣—ምን ያደርጋል ! ከአእምሮዬ ከጠፋ ቆየ! ከብዙ ዓመታት በኋላ ፣ ባለፈው ሌሊት በሕልሜ ሲታወሰኝ ዜማውም ቃሉም ጭምር ነው ። እርግጠኛ ነኝ በዚያን ዘመን የእንግሊዝ አገር እንስሳት በሙሉ ይዘምሩት የነበረና ፣ ከብዙ ትውልድ በፊት ጀምሮ የተረሱ ቃላቶች ናቸው ። ጓዶች ፣ አሁን

ያን መዝሙር እዘምርላችኋለሁ ። ስላረጀሁ ድምጼ ጐርንቷል ፤ ነገር ግን ፥ ጣዕመ ዜማውን ካስተማርኳችሁ በኋላ ፥ እናንተው ራሳችሁ በተሻለ ትዘምሩታላችሁ ። የመዝሙሩ አርዕስት «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የሚል ነው ።

ሽማግሌው ሜጀር ጒሮሮውን በትንፋሹ አጸዳና መዘመር ጀመረ ። እውነትም እንዳለው ድምፁ ጐርናና ነበር ፥ ነገር ግን ፥ እንደምንም ብሎ በደኅና ዘመረው ፤ ጣዕመ ዜማውም ቀስቃሽ ነበር ፤ በ«ክሌሜንታይን»እ ና በ«ላኩክራቻ» መካከል ያለ ዜማ ። ቃላቶቹም እንዲህ የሚሉ ናቸው ።

የእንግሊዝ እንስሳት ፥ ያየርላንድ እንስሳት ፤
በምድርና በአየር የምትኖሩ እንስሳት ፤
ስሙኝ ልንገራችሁ አስደሳቹን ዜና ፤
ወርቃማው በሩህ ቀን ለእኛ ይወጣና ።
ይዋል ይደር እንጂ ጊዜውም ተቃርቧል ፤
ጨቋኙ የሰው ልጅ መገልባጫው ደርሷል ።
ፍሬአማ የእንግሊዝ ሜዳዎች በሙሉ ፤
የእንስሳቱ ብቻ ንብረት ይሆናሉ ።

በያፍንጫችን ላይ ያሉት ቀለበቶች ፤
ከጀርባችን ወርደው እነኒህ ኰርቻዎች ።
ልጓም መኰርኰሪያ ሁሉም ይዝጋሉ ፤
ሁሉም ይወድቃሉ ።
ጨካኝ አለንጋዎች መጮኽ ያበቃሉ ።

አእምሮ ሊያስበው ከሚችል በላይ ሀብት ፤
ስንዴውና ገብሱ ፥ አጃና ድርቆሹ ፤
የግጦሽ ሣሩና አትክልት በያይነቱ ፤
በዚያን ጊዜ ፥ ሁሉም የኛ ይሆናሉ ።

ለዚያ ቀን መቃረብ መጣጣር አለብን ፤
ደስታውን ሳናይ የምንሞትም ቢሆን ፤
ላሞችም ፈረሶች ፥ ዝዮችም ዶሮች ፤
ሁሉም ለነፃነት ይሁኑ ታጋዮች ።

የእንግሊዝ እንስሳት ፤ ያየርላንድ እንስሳት ፤
በምድርና ባየር የምትኖሩ እንስሳት ፤
በደኅናም አድምጡ ፤ ደግሞም አስተጋቡ ፤
መጪው ጊዜ ብሩህ እንደሆነ አስቡ ።

የዚህ መዝሙር ጣዕመ ዜማ እንስሳቱን ሁሉ በደስታ አሰከራቸው ። ሜጀር እስከ መዝሙሩ ፍጻሜ እንኳን ሳይደርስ ፣ በገዛ ራሳቸው መዘመር ጀመሩ ። ከመካከላቸው እጅግ ደንቆሮ የተባሉት እንኳን ሳይቀሩ ጣዕመ ዜማውንና ፣ አንዳንዱን ቃላት አጠኑ ፤ እንደ ዐሣማዎችና ውሾች ያሉት ብልኅ እንስሳት ግን ፣ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ሙሉውን መዝሙር በቃላቸው ያዙ ። ከዚያም ፣ ደጋግመው ጥቂት ሙከራ ካደረጉ በኋላ ፣ የዕርሻው ክልል እንስሳት በሙሉ በሚያስደንቅ ኅብር «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የሚለውን መዝሙር ያስተጋቡት ጀመር ። ላሞች በወፍራም ድምፅ (በእምቧታ) ፣ ውሾች በልቅሦ (በማላዘን) ፣ በጎች በጩኸት (በሜሜታ) ፣ ፈረሶች ፣ በሀሀታ ፤ እንዲያውም አለፉችሁ ሁሉም በየተፈጥሮው ባሕርያቸው ስልት በመጮኸ አምስት ጊዜ እየደጋገሙ ዘመሩት ፤ የሚያቋርጣቸው ነገር ባይፈጠር ኖሮ ሌሊቱን በሙሉ ሲዘምሩ ቢያድሩ በወደዱ ።

ከፉቱ ያ ሁሉ ጩኸት ሚስተር ጆንስን ከእንቅልፉ ቀሰቀሰውና ፣ በግቢው ውስጥ ተኩላ እንደገባ በመጠራጠር ፣ካልጋው ዘሎ ተነሣ ። ሁል ጊዜ በመኝታ ቤቱ ውስጥ ካንድ ጥግ የሚቀመጠውን ረሽ አፈፍ አደረገና አንድ ስድስቴ ተኰሰ ። የረሹ እርሳሶች በመጋዘኑ ግድግዳዎች ውስጥ ተሰገሰጉና ስብሰባውም በጥድፊያ ተበተነ ። እያንዳንዳቸው ወደየመኝታ ቦታቸው አመሩ ፣ ወፎቹ ወደየመስፈሪያ ቦታቸው በረሩ ፤ እንስሳቱ በገለባቸው ላይ ተጋደሙና ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዕርሻው እንስሳት በሙሉ እንቅልፍ ወሰዳቸው ።

# ሁ ለ ት

ከሦስት ሌሊት በኋላ ፣ ሽማግሌው ሜጀር በእንቅልፍ ላይ እንዳለ በሰላም ዐረፈ ። አስከሬኑ ከፍራፍሬ ተክሎች ግርጌ ተቀበረ ።

ይኸውም የሆነው በመጋቢት ወር መጀመሪያ ላይ ነው ። በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ውስጥ ብዙ የምስጢር ድርጊቶች ተካሒደዋል ። የሜጀር ንግግር ፣ በዕርሻው ክልል ውስጥ ለነበሩት ብልኅ እንስሳት ፣ ስለ ኑሮ ይበልጥ የተለየ አመለካከት አሳድሮባቸው ነበር ። ሜጀር የተነበየው ሽፍትነት መቼ እንደ ሚፈጸም ትክክለኛውን ቀን አያውቁትም ነበር ፤ በራሳቸው ዕድሜ ይደርሳል ብለው ለማሰብ ምክንያት አልነበራቸውም ፤ ነገር ግን ፣ ለዚሁ ነገር መዘጋጀት እንደነበረባቸው በግልጽ ይታያቸው ነበር ። ሌሎቹን የማስተማሩና የማደራጀቱ ተግባር ያፈረው ፣ ከሌሎቹ እንስሳት ሁሉ ይበልጥ ብልኅ በነበሩት በዐሣማዎቹ ላይ ነበር ። ከዐሣማዎቹ መካከል ይልቅ ስመ-ጥር የሆኑ ፣ ሚስተር ጆንስ ለሽያጭ ያደልባቸው የነበሩ አስኖቦልና ናፖሊዎን የተሠኙ ሁለት ግልገል የዐሣማ ኮርማዎች ነበሩ ። ናፖሊዎን የተባለው ያሣማ ኮርማ ፣ ወፍራምና የጨካኝነት መልክ የሚታይበት ፣ የበርክሻየር ዝርያ ነው ፤ በዕርሻው ውስጥ ያለ እርሱ የበርክሻየር ዝርያ ያለው ዐሣማ አልነበረም ፤ ንግግር አያበዛም ፤ ግን የግሉ የሆነ አደራረግ ነበረው ። እስኖቦል ከናፖሊዎን ይልቅ ንቁ የነበረ ዐሣማ ነው ፤ ባነጋገሩ ይበልጥ ቀልጣፋና ይበልጥ የፈጠራ ችሎታ የነበረው ፤ ዳሩ ግን ፣ የዚያኑ ያህል የጠባይ ጥልቀት እንዳልነበረው ይገመት ነበር ። በዕርሻው ውስጥ የነበሩት ሌሎቹ ወንድ ዐሣማዎች ሁሉ ለእርድ የሚዘጋጁ ነበሩ ። ከእነርሱም መካከል ይበልጥ ታዋቂው እስኩዊለር (ጭርሬ) የተባለው ጉንጨ ድንቡሎና ዓይኖቹ የሚቁለጨለጩ ፣ ቀልጣፋ እንቅስቃሴና ቀጭን ተንጫራሪ ድምፅ ያለው ፣ እንድ ትንሽ ፣ ወፍራም ዐሣማ ነበር ። ብልኅ ተናጋሪም ነበር ፤ ደግ

ሞም ስለ አንድ አስቸጋሪ ጉዳይ በሚከራከርበት ጊዜ ፣ ከጐን ወደ ጐን እንጣጥ እንጣጥ የማለትና ጭራውን የመቁላት ዐመል ነበረው ፤ ይኸውም ሁኔታው በጣም የማሳመን ተሰጥኦ ነበረው ። ሌሎቹ እንስሳት ስለ እስኩዊለር ሲናገሩ ፣ ጥቁሩን ነገር ወደ ነጭ ለመለጠጥ የሚችል ነው በማለት ያደንቁታል ።

የሽማግሌውን ሜጀር ትምህርት ወደ ተሟላ ያስተሳሰብ መልክ ለመለወጥ ፣ እንስሳዊነት በሚል ስያሜ ፣ ዝርዝር ያስፈሩት እነዚህ ሦስቱ ናቸው ። በየሳምንቱ በብዙ ምሽቶች ፣ ሚስተር ጆንስ እንቅልፍ ከወሰደው በኋላ ፣ በመጋዘኑ ውስጥ በድብቅ እየተሰበሰቡ ፣ የእንስሳዊነትን መሠረተ አሳቦች ለሌሎቹ ያስረዳሉ ።

ሌሎቹ ደግሞ ሲጠይቁ «እኛ ከሞትን በኋላ ለሚደርሰው ነገር ምን አስጨነቀን?» ወይም ፣ «ይህ ሽፍትነት መምጣቱ የማይቀር ከሆነ ፣ እንዲፈጸም ለማድረግ ደከምንስ አልደከምን ምን ልዩነት ያመጣል?» ይላሉ ። ዐሣማዎቹ ደግሞ ይኸን መሣይ አስተያየት ከእንስሳዊነት ፍልስፍና የሚቃረን መሆኑን ለማስረዳት በጣም ይጥራሉ ። ከሁሉም የባሱ የጅል ጥያቄዎችን ያቀረበችው ሞሊ የተባለችው ሴቷ ነጭ ፈረስ ነበረች ። ለእስኖቦል ያቀረበችለት የመጀመሪያው ጥያቄ እንዲህ የሚል ነበር ፤ «ከሽፍትነቱ በኋላም ስኳር ይኖራል?»

«አይኖርም» አለ እስኖቦል ፣ ፍርጥም ብሎ ። «በዚህ የርሻ ስፍራ ስኳር ማምረቻ መሣሪያ የለንም ። ከዚህም በተረፈ ፣ ስኳር አያስፈልግሽም ። የፈለግሽውን ያህል አጃና ድርቆሽ ይሰጥሻል ። »

«ደግሞስ ፣ በጋማዬ ላይ ጌጠኛ ሪባኖችን እንዳሁኑ ለማሠር ይፈቀድልኛል?» ብላ ጠየቀች ፣ ሞሊ ።

«ጓድ» አለ እስኖቦል ። «ይህን ያህል የምትወጃቸው እነዚህ ሪባኖች እኮ ፣ የባርነት ምልክቶች ናቸው ። ነፃነት ከሪባኖች እንደሚበልጥ መረዳት ይሳንሻልን?»

ሞሊ ተስማማች ፤ ግን ይህን ያህልም ያመነችበት አልመሰለችም ።

ሙሴ (ሞዝስ) የተባለው ለማዳ ቁራ ይነዛው የነበረውን የውሸት ፕሮፓጋንዳ ለማስተባበል ዐሣማዎቹ ከዚህም የበለጠ ትግል ነበረባቸው ። የሚስተር ጆንስ ልዩ ተወዳጅ ትንሽ እንስሳ የነበረው ሞዝስ ፣ ሰላይና ወሬ አመላላሽ ሲሆን ፣ ብልኅና ጥሩ ተናጋሪም ነበር ። «እንስሳት ሁሉ ከሞት በኋላ የሚሔዱበት ፣ ሹጋርካንዲ ማውንቴን (ስኳርከረሜላ ተራራ) የሚባል አገር መኖሩን ዐውቃለሁ» ባይ ነበር ። የሚገኘውም በሰማይ ላይ አንድ ቦታ ፣ከዳመናዎች በላይ ነው ፤ ይል ነበር ሞዝስ ።«በስኳር ካራሜላ ተራራ በሳምንት ሰባቱ ቀን እሑድ ናቸው ፤ የግጦሽ ሣር ዓመቱን በሙሉ እንደ ለመለመ ነው ። የስኳርና የተልባ ኬክ በየድንበሩ ዙሪያ ይበቅላሉ ።» እንስሳቱ ሁሉ ሞዝስን ይጠሉታል ፣ ምክንያቱም ተረት ከማውራት በስተቀር ሥራ አይሠራም ነበርና ነው ፤ ግን ፣ አንዳንዶቹ ስለ ስኳርካራሜላ ተራራ መኖር ያምኑ ነበር ።

ከሁሉም ይልቅ የዐሣማዎቹ አማኝ ሁለቱ ጋሪ—ጐታች ፈረሶች ፣ ቦክሰርና ክሎቨር ነበሩ ። እነዚህ ሁለቱ ማናቸውንም ነገር በገዛ ራሳቸው አፍልቀው ለማሰብ ከባድ ችግር ነበረባቸው ። ነገር ግን ፣ ዐሣማዎችን እንደ መምህሮቻቸው አድርገው ይቈጥሯቸው ስለነበረ ፣ የሚነገራቸውን ሁሉ ይቀበላሉ ፤ ደግሞም ያላንዳች ክርክር ለሌሎቹ እንስሳት ያስተላልፋሉ ። ምን ጊዜም በመጋዘኑ ውስጥ ይካኼድ ከነበረው ምስጢራዊ ስብሰባ ቀርተው አያውቁም ፤ ደግሞም በየስብሰባቸው ማብቂያ ይዘመር የነበረው «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘውን መዝሙር ይመሩ የነበሩት እነርሱ ናቸው ።

የሽፍትነቱ ተግባር ከታሰበው ጊዜ በጣም አስቀድሞና ማንም ባልጠበቀው ቀላል መንገድ ሊፈጸም ቻለ ። ባለፉት ዓመታትም ፣ ምንም እንኳን ሚስተር ጆንስ ጥብቅ ጌታ ቢሆንም ፣ ዐዋቂ ገበሬ ነበር ፤ ግን ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ክፉ ቀኖች አጋጥመውታል ፤ በአንድ ክስ ምክንያት ብዙ ገንዘብ አውጥቶ ስለነበረ ፍርሀት አድሮበታል — ተስፋ ቈርጧል ፤ ስለዚህ በሚስማማው በላይ መጠጥ መጠጣትን አዘውትረዋል ። አንዳንድ ጊዜ ፣ ቀኑን ሙሉ በወጥ ቤቱ ውስጥ በነበረው መለጠጫ ወንበሩ ላይ ተንጋሎ ፣ ጋዜጦችን እያነበበ ሲጠጣና ዐልፎ ዐልፎ ሞዝስን በቢራ የራሱ የዳቦ ፍራፍሬዎችን ሲመግብ ይውላል ።

ሠራተኞቹም ሥራ ፈቶችና እምነት የማይጣልባቸው ነበሩ ፤ ማሳዎቹም በአረም የተዋጡ ነበሩ ፤ አብዛኞቹ ቤቶች ከዳናቸው እድሳት ያስፈልጋቸዋል ፤ አጥሮቹ ወዳድቀዋል ፤ እንስሳቱ በቂ መኖ አያገኙም ፤ ተርበዋል ።

የሰኔ ወር ደረሰ ፤ ድርቆሹም ለአጨዳ ተቃርቧል ። በበጋው ወራት አጋማሽ ዋዜማ ዕለት ፥ ቅዳሜ ቀን ፥ ሚስተር ጆንስ ወደ ዊንስዶር ሔዶ በ«ቀይ አንበሳ» (ሬድ ላየን) ከመጠን በላይ ጠጥቶ ከመስከሩ የተነሣ ፥ እስከ ማግሥቱ እሑድ እኩለ ቀን ድረስ አልተመለሰም ነበር ። ሠራተኞቹ ጠዋት በጊዜ ላሞቹን አልበው ፥ ለእንስሳቱ መኖ ለመስጠት ሳይጨነቁ ፥ ጥንቸሎቹን ለማደን ወጥተው ነበር ። ሚስተር ጆንስ እንደተመለሰ በቀጥታ ወደ እንግዳ ቤቱ ገብቶ በሶፋው ላይ በመጋደም «የዓለም ዜና ጋዜጣውን» ፊቱ ላይ ዘርግቶ እንቅልፉን ይለጥጥ ጀመር ፤ እስከ ዚህ ምሽት ድረስ ለእንስሳቱ መኖ የሰጣቸው ሰው አልነበረም ። በመጨረሻም ትዕግሥታቸው ተሟጠጠ ። ከላሞቹ አንድዋ የመጋዘኑን መዝጊያ በቀንድዋ ሰብራ በረገደችውና እንስሳቱ ሁሉ በየጎተራዎቹ ውስጥ የተከማቹትን የእህልና የጥራጥሬ ሲሣይ ይሻሙ ጀመር ። ሚስተር ጆንስ ከእንቅልፉ የነቃው ልክ በዚህ ጊዜ ነበር ። ከዚያ በኋላ ፥ እርሱና አራቱ ሠራተኞቹ ወደ መጋዘኑ ውስጥ ገብተው እንስሳቱን ሁሉ በአለንጋና ባርጩሜ ያራውጡ ጀመር ። ይህ ድርጊት የእነዚያ የተራቡትን እንስሳት ቁጣ ሊገታው አልቻለም ። ምንም እንኳን ያን የመሰለ ድርጊት ለመፈጸም አስቀድመው ያቀዱ ባይሆንም ፥ ባንድ ስምምነት ፥ ባሠቃዮቻቸው ላይ ተወረወሩ ፤ ጆንስና ሠራተኞቹ የቀንድና የእርግጫ ናዳ ከያቅጣጫው ይወርድባቸው ጀመር ። ሁኔታውን ፈጽሞ ሊቆጣጠሩት አልቻሉም ። ከዚያ በፊት እንስሳት እንደዚህ ሲሆኑ መቼም መቼ አይተው አያውቁም ፤ እንደ ፈለጉ ይገርፏቸውና ይበድሉዋቸው የነበሩት ፍጡሮች ድንገተኛ ብጥብጥ ከመጠን በላይ አስደነገጣቸው ። ለጥቂት ጊዜ ያህል ለመከላከል ከሞከሩ በኋላ ፥ ተሸንፉና እግሬ አውጭኝ በማለት በሩጫ ተፈተለኩ ። ከአንድ ደቂቃ በኋላ አምስቱም እየሮጡ በጋሪ መንገድ አቋርጠው ወደ ዋናው ጐዳና ሲያመሩ ፥ እንስሳቱ በድል አድራጊነት እየፈነደቁ በማባረር ሸኙዋቸው ።

ወይዘሮ ጆንስ በመስኮት አሻግራ ድርጊቱን ተመለከተችና በጥድፊያ አንዳንድ ንብረቶችዋን ባንድ ምንጣፍ ጠቅልላ አዝላ

በጓሮ ተሾልካ ወጣች ። ሞዝስ ደግሞ ክንፎቹን ዘርግቶ በመብ ረር በኃይል እየጮኸ ተከተላት ። በዚህ መካከል እንስሳቱ ጆን ስና አራቱን ሠራተኞች አባረው ከዕርሻው ቅጥር ግቢ በማስወ ጣት ፡ የግቢውን በር ቀርቅረውባቸው ተመልሰው ነበር ። ስለ ዚህ ፡ ሳይታወቃቸው በተፈጠረው ሁከት አብዮቱ በተሳካ ሁኔታ ፈነዳ ለማለት ይቻላል ። ጆንስ ተወግዶ የማኖር ዕርሻም የግላ ቸው ሆነ ።

ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ደቂቃዎች እንስሳቱ ስላጋጠማ ቸው መልካም ዕድል ሊያምኑ አልቻሉም ። የሥራቸው አሀዱ ባንድነት በመጋለብ ፡ በዕርሻው ዙሪያ ክልል ተሰማርተው የሰው ልጅ በስፍራው አለመኖሩን ማረጋገጥ ነበር ። አረጋግጠው ተመ ለሱ ። ቀጥሎም በጆንስ ዘመነ መንግሥት የነበሩትን ርዝራዦች ለመጠራረግ ወደ ዕርሻው ቤቶች እየሮጡ ተመልሰው መጡ ። በጋጣዎች መጨረሻ ጥግ የነበረው የጭነት ዕቃዎች መጋዘን ተከፈተ ፤ ልጓሞች ፡ ያፍንጫ ቀለበቶች ፡ የውሻ ሰንሰለቶች ፡ ሚስተር ጆንስ ዐሣማዎችንና በጎችን ለማኮላሸት ይጠቀምባቸው የነበሩት የጭካኔ ካራዎች ሁሉ ከውኀ ጉድጓድ ውስጥ ተወረ ወሩ ። ልጓሞችና መያዣ ጠፍሮቻቸው ፡ ዐይን መጋረጃዎቹ ፡ ያፍ መሸበቢያዎች ሁሉ በግቢው ውስጥ ተቀጣጥሎ በነበረው እሳት ውስጥ ተወረወሩ ። አለንጋዎችም እንደዚሁ ፤ አለንጋዎቹ ሲጋዩ ባዩ ጊዜ ፡ እንስሳቱ ሁሉ በደስታ ፈነጩ ። እንደተለመ ደው በዚያ ቀን የፈረሶችን ጋማዎችና ጭራዎች ያጌጡባቸው የነበሩትን ሪባኖች ጭምር እስኖቦልም እሳቱ ውስጥ ወረወራ ቸው ።

«ሪባኖች» አለ ፤ «የሰው ልጅ ምልክት እንደ ሆኑ መቆ ጠር እንደሚገባቸው የልብስ ዓይነቶች ናቸው ። እንስሳት ሁሉ ራቁታቸውን መሆን አለባቸው ።»

በክሰር ይኸን በሰማ ጊዜ ፡ በበጋ ወራት ዝንቦች ጆሮዎቹ ውስጥ እንዳይገቡ የሚከላከልበትን ፡ ከስንደዶ የተሠራውን ትንሹን ባርኔጣውን ፈልጎ አምጥቶ እሳቱ ውስጥ ጣለው ። እን ስሳቱ ባጭር ጊዜ ውስጥ ማንኛቸውንም ፡ ሚስተር ጆንስን የሚ ያስታውሷቸውን ነገሮች ሁሉ ደምስሰው አጠፉ ። ከዚያ በኋላ ፡ ናፖሊዮን ወደ መጋዘን እየመራ ወሰዳቸውና የእህልና የጥራጥሬ

እጥፍ መቁነናቸውን ለያንዳንዳቸው አደላቸው ። ለውሾች ሁለት ሁለት ብስኩት ተጨመረላቸው ። ከዚያም «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የሚለውን መዝሙር ሰባት ጊዜ ከተወጡት በኋላ ፣ የሌሊት ዕረፍታቸውን ለማረፍ ጋደም ጋደም ብለው ከመቼውም ይልቅ ሰላማዊ እንቅልፋቸውን እንቀላፉ ።

እንደ ወትሮዋቸው ሁሉ ፣ ከእንቅልፋቸው በነቁበት በዚያው ማለዳ ፣ ሁሉም የታወሳቸው የትናንቱ ድርጊት ስለነበረ ፣ ባንድነት እየጋለቡ ወደ ግጦሹ ወረዱ ። ከግጦሹ ቦታ ትንሽ ዕልፍ ብሎ ፣ አብዛኛውን የዕርሻ ቦታ የሚያሳይ አንድ ጉብታ ስፍራ ነበር ። እንስሳቱ ሁሉ ወደ ጉብታው ጫፍ ተሽቀዳድመው ወጥተው ፣ በዙሪያው የተንጣለለውን የዕርሻ ቦታ በጠዋቱ ብርሃን ባድናቆት ተመለከቱ ። አዎ ፤ የግል ንብረታቸው ነው ፤ በዙሪያቸው የሚመለከቱት ሁሉ የራሳቸው ንብረት ነው! በዚህ አሳብ ተመስጠው ፣ እዚህም እዚያም እየቦረቁ ወደ ላይ እየዘለሉ ተደሰቱ ። በጤዛው ላይ ተንከባለሉ ጣፋጩን የበጋ ሣር አፋቸውን ሞልተው ጋጡ ፤ የጥቁሩን አፈር እቧራ አስነስተው የለምነት ሽታውን አሸተቱ ። ከዚያም ፣ የዕርሻ ቦታውን ዞረው በመመርመር ፣ የታረሰውን ማሳ ፣ የድርቆሹን መስክ ፣ የፍራፍሬ አትክልቱን ቦታ ፣ ኩሬውን ፣ ጫካውን ሁሉ በታላቅ አድናቆት ጐበኙ። ይህን ሁሉ ነገር ከዚያ በፊት አይተው እንደ ማያውቁ ሲሆኑ ፣ አሁንም ቢሆን ፣ ይህ ሁሉ ሲሣይ የራሳቸው መሆኑን ለማመን አዳገታቸው ።

ወደ ዕርሻው ሕንፃዎች ተንጋግተው በመመለስ ፣ የእነርሱ በሆነው መኖሪያ ቤት ውስጥ ለመግባት ፈርተው ደጃፉ ላይ ቆሙ ፤ ጥቂት እንደቆሙ ፣ እስኖቦልና ናፖሊዮን መዝጊያውን በትከሻቸው ገፍተው በረገዱትና እንስሳቱ ሁሉ ተራ በተራ በመግባት ፣ ኰሽታ ላለማሰማት እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት አረማመድ ፣ በውስጡ ተዘዋወሩ ። ከሹክሹክታ በላይ ድምፅ ለማሰማት ፈርተውና ለማመን የሚያዳግተውን ድሎት ባክብሮት ተመለከቱ ፤ በላባ በተጐሰሩ ፍራሾች የተነጠፉትን አልጋዎች ፣ የፊት መስታዎቶችን ፣ በፈረስ ጭራና በጋማ ፀጉር የተለበጡ ሶፋዎችን ፤ አበባ ምንጣፎችን ፣ በእንግዳ ቤቱ ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን የንግሥት ቪክቶሪያ ምስል ሁሉ ባክብሮትና ባድናቆት እየተመለከቱ ፣ ኰቴያቸውን ሳያሰሙ ካንዱ

ክፍሉ ወደ ሌላው ክፍል እየተዘዋወሩ ጐበኙ ። ሞሊ ከመካከላቸው እንደጠፋች የተረዱት ከመኖሪያ ቤቱ የሚያስወጣውን ደረጃ ሲወርዱ ነበር ። ሌሎቹ ተመልሰው ገብተው ሲፈልጓት ፣ ከዋናው መኝታ ቤት ውስጥ አገኟዋት ። ከሚስስ ጆንስ መልበሻ ጠረጴዛ መሳቢያ ውስጥ አንዲት ሰማያዊ ሪባን አውጥታ በደረቷ ላይ እየሞከረች ፣ እንደ ቂል በመስታወቱ ስትመለከት ነበር ። ሌሎች ክፉኛ ወቀሷትና ወደ ውጭ ወጡ ። በወጥ ቤቱ ውስጥ ተንጠልጥለው የነበሩ ጥቂት ያሣማ ወርች ሥጋዎች ወጥተው እንዲቀበሩ ተደረገ ፤ ከወጥ ቤቱም አጠገብ በነበረው ክፍል ውስጥ የተገኘው የቢራ በርሜል በቦክሰር ኰቴ ተረግጦ ተደፋ ፤ ከዚህ በተረፈ ፣ የዕርሻው ባለቤት መኖሪያ ቤት በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ከነበረው አንዳችም ነገር አልተነካም ። የነበረው ቤት በሙዜውምነት ተጠብቆ እንዲቆይ ፣ እዚያው አንድ ውሳኔ ተላለፈ ። ማንኛውም እንስሳ በዚያ ውስጥ እንዳይኖር ሁሉም ተስማሙ ።

እንስሳቱ ሁሉ ቁርሳቸውን በሉና ፣ እስኖቦልና ናፖሊዮን እንደገና ጠርተው ሰበሰቧቸው ።

« ጓዶች ፤ » አለ እስል ፤ «አሁን አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ሆንዋል ፤ እስኪመሽ ድረስ ረዥም ጊዜ አለን ። ዛሬ የድርቆሽ አጨዳውን ሥራ መጀመር አለብን ። ነገር ግን ፣ ከዚህ አስቀድመን መሥራት ያለብን አንድ ነገር አለ ። »

አሁን ዐሣማቹ እንደገለጹት ፣ ድሮ የሚስተር ጆንስ ልጆች ይጣሉበት የነበረና ከቆሻሻ ማጠራቀሚያው ክምር ላይ ባገኙት አሮጌ የጽሕፈት መማሪያ መጻሕፍት ተጠቅመው ፣ ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ማንበብና መጻፍ በራሳቸው ጥረት ተምረዋል ። ናፖሊዮን ጥቁርና ነጭ ቀለም በማሰሮች እንዲመጣ ላከና ወደ ዋናው ጐዳና ወደ ሚያስወጣው ባለ አምስት የብረት መዝጊያ እየመራቸው ኼዱ ። ከዚያ በኋላ ፣ እስኖቦል (ምክንያቱም በጽሕፈት የሚሻለው እስኖቦል ነበርና) የቀለም ብሩሹን በሁለት ጥፍሮቹ መኻል አስገብቶ ከዋናው በር በላይ ተጽፎ የነበረውን የ« ማኖር ዕርሻ » የሚለውን ጽሑፍ አጠፋና « የእንስሳት ዕርሻ » በሚል ጽሑፍ ተካ ።

ከዚህ ወዲያ ዕርሻው የሚታወቀው በዚህ ስም [illegible] በኋላ ፥ ተመልሰው ወደ እርሻው ሕንፃዎች ኼዱ ፤ ለዚያም እስኖባልና ናፖሊዮን አንድ ረዥም መሰላል እንዲመጣ አስ ደርገው ፥ በትልቁ መጋዘን የመጨረሻ ግድግዳ ላይ ተደግፎ እንዲቆም አስደርገው ፥ በትልቁ መጋዘን የመጨረሻ ግድግዳ ላይ ተደግፎ እንዲቆም አስደረጉ ። ባለፉት የሦስት ወራት ጥናታቸው ፥ የእንስሳዊነትን መሠረታዊ አሳቦች ትእዛዛትን ለማጠቃለል የቻሉ መሆናቸውን አስረዱ ። አሁን እንግዲህ ፥ ሰባቱ ትእዛዛት በግድግዳው ላይ ይጻፋሉ ፤ እነዚህም የማይለ ለወጡ ሆነው ፥ በእንስሳት ዕርሻ ውስጥ የሚኖሩት እንስሳት ሁሉ የሚተዳደሩበት ፥ የማይለወጥ ሕግ ሆኖ እስከ ዘለቄታው ይሠራበታል ። በብዙ ችግር ፥ (ምክንያቱም አንድ ዐሣማ ሚዛኑን ጠብቆ በመሰላል ላይ መውጣት ቀላል ባለመሆኑ ) እስኖቦል በመሰላሉ ላይ ወጥቶ ሥራውን ጀመረ ፤ እስኩዊለርም ከበታቹ ሆኖ የቀለሙን ማሰሮ ያዘለት ። ትእዛዛቱ ፥ ሬንጅ በተለቀለቀው ግድግዳ ላይ ፥ በሩቁ ለመነበብ እንዲቻል በጉልህ ፊደላት ተጻፉ ። ቃሉም እንዲህ ይነበባል ።

## ሰባቱ ትእዛዛት

1. በሁለት እግር የሚኼድ ሁሉ ጠላት ነው ።
2. በአራት እግር የሚኼድ ፥ ወይም ክንፍ ያለው ሁሉ ወዳጅ ነው ።
3. ማንኛውም እንስሳ ልብስ መልበስ የለበትም ።
4. ማንኛውም እንስሳ በአልጋ ላይ መተኛት የለበትም ።
5. ማንኛውም እንስሳ አልኮል መጠጣት የለበትም ።
6. ማንኛውም እንስሳ ፥ ማንኛውንም ሌላ እንስሳ መግ ደል የለበትም ።
7. እንስሳት ሁሉ እኩል ናቸው ።

ጥርት ያለ አጻጻፍ ነበር ፤ ቢሆንም አንድ ሁለት ግድፈቶች ተገኝተዋል ። ሌሎችም እንዲሰሙት እስኖቦል ድምፁን ከፍ አድርጎ አነበበላቸው ። እንስሳቱ ሁሉ ሙሉ ስምምነታቸውን

በራስ ንቅናቄያቸው ገለጹ ፤ ይበልጥ ብልኖቹ ወዲያው ትእዛዛቱን በቃል ማጥናት ጀመሩ ።

«አሁን ፣ ጓዶች» አለ እስኖቦል ፣ ድምፁን ከፍ በማድረግና የቀለሙን ብሩሽ ወዲያ ጥሎ ፣ «በሉ ወደ ድርቆሽ ሜዳ እንኺድ ፣ ጆንስና ሠራተኞቹ ይፈጅባቸው ከነበረው ባነሰ ጊዜ ውስጥ አጭደን ለማስገባት ቃል እንገባለን!»

ነገር ግን ፣ በዚህ ወቅት ፣ ከቅድም ጀምሮ ሲቁነጠነጡ የነበሩት ሦስቱ ላሞች ከፍ ያለ የእምቧታ ድምፅ አሰሙ ። ባለፉት ሀያ አራት ሰዓቶች ጊዜ ውስጥ ሳይታለቡ ቆይተው ስለነበረ ፣ ጡቶቻቸው ሊፈነዱ ተቃርበዋል ። ጥቂት አሰብ ካደረጉ በኋላ ፣ ዐሣማዎቹ ባልዲ አስመጥተው በተሳካ ሁኔታ አለቡዋቸው ፤ ለዚህ ሥራ ጥፍሮቻቸው ያመቹ ነበርና ነው ። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ፣ ብዙዎቹ እንስሳት በጉጉት ዓይን የተመለከቱት ፣ አረፋው የተኩረፈረፈ አምስት ባልዲ ወተት ተገኘ ።

«ይህ ሁሉ ወተት ምን ሊደረግ ነው?» አለ አንዱ ።

አንዷ ዶሮ ስትመልስ ፣ «ጆንስ አንዳንድ ጊዜ ከፊሉን ለእኛ ምግብ መበጥበጫ ይጠቀምበት ነበር» አለች ።

«ለወተቱ አታስቡ ፣ ጓዶች!» አለና ጮኸ ናፖሊዎን ፣ የተደረደሩትን የወተት ባልዲዎች እየከለለ ። «የወተቱ ጉዳይ ይታሰብበታል ፤ የድርቆሹ ሣር አጨዳ ጉዳይ የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ። ጓድ እስኖቦል መንገዱን ይመራችኋል ። እኔ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እከተላችኋለሁ ። ወደፊት ፣ ጓዶች! ድርቆሹ ይጠብቃችኋል!»

ስለዚህ እንስሳቱ ተከታትለው ወደ ድርቆሹ ሜዳ ወረዱና የአጨዳውን ሥራ ጀመሩ ። ማታ ሲመለሱ ግን ፣ ወተቱ እንደ ተሠወረ አስተዋሉ ።

# ሦ ስ ት

ድርቆሹን ሣር አጭደው ለማስገባት ፥ ምንም ያህል ድካ ምና የላብ መንቆርቆር ቢያስከትልባቸው ፥ ተከሰዋል ! ይልቁ ንም ያገኙት ምርት ከጠበቁት በላይ ነው ።

አንዳንድ ጊዜ ፥ ይከብዳልም ፥ ያስቸግራልም ። ምክንያ ቱም መሣሪያዎቹ የተሠሩት ለእንስሳት መገልገያነት ሳይሆን ለሰው አመቺነት ባለው ዘዴ ስለ ነበርና ፥ በሁለት እግሮቹ ቆሞ መሥራትን በሚጠይቀው መሣሪያ ሊገለገልበት የሚችል እንስሳ አለመሆኑ እንቅፋት ሆነባቸው ። ዐሣማዎቹ ግን በጣም ብልኆች በመሆናቸው ለያንዳንዱ ችግር መፍትሔ ያገኙለታል ። ፈረሶቹ ደግሞ ፥ እያንዳንዱን የሜዳውን ስንዝር መሬት ያው ቃሉ ። እንደ እውነቱ ከሆነ ደግሞ የድርቆሽ ሣር አስተጫጨድና አስተሳሠር ሥራ ፥ እነ ጆንስና ሠራተኞቹ ያከናውኑት ከነበረው በተሻለ ሁኔታ ማቀላጠፉን ዐውቀውበታል ። በመሠረቱ ዐሣ ማዎቹ ሌሎቹን ይመሩና ይቆጣጠሩ እንጂ አይሠሩም ነበር ። በዕውቀት ከሌሎቹ ብልጫ ስለነበራቸው መሪነቱን መያዝ እንደ ነበረባቸው የተለመደ ነው ። ቦክሰርና ክሎቨር ራሳቸውን ለአ ጨዳው ወይም ለድርቆሹ ሣር መሰብሰብ ሥራ ፥ በፈረስ ዕቃ አስታጥቀው (በዚህ ጊዜ ልጓም የሚባል ነበር አስፈላጊ እንዳል ነበረ የታወቀ ነው) ላይና ታች በሜዳው ሲመላለሱ ፥ አንድ ዐሣማ ከኋላቸው እየተከተለ «ቼ ፥ ጓድ!» ወይም «ቼ-ኡ-ሽ ተመ ለስ ፥ ጓድ!» እያለ እንዳስፈላጊነቱ ይነዳቸዋል ። እያንዳንዱ እንስሳ ፥ የመጨረሻ ትንሹ ሳይቀር ፥ አንዳችም ሰብል አላባከ ነም ። ሣር ሳይቀር ለቅመዋል ። ዳክዬዎቹና ዶሮዎቹ እንኳን ቀኑን ሙሉ በፀሐይ ላይና ታች በመመላለስ ፥ አነስተኛ የድር ቆሽ ሣር እሥሮችን በመንቁራቸው እያነሡ ለመከመር ይጣጣሩ ነበር ። በመጨረሻ ፥ የሰብል አሰባሰቡን ሥራ ፥ ጆንስና ሠራ ተኞቹ ይፈጅባቸው ከነበረው ጊዜ ሁለት ቀን አስቀድመው

ጨረሱ ። ከዚህም በተረፈ ፣ ዕርሻው አይቶት ከሚያውቀው በጣም የበለጠ ሰብል ነበር ። እንዳችም የባከነ ሰብል አልነበ ረም ፤ ዳክዬዎቹና ዶሮዎቹ ፣ ጥቃቅንዋን ነገር ሁሉ ለማየት ችሎታ በነበራቸው ዓይኖቻቸው በመጠቀም እስከ መጨረሻ ይቱ ቅንጣት ሣር ለቅመው ሰብስበው ነበር ። ደግሞ አንድም እንስሳ አንዲት ጉርሻ እንኳን የሰረቀ አልነበረም ።

በበጋው ወራት ሁሉ የዕርሻው ሥራ በመልካም ሁኔታና ያለ ችግር ተከናወነ ። እንስሳቱ እንዲህ ብለው ያሉ ሰቡትን ያህል ደስ ተሠኙ ። እያንዳንዱ ጉርሻ ምግብ ጥልቅ ደስታን ይሰጣቸ ዋል ። በእርግጥም የሌላው ሸክም የሆኑት የሰው ልጆች ከተወ ገዱ ወዲህ የራሳቸው ምግብ ከሆነ ወዲህ ፤ ባንድ ቂመኛ ጌታ የተጣለላቸው ሳይሆን ፣ በራሳቸውና ለራሳቸው የተመረተ ፣ ለያንዳንዱ የሚሆን የበለጠ ምግብ ነበር ። ምንም እንኳ እንስሳቱ ልምድ ባይኖራቸውም ፣ የበለጠ የመዝናኛ ጊዜም ጭምር አገኙ ። ብዙ ችግሮች አጋጥመዋቸዋል ፦ ለምሳሌ ፣ ባመቱ መጨረሻ ላይ ፣ ሰብሉን በሚሰበስቡበት ጊዜ ፣ ዕርሻው መውቂያ መኪና ስላልነበረው በድሮው ያሠራር ዘዴ ማኼድና ገለባ ውንም በትንፋሻቸው መለየት ነበረባቸው ፤ ነገር ግን ዐሣማዎቹ በብልኀታቸው ፣ ቦክሰርም በጉልበቱ ፣ ዘወትር ከችግር ያወጡ ዋቸዋል ። ቦክሰር የሁላቸውንም አድናቆት ያተረፈ ፈረስ ነው ። በጆንስ ጊዜም ቢሆን በብርቱ ሠራተኛነቱ የታወቀ ሲሆን ፣ አሁን ግን ፣ አንድ ፈረስ ሳይሆን ሦስት ፈረስ እንደ ሆነ የሚያ መት ሆነ ። መላው የርሻው ሥራ በእርሱ ጫንቃ ላይ እንዳረፈ፣ የሚቆጠርባቸው ቀኖች ነበሩ ። ዘወትር በከባድ ሥራ ቦታ በመ ገኘት ፣ ከጥዋት እስከ ማታ ሲገፋና ሲጐትት ይውላል ። በየ ጠዋቱ ከማንም በፊት አኩል ሰዓት አስቀድሞ እንዲጠራው ከአንዱ አውራ ዶሮ ጋር ስምምነት አድርጎ ፣ መደበኛው የሥራ ሰዓት ከመጀመሩ በፊት ፣ ማንኛውንም ይልቅ አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ሥራ በፈቃደኝነት ይሠራል ። ለችግሩ ሁሉና ለማንኛውም እንቅፋት የእርሱ መልስ ፣ «በበለጠ በርትቼ እሠ ራለሁ!» የሚል ነበር — ይኸንኑ የግል መፈክሩ አድርጎ ያዘው ።

ነገር ግን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸው ይጥራሉ ። ለምሳሌ ፣ ዶሮዎችና ዳክዬዎች ፣ በሰብሉ አሰባሰብ ወቅት ፣ የተበተኑትን የእህል ቅንጣቶች በመሰብሰብ አምስት ዳውላ

እህል አድነዋል ። ማንም አልሰረቀ ፤ ማንም በመቁነኑ ያጉረ መረመ የለም ፤ በድሮ ጊዜ ዕለት ተለት ያጋጥም የነበረው ጠብና መናከስ ፥ እንዲሁም የቅናት መንፈስ ፈጽሞ ጠፍቶ ነበር ለማ ለት ይቻላል ። ማንም አይለግምም — ወይም ማንም ለማለት ይቻላል ። በእርግጥ ፥ ሞሊ ማለዳ መነሣት የማይሆንላት ብጤ ሆንዋም በስተቀር ፥ ጥፍሬ ውስጥ ጠጠር ገባብኝ በሚል ሰበብ ከሥራ ሰዓት ማብቂያ አስቀድማ ትለያለች ። የድመትዋ ጠባይ ደግሞ በመጠኑ ለየት ያለ ነበር ። አንድ የሚሠራ ሲኖር ድመ ቲቱ እንደማትገኝ ተደርሶበታል ። ለብዙ ሰዓታት ጠፍታ ትሠ ወርና ፥ በምግብ ሰዓት ፥ ወይም የሥራ ሰዓት ካለፈ በኋላ ፥ ማታ ተመልሳ እንደ ዘበት ትመጣለች ። ነገር ግን የምታቀርባቸው ሰበቦች እጅግ አሳማኝ ከመሆናቸው በላይ ፥ በፍቅር ስሜት ስለ ምታንኳርፍ አሳቦችዋ ጥሩ ናቸው ብሎ ላለማመን ያዳግታል ። ካብዮቱ ወዲህ ፥ አሮጌው አህያ ቤንጃሚን ፥ ምንም የተለወጠ አይመስልም ። በጆንስ ጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ ፥ ሥራውን የሚያከናውነው በዚያው በችኮነት ቀስ ብሎ ነው ፤ ምን ጊዜም ከሥራ አይጠፋም ፤ ምን ጊዜም ደግሞ ትርፍ ሥራ በፈቃደኝ ነት አይሠራም ። ስለ አብዮቱና ስለ ውጤቱ አንዳችም አስተ ያየት አይሰጥም ። «ጆንስ በመባረሩ ከቀድሞው ይበልጥ ደስተኛ አልሆንህም ወይ?» ተብሎ ሲጠየቅ ፥ የሚሰጠው መልስ ፥ «አህዮች ረጅም ዕድሜ ይኖራሉ ። ከእናንተ መኻል የሞተ አህያ ያየ የለም» ይላቸዋል ። እነርሱም ቢሆኑ ፥ እንደዚህ ያለውን የተ ድበሰበሰ ምስጢራዊ መልስ ግድ መቀበል ነበረባቸው ።

እሑድ ቀን ሥራ አልነበረም ። ቁርስ የሚበላው ከተለመ ደው አንድ ሰዓት ዘግይቶ ሲሆን ፥ ከቁርስ በኋላ ደግሞ ፥ በየሳም ንቱ ሳይጓደል የሚፈጸም ሥርዓት ነበር ። በመጀመሪያ ዓላማው በሰንደቁ ላይ ይሰቀላል ። እስኖቦል ፥ የሚስስ ጆንስ የጠረጴዛ ልብስ የነበረ አንድ አረንጓዴ አሮጌ ጨርቅ ከዕቃ ቤት ውስጥ አግኝቶ ፥ በላዩ ላይ ያንድ ኮቴና ያንድ ቀንድ ምስል በነጭ ቀለም ሥሎበታል ። ይኸው ዓላማ ፥ በየእሑድ ዕለት ጠዋት ፥ በዕር ሻው ግቢ አትክልት መኻል ቆሞ በነበረው ሰንደቅ ላይ ይሰቀ ላል ። እስኖቦል እንዳስረዳው ፥ የዓላማው አረንጓዴ ቀለም የሚያመለክተው ፥ የእንግሊዝ አገርን አረንጓዴ ሜዳዎች ሲሆን ፥ በላዩ ላይ የተሣሉት የኮቴና የቀንድ ምስሎች የሚያመለክቱት ፥ የሰው ልጅ ለዘለቄታው በተገለበጠ ጊዜ የሚቋቋመውን ፥ የወደ

ፊቱን የእንስሳዊነት ሪፑብሊክ ነው ። ባንዲራው ከተሰቀለ በኋላ ፣ እንስሳቱ ሁሉ ፣ «ጉባዔው» በመባል ይታወቅ ለነበረው ጠቅላላ ስብሰባ ፣ ወደ ትልቁ መጋዘን ይገባሉ ። በዚሁ ስብሰባ ላይ ፣ የመጪው ሳምንት ሥራ ዕቅድ ይወጣና የውሳኔ አሳቦች ቀርበው ክርክር ይካሄድባቸዋል ። ሁል ጊዜ የውሳኔ አሳቦችን የሚያቀርቡት ዐሣማዎች ነበሩ ። ሌሎቹ እንስሳት ድምፅ እስ ጣጡን ይችሉ ነበር እንጂ ፣ የራሳቸው የሆነ የውሳኔ አሳብ ማፍ ለቅ ከቶ አይችሉም ። እስኖቦልና ናፖሊዎን ምን ጊዜም በክር ክር ወቅት ከማንም የላቀ ተሳትፎ ያደርጋሉ ። ነገር ግን ፣ እነ ዚህ ሁለቱ መቼም መች ስምምነት እንዳልነበራቸው ተስተው ሏል ፤ ከነሱ ማንኛቸውም አንዳች አሳብ ያቀረበ እንደ ሆነ ሌላው እንደሚቃወመው የታወቀ ነበር ። ውሳኔው ከተላለፈም በኋላ እንኳን ፦— በመሠረቱ ማንም በዚያ ጉዳይ ላይ ተቃውሞ ለማቅረብ የማይችል ቢሆንም ፦— የሥራ ዘመናቸውን ለፈጸ ሙና በጡረታ ለሚገለሉት እንስሳት ማረፊያ እንዲሆን ፣ ከፍ ራፍሬ እትክልቶች በስተኋላ የሚገኘው ትንሹ መስክ ይከለል ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ፣ ስለ እያንዳንዱ የእንስሳት መደብ የመ ጦርያ ትክክለኛ ዕድሜ አወሳሰን የተጋጋለ ክርክር ተነሥቶ ነበር ። በየጉባዔው ፍጻሜ ሁሉ ፣ «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» መዝሙር ይዘመርና የቀትር በኋላው ሰዓት ለመዝናኛ ጊዜ የተ መደበ ነው ።

ዐሣማዎቹ የሥራ ቤቱን ክፍል ለራሳቸው ዋና መሥሪያ ቤትነት ለይተው መድበውታል ። በዚህም ክፍል ውስጥ ፣ በየምሽቱ ሰዓት ፣ የብረት ሥራ ፣ የአናጢነትና ፣ የሌሎችንም ሥነ ጥበቦች ዕውቀት ፣ የጆንስ መኖሪያ ከነበረው ቤት ወስ ደዋቸው በነበሩት መጻሕፍት እየተመሩ ይለማመዱ ነበር ። እስኖቦልም በበኩሉ ፣ «የእንስሳት ኮሚቴዎች» በሚለው ድር ጅት ሌሎችን እንስሳት ያደራጅ ነበር ። በዚህ ተግባር ላይ ያላ ንዳች መታከት ይሠራል ። የዕንቁላል ማምረቻ ኮሚቴ ፣ ለዶ ሮዎች ፤ የጽዱ ጭራዎች ማኅበር ፣ ለላሞች ፤ ያውሬ ጓዶችን መልሶ-ማሠልጠኛ ኮሚቴ ፣ (የዚህ ዓላማ ዐይጦችንና ጥንቸሎ ችን ለማዶች ለማድረግ የነበረ ነው) ፤ ለበጎቹ ደግሞ ይልቅ ነጭ ጠጕር ማምረቻ ፤ ደግሞም ከማንበብና ከመጻፍ ትምህርት ክፍ ሎች በስተቀር ፣ ሌሎችም ብዙ እንቅስቃሴዎችን አቋቋሙ ። ባጠቃላይ ፣ እነዚህ ሁሉ ዕቅዶች አልተሳኩም ። ለምሳሌ ፣

አውሬዎችን ለማዶች ለማድረግ የተደረገው ሙከራ ፣ ወዲያው በጅምሩ ፈረሰ ለማለት ይቻላል ። እንደ ድሮው መመራታቸውን ፈጽሞ አልተውም ፤ ደግሞም በልግሥና እያያዝ በተከባከቡ መጠን፡ጭራሹኑ በዕድሉ መጠቀምን አበዙ ። ድመቲቱ በመ ልሶ ማሠልጠኛው ሥራ ውስጥ ገብታ ስለ ነበረ ፣ በመጀመሪ ያው ጊዜ በዚሁ ሥራ በጣም ከፍ ያለ ተሳትፎ አሳይታለች ። አንድ ቀን ፣ ባንድ ጣራ ላይ ተቀምጣ ፣ ከእርሷ ትንሽ ዕልፍ ብለው ተቀምጠው ልትደርስባቸው ላልቻለችው አንዳንድ ጨረ ባዎች ንግግር ስታደርግ ታይታለች ። እንስሳት ሁሉ አሁን እኩል እንደ ሆኑና ማንኛውም ፈቃደኛ የሆነ ጨረባ መጥቶ በመዳፎችዋ ላይ ሊያርፍ እንደሚችል እየነገረቻቸው ነበር ፤ ጨረባዎቹ ግን አልቀረብዋትም ።

ይሁን እንጂ ፣ የማንበብና የመጻፍ ትምህርት ክፍሎች በጣም የተሳኩ ክንውኖች ናቸው ። በመጪው ወራት ፣ እያን ዳንዱ እንስሳ ሊባል ይቻላል ፣ በመጠኑም ቢሆን ከማይምነት ተላቆ ነበር ።

ዐሣማዎቹ ግን ፣ እንከን በሌለው ሁኔታ ማንበብና መጻፍ አስቀድመው ችለዋል ። ውሾቹ በቂ የማንበብ ችሎታ ነበራ ቸው ፤ ነገር ግን ፣ ሰባቱን ትእዛዛት ካልሆነ በስተቀር ፣ ሌላ ምንም ነገር የማንበብ ፍላጎት አልነበራቸውም ። ሙርየል የተ ባላችው ፍየል ፣ ከውሾቹ በመጠኑ በተሻለ ሁኔታ ማንበብ ችላ ለች ፤ ደግሞም በቆሻሻው መጣያ ላይ ካገኘቻቸው የጋዜጦች ቁርጥራጭጮች ለሌሎች ታነብላቸው ነበር ። ቤንጃሚን የተባለው አህያ እንደ ዐሣማም ሁሉ የማንበብ ችሎታ ነበረው ፤ ነገር ግን በችሎታው መቼም መች ሠርቶበት አያውቅም ። እርሱ በሚያ ውቀው መጠን ፣ ለማንበብ የሚያጓጓ አንዳችም ነገር እንደሌለ ይናገራል ። ክሎቨር ፊደሎቹን ሁሉ ተምሮ ሳለ ፣ ፊደሎቹን አገጣጥሞ ቃላትን ለመሥራት አይችልም ። ቦክሰር ከ «መ» ፊደል ወዲያ ማለፍ አልቻለም ። በትልቁ ኮቴው አቧራ ላይ ሀ ፣ ለ ፣ መ ፣ ብሎ ይጽፍና ፣ ከዚያ በኋላ ፣ ዠሮዎቹን ወደ ኋላ ቀስሮ ቆሞ ፊደሎቹን አተኩሮ ይመለከታል ፤ አንዳንድ ጊዜ ግንባሩ ላይ የወረደውን ፀጉር እየነሰነሰ ፣ ከዚያ በኋላ የሚከተለ ውን ፊደል ለማስታወስ ይጨነቃል ፤ ግን አግኝቶት አያውቅም ። በእርግጥም ፣ በየአጋጣሚ ምክንያቶች ወቅት ፣ ሠ ፣ ረ ፣ ሰ ፣ ሽ ፣

ድረስ ተምሮአል ፤ ነገር ግን እነዚህን ካጠና በኋላ ፣ በኋላ ፣ ሐ ፣ እና መን እንደ ረሳቸው ተደጋግሞ ታውቆበታል ። በመጨረሻ አራቱ ፊደላት ይበቁኛል ብሎ ወሰነና ፣ በየቀኑ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ በመጻፍ እንዳይረሳቸው ያደርግ ጀመር ። ሞሊ የራስ ዋን ስም ለመጻፍ የሚያስፈልጉትን ሁለቱን ፊደላት ካልሆነ በስተቀር ሌሎቹን ለማጥናት አልፈለገችም ። እነዚህን ፊደሎች ቀንበጦችን በመገጣጠም አሳምራ ትጽፍና ከዚያ በኋላ ፣ ባንድ ሁለት አበቦች አስጊጣ በዙሪያቸው እየቶንጐራደደች ታደንቃ ቸዋለች ።

በዕርሻው ውስጥ የነበሩት ሌሎቹ እንስሳት ፣ ከ «ሀ» ፊደል ለማለፍ አልቻሉም ። ከጊዜ በኋላ እንደታወቀው ፣ እጅግ ደን ቆሮች ከነበሩት መካከል ፣ እንደ በጎች ፣ ዶሮዎች ፣ እና ዳክዬ ዎች የመሳሰሉት ሰባቱን ትእዛዛት በቃል ማጥናት እንዳልቻሉ ጭምር ተገልጦዋል ። በጣም ተጨንቆ ካሰበ በኋላ ፣ ሰባቱ ትእ ዛዛት ፣ በመሠረቱ ፣ በአንድ መርሆ ሊጠቃለሉ እንደሚችሉ እስኖቦል አስታወቀ ። ማለትም ፣ «ባለ አራት እግር ጥሩ ፤ ባለ ሁለት እግር መጥፎ ።» ይህ መፈክር የእንስሳዊነትን ዋና ዋና መሠረታዊ ሐሳቦችን ያጠቃልላል በማለት ተናገረ ። ይህን መሠ ረተ ሀሳብ በጥቅል የተረዳ ሁሉ ፣ ከሰው ተጽዕኖች ሁሉ ይላ ቀቃል ።

ራሳቸውም ሁለት እግሮች ያላቸው ስለመሰላቸው ወፎቹ ፣ በመጀመሪያ ላይ ተቃወሙ ፤ ነገር ግን ፣ እስቲሰሰባቸው ትክክል አለመሆኑን እስኖቦል ማስረጃ አቀረበላቸው ።

«ጓዶች ፣ ያንዲት ወፍ ክንፍ የመመንደጊያ አካል ክፍል ነው እንጂ የማታለያ አይደለም ። ስለዚህ ፣ እንደ እግር መቆጠር ይኖርበታል ። የሰው መለያው ምልክት ፣ ተንኰሎቹን ሁሉ የሚ ሠራብት «እጅ ነው» አለ ።

ወፎች እስኖቦል በረጃጅም ቃላት ያቀረባቸው ነገሮች አል ገባቸውም ፤ ነገር ግን ፣ ማብራሪያውን ተቀበሉትና ፣ ዝቅተኞቹ እንስሳት ሁሉ አዲሱን መሠረተ ሐሳብ በቃል ለማጥናት ተነ ሣሡ ። «አራት እግሮች ጥሩ ፣ ሁለት እግሮች መጥፎ» የሚለው መፈክር ፤ ትልቁ መጋዘን ክፍል ፣ ከሰባቱ ትእዛዛት ጽሑፍ

በላይ ፣ በመጨረሻ ግድግዳ ላይ በጉልህ ተጽፏ ። በቃል ካጠኑት በኋላ ፣ በጎቹ ስለዚህ መመሪያ ጽኑ ፍቅር አደረባቸውና በመስኩ ላይ ባረፉ ቁጥር ሁሉም በኅብር «አራት እግር ጥሩ ፣ ሁለት እግር መጥፎ ፣ አራት እግር ጥሩ ፣ ሁለት እግር መጥፎ» እያሉ መዘመር ይጀምራሉ ፤ ሲደጋግሙትም ቢውሉ አይሰለቻቸውም ።

ናፖሊዮን ፣ ስለ እስኖቦል ኮሚቴዎች አንዳችም ዝንባሌ አልነበረውም ። የጐለመሱትን ከማስተማር ይልቅ ፣ ወጣቶችን ማስተር የበለጠ ጥቅም ይሰጣል ባይ ነው ። የድርቆሹ ሣር አጨዳ በተገባደደበት ሰሞን ፣ ጄሲና ብሉቤል ዘጠኝ ጠንካራ ቡችሎችን ወልደው ነበር ። እናቶቻቸው ጡት እንዳስጣሉዋቸው ፣ «እኔ ማስተማር አለብኝ» ብሎ ፣ ናፖሌዮን ከእናታቸው ነጥሎ ወሰዳ ቸው ። ከሥራ ቤቱ ክፍል ፣ ከኮርኒሱ በላይ ፣ በመሰላል ብቻ ይደ ረስበት በነበረው ክፍል ውስጥ ደብቋቸው ስለነበረ ፣ በዕርሻው ግቢ ከነመኖራቸውም ተረሱ ።

ወተቱ ወዴት ደረሰ የሚለው ምስጢር ተገለጠ ። በየቀኑ ለዐሣማዎቹ ዱቄት መበጥበጫ ይጠቀሙበታል ። የፖም ፍራፍሬዎች አሁን መብሰል ጀምረዋል ፤ ከፍራፍሬ ዛፎች ሥር ያለው ሣር ፣ በነፋስ ኃይል እየተቀጠፉ በወደቁ ፍሬዎች ተሸፍ ኖዋል ። እነዚህ ፍሬዎች ለሁሉም እንደሚከፋፈሉ እንስሳቱ ገምተው ነበር ፤ ይሁን እንጂ ፣ አንድ ቀን ፣ በተላለፈው ትእዛዝ መሠረት ፣ ንፋስ የጣላቸው ፍሬዎች ሁሉ ለዐሣማዎቹ ጥቅም እንዲውሉ ፣ ተለቅመው ወደ ሥራ ክፍል እንዲወሰዱ ተነገረ ። አንዳንዶቹ እንስሳት በዚህ ጉዳይ ላይ አጉረምርመው ነበር ፤ ነገር ግን ፋይዳ አልነበረውም ። ዐሣማዎቹ ሁሉ ፣ እስኖቦልና ናፖሊንም ጭምር ፣ በጉዳዩ ተስማምተውበታል ። እስኩዊ ለር ለሌሎቹ ማብራሪያ እንዲሰጥ ተላከ ።

«ጓዶች!» ብሎ ጮኸ ። «እኛ ይህን ያደረግነው በራስ ወዳድ ነት መንፈስና በልዩ መብት ነው ብላችሁ እንደማትገምቱ ተስፋ አለኝ! እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ በዙዎቻችን ወተትና ፖም መመ ገብ አንወድም ። እኔ በበኩሌ አልወዳቸውም ። እነዚህን ነገሮች እንድንመገብ ያስገደደን አንድ ዓላማ ብቻ ነው ፤ ጤናችንን ለመ ጠበቅ ። ወተትና የፖም ፍሬዎች ፣ ይህ በሳይንስ የተረጋገጠ ነው ፣ ጓዶች! ለአንድ ዐሣማ ጤንነት መጠበቂያ ያለጥርጥር አስ

ፈላጊ የሆኑ ፍቱን ንጥረ ነገሮችን የያዙ ናቸው ። እኛ ዐሣማዎች ያዕምሮ ሠራተኞች ነን ። የዚህ ዕርሻ አስተዳደርና አደረጃጀት ኃላፊነት የወደቀው በእኛ ጫንቃ ላይ ነው ። ሌት ተቀን የምንጠብቀው የእናንተን ደኅንነት ነው ። ያን ወተት የምንጠጣውና እነዚያን የፖም ፍሬዎች የምንበላው «ለእናንተ» ብለን ነው ። እኛ ዐሣማዎች ኃላፊነታችንን መወጣቱን ብንዘጋ ፣ ምን ይደረስ እንደነበረ ታውቃላችሁ ? ጆንስ ተመልሶ መጥቶ ለማየት የሚፈልግ ማንም እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ ፤ አይደለም እንዴ ጓዶች?» አለ ።

አሁን እንግዲህ ፤ እንስሳቱ ሁሉ በእርግጥ የሚያምኑበት ነገር ቢኖር ፣ ጆንስ ተመልሶ እንዲመጣ አለመፈለጋቸውን ነው ። በዚህ እኳኋን በተገለጠላቸው ጊዜ ፣ የሚጨምሩበት አንዳችም ነገር አልነበረም ። የዐሣማዎችን በመልካም ጤና የመጠበቁ ጉዳይ ከሁሉም በላይ የሚታሰብበት ነገር እንደ ነበረግልጽ ነው። ስለዚህ ፣ ወተቱና ንፋስ የጣላቸው (ከዚያ በኋላ የተለቀሙት) የፖም ፍሬዎች ፣ ለዐሣማዎች ብቻ እንዲጠበቅ ከመስማማት በስተቀር አንዳችም ሌላ ክርክር አላስከተለም ።

## አ ራ ት

በእንስሳት ዕርሻ የተፈጸመው ድርጊት በበጋው ወራት መገባደጃ ላይ ፣ ባውራጃው ክልል በግማሹ ተሠራጨ ። በየቀኑ እስኖቦልና ናፖሊዎን ርግቦቹን ወደ ጐረቤት ዕርሻዎች ይልኩዋቸዋል ። የእነዚህም ርግቦች ተልዕኮ በጐረቤት ዕርሻዎች እንስሳት መኸል እየተደባለቁ ስለ ሽፍትነት ታሪክ እንዲያወሩና «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኙውን መዝሙር እንዲያስተምሩ ነው ።

በዚህ ወቅት ፣ ሚስተር ጆንስ በዊሊንግዶን ዕርሻ በሚገኘው «ሬድ ላየን» (ቀይ አንበሳ) በተሠኘው መጠጥ ቤት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ያሳልፍ ነበር ። ሰሚ ባገኝ ቁጥር በማይረቡ ጥርቅም እንስሳት ፣ በጣም አስፈሪና ፍርደ ገምድል ድርጊት ከንብረቱ እንዴት እንደተባረረ ሲያወራ ይውላል ። ሌሎች ገበሬዎች በመሠረቱ ያዝኑለት ነበር ፤ ግን ፣ በመጀመሪያው ሰሞን ፣ ምንም

ያህል የረዱት ነገር የለም ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ፣ ብጀኘስ ላይ በደረሰው መጥፎ ዕድል መጠቀም የሚችሉበትን ሁኔታ ውስጥ ውስጡን በስውር ያስቡ ነበር ። እንደ ዕድል ሆኖ ፣ ከእን ስሳቱ ዕርሻ የሚዋሰኑት ሁለቱ የዕርሻ ተቋሞች ፣ ያለመግባባትና የቂመኝነት ቅራኔ ነበራቸው ። «ፎክስ ውድ» በመባል ይታወቅ የነበረው አንዱ ፣ በቸልታ የተያዘና ዘመናዊ ያልሆነ ሰፊ የዕርሻ ቦታ ሲሆን ፣ ቁጥቋጦዎች የበዙበት ፣ የግጦሽ ሣሩ የተሟጠጠና ባሳፋሪ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ነበር ። የዚህ ዕርሻ ባለቤት ፣ ሚስተር ፒልኪንግተን ፣ በግዴለሽነት የሚኖር ገበሬ ሲሆን ፣ እንደ ወራቱ አመቺነት ፣ አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው በዐሣ አስጋሪ ነት ፣ ወይም በአደን ነበር ። «ፒንችፊልድ» በመባል ይታወቅ የነበረው ፣ ሌላው የዕርሻ ቦታ ፣ አነስ ያለና የተሻለ ጥንቃቄ የሚ ደረግለት ፣ የዚህ ዕርሻ ባለቤት ሚስተር ፍሬድሪክ ይባላል ፤ ኃይለኛ ፣ ብልጥ ፣ ዕድሜ ልኩን ከክስ ያልተላቀቀና በዋጋ ክርክር ጥብቅነቱ የታወቀ ሰው ነው ። እነዚህ ሁለቱ ሰዎች እንዳቸው በሌላቸው ላይ ከነበራቸው ጥላቻ ብዛት የተነሣ ፣ የግል ጥቅማ ቸውን በሚመለከት ረገድ እንኳን አይስማሙም ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፣ በእንስሳቱ ዕርሻ በደረሰው የሽፍትነት ተግ ባር ሁለቱም በጣም ተደናግጠው ፣ የራሳቸው እንስሳት ስለ ሁኔ ታው ብዙ ወሬ እንዳይሰሙ ለመከላከል ይጨነቁ ነበር ። በመጀ መሪያ ሰሞን ፣ እንስሳቱ የራሳቸውን ዕርሻ በራሳቸው አመራር ያካኼዱ የሚለውን አሳብ በመሣለቅ ሊሥቁባቸው ሞከሩ።«ነገሩ ሁሉ በአሥራ አምስት ቀኖች ውስጥ ያከትማል» ይሉ ነበር ። «የእንስሳት ዕርሻ» የሚለው ስም ሊዋጥላቸው አልቻለም ነበ ርና አሁንም«የማኖርዕ ርሻ» በሚለው ስም ይጠሩታል።) በማኖር ዕርሻ እንስሳቱ እርስ በእርሳቸው ዘወትር እንደተፋጁ ናቸው ፤ ደ ግሞም በየዕለቱ በችጋር ጭምር እየሞቱ ናቸው ፣ ብለው ያስወሩ ነበር ።ጊዜው እያለፈ ሲኼድና እንስሳቱ በእርግጥም በችጋር አለ መሞታቸው ሲታወቅ ፍሬድሪክና ፒልኪንግተን የወሬ ቅኝታ ቸውን ለወጡና ፣ በአሁኑ ጊዜ በእንስሳት ዕርሻ ውስጥ ስለሚፈ ጸሙት የፀመፅ ተግባሮች ማውራት ጀመሩ ። በእዚያ ያሉት እንስሳት የመሰሎቻቸውን ሥጋ መብላት (ካኒባሊዝም) ጀምረ ዋል ፤እርስ በርሳቸው በጋሉ የፈረስ ኮቴ ብረቶች ይሠቃያሉ ፤ በሚስቶቻቸውም በጋርዮሽ ይጠቀማሉ ፤ የሚል ወሬ ነዛ ።

የተፈጥሮን ሕግጋት ተቃውሞ ። ሸፈት ይህን የመሳሰሉትን ዐመጾች ያስከትላል አሉ ፥ ፍሬድሪክና ፒልኪንግተን ።

ይሁን እንጂ እነዚህ ታሪኮች ምን ጊዜም ሙሉ በሙሉ አል ታመኑም ። የሰው ልጆች የተባረሩበትና እንስሳት የራሳቸውን ጉዳዮች በራሳቸው የሚመሩበት ፥ ዕፁብ ድንቅ ዕርሻ የመኖሩ ወሬ ፥ በደብዛዛና በተዛባ መልኩ መዛመቱ አልተቋረጠም ፤ በዓመቱም ውስጥ የሽፍትነት ማዕበል ባገር ቤቱ ውስጥ ሁሉ ተሠራጨ ። በቀላሉ ይገሩ የነበሩት በሬዎች ድንገት ወደ አውሬ ነት ተለወጡ ፤ በጎች አጥሮችን እየጣሱ የተከለሉትን የግጦሽ ሣር በታዎች መደመዱ ፤ ላሞች ባልዲዎችን በርግጫ እየደፉ ወተቱን አፈሰሱ ። የግልቢያ ፈረሶች ከመሮጫ መሥመራቸው እየወጡ ጋላቢዎቻቸውን እያሽቀነጠሩ ይጥሉ ጀመር ። ከሁሉም በላይ ፥ «የእንግዘተዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘው መዝሙር ጣዕመ ዜማ ፥ ግጥሞቹ ሳይቀሩ ፥ በያለበት ታወቁ ፤ ባስደናቂ ፍጥነት ተሠራጩ ።

የሰው ልጆች ፥ ምንም እንኳን ፥ እንደ መሣቂያ ነገር የቈጠሩት ቢያስመስሉም ፥ መዝሙሩን በሰሙ ቁጥር ንዴታቸውን ሊገቱ አልቻሉም ። ይህን መሰሉን የተናቀ እንቶ ፈንቶ እንስሳት እንኳን ተዋርደው ሊዘፍኑት እንዴት እንደበቁ ሊገባን አይችልም ይላሉ ። ይህን መዝሙር ሲዘምር የተገኘ ማንኛውም እንስሳ ፥ እዚያው በዚያው ይገረፍ ነበር ። የሆነ ሆኖ ፥ መዝሙሩ ሊገታ አልቻለም ። «ብላክበርድስ» የተባሉት ወፎች ባጥር ላይ ይዘምሩታል ፥ ርግቦች ከዛፎቹ ጫፍ ላይ በኩኩ መለኩቴ ድምፅ ይዘምሩታል ፤ ያንጥረኞች መዶሻዎችና የቤተስኪያን ደወሎች ይኸንኑ ዜማ ያስተጋባሉ ። የሰው ልጆችም ይህን ድምፅ በሰሙ ቁጥር የወደ ፊቱ መጥፎ ዕድላቸው ትንቢታዊ ድምፅ እየተሰማቸው ውስጥ ውስጡን ያንቀጠቅጣቸዋል ።

በጥቅምት ወር መጀመሪያ ሰሞን ፥ ሰብሉ ታጭዶና ተከምሮ ፥ ከፊሉም ቀደም ብሎ ተወቅቶ ነበር ። አንድ የርግቦች መንጋ በሰማይ ላይ እያንዣበበ መጥቶ በእንስሳቱ ዕርሻ ግቢ ውስጥ በማረፍ ፥ የታላቅ መሸበር ጩኸት አሰማ ። ሚስተር ጆንስና ሠራተኞቹ ሁሉ ፥ ከፎክስውድና ከፒንችፊልድ የመጡት ሌሎች ስድስት ሰዎች ጭምር ፥ ባለአምስቱን የብረት መዝጊያዎች አልፈው ፥ የጋሪ መንገዱን ተከትለው ወደ ዕርሻው ግቢ በማምራት ላይ ነበሩ ። በእጁ ጠመንጃ ይዞ ፊት ፊት ይመራ

ከነበረው ጆንስ በስተቀር ፣ ሁሉም በትሮችን ይዘዋል ። አመጣ ጣቸው የዕርሻውን ቦታ አስለቅቀው እንደ ገና ለመያዝ እንደ ነበር ግልጽ ነው ።

ይህ እንደሚመጣ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የተጠበቀ ነገር ስለ ነበረ ፣ ማንኛውም ዝግጅት ተደርጎዋል ። እስኖቦል ፣ በመኖሪ ያው ቤት ውስጥ አግኝቶት የነበረውን ፣ አንድ አሮጌ የዩልዮስ ቄሣርን የውጊያ ስልት መጽሐፍ አጥንቶ ስለነበረ ፣ የመከላከሉ ውጊያ መሪ ሆነ ። በፍጥነት ትዕዛዙን አስተላለፈና በሁለት ደቂቃ ውስጥ እያንዳንዱ እንስሳ በየተመደበለት ቦታ ላይ ተገኘ።

ሰዎቹ ወደ ዕርሻው ቤቶች እንደ ተቃረቡ ፣ እስኖቦል የመጀ መሪያውን የማጥቃት እንቅስቃሴውን ጀመረ ። ብዛታቸው ሰላሳ አምስት ይደርስ የነበረው ፣ ዕርግቦቹ ሁሉ በሰዎቹ ላይ እየተመ ላለሱ በማንዣበብ በጨኸት አደነቁሩዋቸው ፤ ሰዎቹ ደግሞ ይህን ሲከላከሉ ሳሉ ፣ በየቁጥቋጦው ሥር ተደብቀው የነበሩት ዳክዬዎች እየተግተለተሉ በመውጣት ፣የየሰዎቹን እግር ባቶች ክፉኛ እየነካከሱ አሠቃዩዋቸው ። ይሁን እንጂ ፣ ይህች አነስ ተኛዋ የቁርቋሶ ውጊያ ስልት ሆና ፣ አነስተኛ ትርምስ ለመፍጠር የታቀደች ነበረች ፣ ሰዎቹም ዳክዬዎቹን በቀላሉ በበትሮቻቸው ሊያባርሩ ችለዋል ። ይኸን ጊዜ እስኖቦል ሁለተኛውን የማጥ ቃት ስልቱን ጀመረ ። ሙርየል ፣ ቤንጃሚንና በጎቹ ሁሉ ፣ እስኖ ቦልን አስቀድመው ወደፊት ተንደርድረው ሰዎቹን ከያቅጣጫው በመጎንተልና በመርገጥ አዋከቡዋቸው ፤ ቤንጃሚን ደግሞ ፊቱን እያዞረ በኋላ እግሮቹ ኮቴ በርግጫ ይለትማቸው ጀመር ። ነገር ግን ፣ አሁንም ፣ ሰዎቹ በያዙት በትርና በተጫሙዋቸው ባለወፍራም ምስማር ጫማዎች በመጠቀም አየሉባቸው ፤ ስለዚህ ፣ የማፈግፈግ ምልክት የነበረውን ጨኸት ድንገት እስኖ ቦል ባሰማ ጊዜ ፣ እንስሳቱ ሁሉ ፊታቸውን አዙረው በዋናው በር አድርገው ወደ ግቢያቸው ሸሹ ።

ሰዎቹ የድል አድራጊነት ጨኸታቸውን አሰሙ ። እንደ ገመቱትም ፣ ጠላቶቻቸው ሲሸሹ አዩና ፣ ተበታትነው በመሮጥ ያባርሩዋቸው ገቡ ። እስኖቦልም የፈለገው ልክ ይኸንኑ ነበር ። ግቢው ውስጥ ገብተው እንዳበቁ ፣ ሦስቱ ፈረሶች ፣ ሦስቱ ላሞ ችና በከብቶች በረት ውስጥ ተደብቀው ቆይተው የነበሩትም

ሌሎቹ ዐማማዎች ፣ ድንገት ከኋላቸው ወጥተው አቋረጧቸው ። ይኸን ጊዜ ፣ እስኖቦል የውጊያ ትእዛዝ ሰጠ ። እርሱ ራሱ በቀ ጥታ ወደ ጆንስ አመራ ። ሲመጣ አየውና ጆንስ ጠመንጃውን ደግኖ ተኮሰ ። እርሳሶቹ የእስኖቦልን ጀርባ ጫራርፈው በደም በከሉት ፤ አንዲት በግም ሞታ ተዘረረች ። ላንድ አፍታ እንኳን ሳይቆም ፣ እስኖቦል እንደተንደረደረ ኼዶ ፣ በዚያ ሁሉ ክብደቱ ከጆንስ ቅልጥሞች ጋር ተላተመ ። ጆንስ ባንድ በተከመረ አዛባ ላይ ተንከባልለና ጠመንጃውም ከእጁ አምልጦ ወዲያ ተሽቀነጠረ ። ነገር ግን ፣ ከማንኛውም ይልቅ አስፈሪ ትርኢት ያሳየው ቦክሰር ነበር ፤ በ'ላ እግሮቹ ቆሞ ፣ የፊት እግሮ ትርኢት ያሳየው ቦክሰር ነበር ፤ በኋላ እግሮቹ ቆሞ ፣ የፊት እግ ሮቹን ወደ ሰማይ ይሰቅልና ፣ በብረት ጫማ በተጫሙት ኮቴ ዎቹ ፣ እንደ ድንጉላ ፈረስ በኃይል ይመታል ። የመጀመሪያው ምቱ ያረፈበት ፣ ከፎክስውድ የመጣው አንድ የፈረሶች ጠባቂ ወጣት ፣አናቱ ላይ በመመታቱ በጭቃው ላይ እንደ ተዘረረ ቀረ። ይህን ድርጊት የተመለከቱት ብዙዎቹ ሰዎች በትሮቻቸውን እየ ሁሉ ለመሮጥ ሞከሩ ። ብርክ ያዛቸው ፤ ከዚያውም እንስሳቱ ጣሉ ተሰብስበው በጊቢው ውስጥ ዙሪያውን ያራውጧቸው ጀመር ። በቀንድ ተወጉ ፣ በርግጫ ተረገጡ ፣ በጥርስ ተነከሱ ፣ በላያቸው ላይ ተረማመዱባቸው ። በዕርሻው ውስጥ ከነበሩት እንስሳት ፣ በየልማዱ መሠረት ፣ ቂሙን ያልተበቀለ እንስሳ አልነበረም ። ድመቲቱ እንኳን ሳትቀር ፣ ከጣራ ላይ ተወርውራ ወርዳ ባንዱ የከብት አርቢ ገበሬ ትከሻ ላይ ዐርፋ ፣ ጥፍሮችዋን ባንገቱ ላይ በመትከል ክፉኛ አስጮኸችው ። ወዲያው ክፍት መንገድ እንዳገኙ ፣ ሰዎቹ ከግቢው ወጥተው ለማምለጥ ፣ ወደ ዋናው መንገድ በመሸሽ እሮይታ ተሰማቸው ። በዚህም አኳ ኋን ፣ በአምስት ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ፣ በመጡበት መንገድ ፣ በውር ርደት አፈግፍገው ሲሸሹ ፣ ዳክዬዎቹ እየተከታተሉ ባቶቻቸውን እየነከሱ ሸኙዋቸው ።

ካንዱ በስተቀር ሰዎቹ ሁሉ ኼደዋል ። ወደ ግቢው ውስጥ ተመልሶ ቦክሰር ፣ በጭቃ ላይ ባፍ ጢሙ ተደፍቶ ቀርቶ የነበ ረውን ፣ ፈረስ ጠባቂውን ልጅ በኮቴው ይደባብሳል ። ልጁ አል ተንቀሳቀሰም ።

«ሞትዋል!» አለ ቦክሰር ባዘኔታ ። «ይህን ለማድረግ አሳብ እንኳ አልነበረኝም ። የብረት ጫማዎች መጫማቴን ረስቼ ነው ። ዐውቆ አላደረገውም ብሎ ማን ያምነኛል?»

በጀርባው ላይ ከነበረው ቁስል፤እስካሁንም ደም ይንጠባጠብ የነበረው እስኖቦል ፣ በቁጣ ቃል ፣ «የርኅራኄ ስሜት አያስፈልግም ፣ ጓድ» ብሎ ጮኸና ፣ «ጦርነት ጦርነት ነው ። የሰው ደኅና የሞተው ብቻ ነው» አለ ።

«ሞሊ የት አለች?» ብሎ ጠየቀ አንዱ ። ሞሊ እውነትም ጠፍታለች ። ለጊዜው ሁሉም ተሸብረው ነበር ፤ ምናልባት ሰዎቹ አንዳች ጉዳት አድርሰውባት ይሆናል ፤ ወይ እንዲያውም ይዘዋት ኼደው ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አሳደረባቸው ። ይሁን እንጂ ፣ በመጨረሻው ፣ በጋጣዋ ውስጥ ፣ ራስዋን ከግርግምዋ ውስጥ ከነበረው ድርቆሽ ሣር መኻል ቀብራ ተገኘች ። ጠመንጃው በተተኮሰ ጊዜ ነበር ፈርጥጣ የኼደችው ። ከዚያም ፣ ሌሎቹ ከእርስዋ ፍለጋ በተመለሱ ጊዜ ፣ ለጊዜው ሲመታ ሕሊናውን ስቶ የነበረው ፈረስ ጠባቂው ልጅ ፣ በመካከሉ ሕሊናው ተመልሶለት ፣ ለካስ እግሬ ረውጭኝ ብሎ አምልጦ ኖሮዋል !

በዚህ ጊዜ ፣ እንስሳቱ ሁሉ በታላቅ ደስታ ተሰበሰቡ ፤ እያንዳንዳቸው እየጮኹ በጦርነቱ ላይ ስለፈጸሙት የግል ጀብዱ ይተርካሉ። ወዲያው ያልታሰበ ክብረ በዓል ተደረገ ። ባንዲራው ተሰቀለና ፤ «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘው መዝሙር ተደጋግሞ ተዘመረ ፤ ከዚያ በኋላ ፣ የተገደለችው በግ በታላቅ ክብር ተቀበረች፤ በመቃብርዋ ላይ አጋም እንጨት ተተከለበት። በመቃብሩ አጠገብ እስኖቦል አጭር ንግግር በማድረግ ፣ እንስሳቱ ሁሉ ፣ ለእንስሳት ዕርሻው መዋደቅ እንዳለባቸውና ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ፣ ሕይወታቸውን ጭምር መሰዋት እንደሚገባቸው አበክሮ አሳሰበ ።

እንስሳቱ በሙሉ ድምፅ ባሳለፉት ውሳኔ «አንደኛ ደረጃ የእንስሳት ጀግና» የተሠኘ የጀግንነት ኒሻን እንዲኖር ተወሰነ ፤ ይኸውም ኒሻን እዚያው በዚያው ፣ ለእስኖቦልና ለቦክሰር እንዲሸለም ተደረገ ። ከነሐስ የተሠራ ሜዳልያ ሲሆን፣(እንደ እውነቱ ለመናገር ፣ በሥራ ቤቱ ውስጥ የተገኙ አሮጌ የፈረስ ዕቃ ነሐ

ሶች ነበሩ)። በደረት ላይ የሚደረጉትም በእሑድና በበዓላት ቀኖች ነበር ። ሌላ ደግሞ «ሁለተኛ ደረጃ የእንስሳት ጀግና» የተሠኘ ኒሻንም ነበር ፤ ይኸውም የተሰጠው ለሟቿትዋ በግ ሲሆን ፥ ከሞት በኋላ በሚፈጸመው ሥርዓት ነው ።

ጦርነቱ ምን ተብሎ ይሰየም? ተብሎ በቀረበው ጉዳይ ላይ፥ ብዙ ክርክር ተካኼደ.ል ። በመጨረሻ ፥ «የከብቶች በረት ጦር ነት» ተብሎ እንዲሰየም ተወሰነ ፤ ምክንያቱም ፥ ደፈጣው የተነ ሣው ከዚያ ነበረና ነው ። የሚስተር ጆንስ ጠመንጃ በጭቃው ውስጥ ወድቆ ተገኘ ፤ በመኖርያ ቤቱ ውስጥ በርከት ያሉ የጥ ይት ክምችቶች መኖራቸው ይታወቅ ነበር ። ጠመንጃው በሰን ደቁ ሥር (ግርጌ) እንደ አንድ መድፍ እንዲቆምና በዓመት ሁለት ጊዜ ፥ ማለትም ፥ በጥቅምት ዐሥራ ሁለት ቀን ፥ የከብቶች በረት ጦርነት መታሰቢያ ዕለት ፥ አንድ ጊዜ ፤ እንደዚሁም ፥ በበጋው ወራት አጋማሽ ፥ በሽፍትነት መታሰቢያ ቀን አንድ ጊዜ እንዲ ተኮስ ተወሰነ ።

# አ ም ስ ት

ክረምቱ እየገፋ ሲኼድ ፥ ሞሊ እያደር የባሰ አስቸጋሪ እየ ሆነች ኼደች ። በየዕለቱ ጠዋት ወደ ሥራ የምትመጣው እያረ ፈደች ነው ፤ እንቅልፍ ወስዶኝ ነው ፥ የሚል ምክንያት ታቀርባ ለች ፤ ደግሞም ልትረዳው ያልቻለችው ዓይነት ሕመም እንደሚ ሰማት ትናገራለች ፤ የምግብ ፍላጎትዋ ግን እጅግ የላቀ ነው ። በየምክንያቱ ከሥራ ጠፍታ ወደ ውኃ መጠጫው ኩሬ ትኼዳ ለች ፤ በዚያም ፥ በውኃው ውስጥ የገዛ መልኳን አትኩራ በመመ ልከት ፥ እንደ ሞኝ ፈዛ ትቀራለች ። ነገር ግን ፥ ከዚህ ይልቅ ከባድ ስለሆነ ነገር ጭምጭምታዎችም ጭምር ነበሩ ። አንድ ቀን ሞሊ በደስታ ስሜት ረጅሙን ጭራዋን እየነሰነሰችና አንዲት የድር ቆሽ ሣር እያኘከች በግቢው ውስጥ ስታልፍ ፥ ክሎቨር በምስ ጢር ልታነጋግራት ወደ ጐን ወሰደቻት ።

«ሞሊ!» አለቻት ፤ «አንድ የምነግርሽ ብርቱ ጉዳይ አለኝ ። ዛሬ ጠዋት የእንስሳት ዕርሻን ከፎክስውድ በሚለየው ድንበር ላይ ካለው ተክል ባሻገር ስትመለከቺ አይቼሻለሁ ። ከድንበሩ

ወዲያኛው በኩል ፣ አንድ የሚስተር ፒልክንግተን ሠራተኛ ቆሞ ነበር ። እና—እኔ ራቅ ብዬ ነበር የቆምኩት ፤ ሲያነጋግርሽ ነበር ፤ አንቺ ደግሞ አፍንጫሽን እንዲደባበስ ፈቅደሽ ለት ነበር ። ይህ ምን ማለት ነው ፣ ሞሊ?»

«አላደረገም! አልነበርኩም! ሐሰት ነው!» ብላ ጮኸች ሞሊ ፣ ወዲያና ወዲህ እየዘለለችና መሬቱን በኮቴዋ እየተመተመች ።

«ሞሊ! እስቲ ዐይኔን እይኝ ። ያ ሰውዬ አፍንጫዬን አይደባብስም ነበር ብለሽ ትምይልኛለሽ?»

«ሐሰት ነው!» ብላ ደገመች ሞሊ ፤ ነገር ግን ፣ ቀና ብላ የክሎቨርን ዐይን አላየችም ፤ ከዚያ በኋላ ፣ እየሮጠች በማልቢያ ወደ ሜዳው ፈረጠጠች ።

ክሎቨር አንድ አሳብ ብልጭ አለላት ። ለሌሎቹ ምንም ሳትናገር ፣ ወደ ሞሊ ጋጣ ኼደችና ድርቆሹን በኮቴዋ አገላበጠች ። ከገለባው ሥር የተደበቀ አንድ ትንሽ የስኳር ክምርና የተለያዩ ቀለማት የነበራቸው ብዙ ሪባኖች ነበሩ ።

ከሦስት ቀኖች በኋላ ፣ ሞሊ ጠፋች ። እስከ ጥቂት ሳምንታት ድረስ የት ትገኝ እንደ ነበረ አልታወቀም ነበር ። ከዚያ በኋላ ፣ ከዊሊንግደን ወዲያኛው ወገን መታየቷን ርግቦቹ ገለጹ ። በአንድ የሕዝብ መጠጥ ቤት ደጅ ቆሞ በነበረ ፣ በቀይና በጥቁር ቀለማት ባሸበረቀው የቅንጦት ሠረገላ መጐተቻ ዘንጎች መካከል ቆማለች ። አንድ አሳላፊ የሚመስል ወፍራም ፣ ፊቱ እንደ በርበሬ የቀላ ፣ የፈረሰኛ ልብስ የለበሰ ሰው አፍንጫዋን እየደባበሰ የስኳር አንኳር ያጐረሳት ነበር ። ኮትዋ አዲስ የተሰፋ ሲሆን ፣ በግንባርዋ ላይ የሚወርደው ፀጉርዋ በቀይ ሪባን ተጊጦዋል ። የደላት ትመስላለች ፣ አሉ ርግቦቹ ሲያወሩ ። ዳግመኛ ስለ ሞሊ ያነሣ እንስሳ አልነበረም ።

በጥር ወር እጅግ የበረታ ብርዳም አየር ተከሥቶ ነበር ። መሬቱ እንደ ብረት ጠጠረና በዕርሻው ሜዳ ላይ እንዳችም ሥራ ለመሥራት አልተቻለም ። በታላቁ መጋዘን አዳራሽ ውስጥ ብዙ ስብሰባዎች ተካኼዱ ፤ ዐሣማዎቹም በመጪዎቹ ወራቶች ስለሚሠሩት ሥራዎች ዕቅድ በማውጣት ሥራ ተጠምደው ነበር ። ከሌሎቹ እንስሳት ይበልጥ ብለኅ እንደ ነበሩ በጉልህ ያሳዩት ዐሣማዎች ፣ ስለ ዕርሻው የፖሊሲ ጉዳዮች አወሳሰን የእነርሱ

ፈንታ ነው የሚል እምነት ያሳደረ ቢሆንም ፣ ውሳኔዎቹ በድምፅ ብልጫ መደገፍ ነበረባቸው ።

በእስኖቦልና በናፖሊዎን መካከል የሚፈጠሩት ጠቦች እን ቅፋት ባይሆኑ ኖሮ ፣ ይህ ያሠራር ስልት መልካም ውጤት ባስገኘ ነበር ። አለመስማማት ይቻል በነበረበት ጊዜ ሁሉ ፣ እነዚህ ሁለቱ በየነጥቡ ላይ ሁሉ ይቃረናሉ ። ከእነሱ አንዱ ከዕርሻው ይበልጥ ክፍሉ ገብስ ይዘራ የሚል አሳብ ካቀረበ ፣ ሌላኛው ከዕር ሻው ይበልጥ ክፍሉ አጃ ይዘራ የሚል አሳብ እንደሚያቀርብ የታወቀ ነበር ፤ ደግሞ አንደኛቸው እንዲህ እንዲህ ያለው ማሳ ለጎመን ተክል ይልቅ አመቺ ነው ያለ እንደሆነ ፣ ሌላኛው ለሥራ ሥር ተክል እንጂ ለሌላ ፈጽሞ አይሆንም ይላል ። እያንዳንዱ የራሱ ደጋፊ ነበረውና አንዳንድ ብርቱ ክርክሮች ይፈጠራሉ ።

በጉባዔዎች ወቅት እስኖቦል በብልኅ አነጋገሩ ፣ ብዙውን ጊዜ የምድፅ ብልጫውን ያሸንፍ ነበር ፤ ነገር ግን ፣ ናፖሊዮን በስብሰባዎች ማቋረጫ ወቅት ፣ የራሱን ደጋፊዎች የማግባባት የተሻለ ችሎታ ነበረው ።

በተለይም በበጎቹ ዘንድ ይበልጥ ተደማጭነትን አግኝ ቷል ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፣ በጎቹ በወቅቱም ይሁን ከወቅቱ ውጭ «አራት እግሮች ጥሩ ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ» እያሉ መጮኽን አዘውትረዋል ፤ ስለዚህ ፣ በዚህ ጩኸታቸው ብዙውን ጊዜ ጉባዔውን ያቋርጡ ነበር ። የእስኖቦል ንግግር በጣም በሚጋጋ ልበት ወቅት ፣ በተለይ ሆን ብለው ለማቋረጥ «አራት እግሮች ጥሩ ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ» እያሉ መጮኹን ልምድ እንዳ ደረጉ ታውቋል ።

እስኖቦል ከመኖሪያ ቤት ውስጥ ባገኛቸው «ገበሬውና ከብት አርቢው» በሚል አርእስት የታተሙትን አንዳንድ አሮጌ መጽሔቶች በማጥናት ፣ ለአዳዲስ ግኝቶችና ማሻሻያ ዎች ብዙ ዕቅዶችን እያወጣ ነበር ። ስለ ዕርሻ ቦታ ቦዮች ፣ ስለ እንስሳት ማደለቢያ መኖና ስለመሳሰሉት ጠቃሚ ነገሮች በምሁር ቋንቋ ያስረዳል ፤ ደግሞም ፣ በጋሪ የማጓጓዙን ሥራ ለማስቀረት ፣ እንስሳቱ እበታቸውን ሁሉ በዕርሻው ላይ ፣ በተለያዩ ቦታዎች ፣ በየቀኑ እንዲጥሉ ለማድረግ አንድ አስቸጋሪ ዕቅድ አውጥቶ ነበር ።

ናፖሊዎን የራሱ የሆነ አንዳችም ዕቅድ አላወጣም ። ነገር ግን የእስኖቦል ዕቅዶች ምንም ውጤት እንደ

ማይኖራቸው በስውር ይናገር ነበር ፤ አመቺም ጊዜውን የሚጠ ብቅ ይመስላል ። ነገር ግን ከተቃረኑባቸው ጉዳዮች ሁሉ ፥ በንፋስ ወፍጮው ጉዳይ ላይ የተነሣውን ያህል የከረረ አልነበረም ።

ከግጦሹ ቦታ ዐለፍ ብሎ ፥ ከርሻው ቤቶች ብዙም ያልራቀ ከርሻው ቦታዎች ሁሉ በላይ ከፍታ የነበረው ፥ አንድ ጉብታ አለ ። መሬቱን ዞሮ ከመረመረ በኋላ ፥ ይህ ቦታ ለነፋሱ ወፍጮ መትከያ በጣም አመቺ ነው በማለት ፥ የንፋስ ወፍጮውም ዲናሞ በማዞር ለዕርሻው ቦታ በሙሉ በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት እንደሚያስችል እስኖቦል አስታወቀ ። የኤሌክትሪኩም ኃይል ለጋጣዎቻቸው ሁሉ መብራት ከመስጠቱም በላይ ፥ በክረምት ወራት ያሞቃቸዋል ፤ ደግሞም ክብ መጋዝ ፥ የሣር ማጨጃ ፥ የእንስሳት መኖ መከተፊያ ፥ የወተት ማለቢያ መሣሪያዎችን ያንቀሳቅሳል ። እንስሳቱ ከዚያ በፊት ይህን የመሰለ ነገር ሰምተው አያውቁም ፤ (ምክንያቱም የዕርሻው ተቋም ኋላ ቀር ከመሆኑ የተነሣ ፥ መሣሪያዎቹም ሥልጣኔ ያፈራቸው ዓይነት አልነበሩም።) እነርሱም ፥ የእጅግ አስደናቂ መሣሪያዎችን ሥዕሎች ፥ እስኖቦል በምትሀታዊ ቅልጥፍና ሲያሳያቸውና ፥ እነዚህም መሣሪያዎች የእነሱን ሥራዎች እየሠሩ ሳሉ ፥ እነርሱ ተዝናንተው በግጦሽ ሜዳዎቻቸው ላይ እንደሚሰማሩ ፥ ወይም በንባብና በውይይት አዕምሮዋቸውን እንደሚያዳብሩ ሲነግራቸው በአድናቆት አዳመጡ ።

በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ፥ የእስኖቦል የነፋስ ወፍጮ ፕላን ሥራ በሙሉ ተጠናቀቀ ። ሜካኒካዊ ዝርዝሮቹ አብዛኞዎቹ የተገኙት ፥ የሚስተር ጆንስ ንብረት ከነበሩት ሦስት መጻሕፍት ነው ፦ «ለቤት አገልግሎት እንዲውሉ መሠራት ያለባቸው አንድ ሺ ጠቃሚ ነገሮች» «እያንዳንዱ ሰው የራሱ ግንበኛ»፥ እና «ኤሌክትሪሲቲ ለጀማሪዎች» ከሚሉት መጻሕፍት ነው ።

እስኖቦል ለራሱ ቢሮ ይገለገልበት የነበረው ፥ ቀድሞ ለእንቁላሎች መፈልፈያ ይጠቀሙበት የነበረና ፥ ለንድፍ ሥራ አመቺ የሆነ ቀጥተኛ የሣንቃ ወለል ባለው ቤት ውስጥ ነው ። በየቀኑ ለብዙ ሰዓቶች እዚያ ውስጥ ተዘግቶ ይውላል ። መጻሕፍቶቹን ገልጦ ካንድ ድንጋይ ላይ ያስደግፍና ፥ ጠመኔውን በኮቴ

ዎቹ ጥፍሮች መካከል ስከቶ ፥ ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተጣደፈ በመንቀሳቀስ ፥ መሥመሮቹን አቀጣጥሎ ካሠመረ በኋላ ፥ በቀጭን ድምፅ የደስታ ጩኸቶችን ያሰማል ። እያደር የፕላኑ ንድፍ ሥራ በመዘውሮችና በባለ ጥርስ ክብ ምስሎች ተቀነባብሮ እያደገ ኼደ ፤ ሌሎቹ እንስሳት ፥ ሊረዱት ባይችሉም ፥ መደነቃቸው አልቀረም ። ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ እየመጡ ይመለከቱታል ። ዶሮዎቹና ዳክቹዬቹ እንኳን ሳይቀሩ ይመጡና ፥ የጠመኔዎቹን መሥመሮች ረግጠው እንዳያጠፉ ይጠነቀቃሉ ። ገለልተኛ ሆኖ የነበረው ናፖሌዎን ብቻ ነበር ። ከመጀመሪያው ጀምሮ ነው ፥ የንፋስ ወፍጮውን ጉዳይ የተቃወመው ። ይሁን እንጂ ፥ አንድ ቀን ፥ ፕላኖቹን ለመጐብኘት ድንገት ሳይታሰብ መጣ ። በቤቱ ዙሪያ ተንጐራደደ ፤ የፕላኖቹን እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ አትኩሮ ተመለከተና አንድ ወይም ሁለት ጊዜ አነፈነፈባቸው ፤ ከዚያም ፥ የጐሪጥ እየተመለከታቸው ለጥቂት ጊዜ ቆየ ፤ ከዚያ በኋላ ፥ በድንገት እግሩን አንሥቶ በፕላኖቹ ላይ ሽንቱን ሸናና ፥ አንድም ቃል ሳይናገር ወጥቶ ኼደ ።

በንፋስ ወፍጮው እርእሰት ላይ ፥ የርሻው እንስሳት በሙሉ ትልቅ ልዩነት ነበራቸው ። ይኽን ለመሥራት ከባድ ድካም የሚጠይቅ መሆኑን እስኖቦል አልካደም ። ድንጋይ በሸክም ተግዞ በግንብ መልክ መታነፅ ይኖርበታል ፤ ከዚያ በኋላ ፥ የንፋስ መቅዘፊያ መዘውሮች መሠራት ይኖርባቸዋል ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ፥ ዲናሞዎችና የኤሌክትሪክ ሽቦዎች ያስፈልጋሉ ። (እነዚህ ነገሮች እንዴት እንደሚገኙ እስኖቦል አልተናገረም ።) ነገር ግን በአንድ ዓመት ውስጥ ተጠናቆ እንደሚያልቅ እስኖቦል ተናግሮዋል ። ከዚያም በመቀጠል ሲያብራራ ፥ አብዛኛው የሥራ ድካም ከመቃለሉ የተነሣ ፥ እንስሳቱ መሥራት የሚያስፈልጋቸው በሳምንት ሦስት ቀን ብቻ እንደሚሆን አስታወቃቸው ። ናፖሊዎን ፥ በሌላ አንጻር ፥ ባሁኑ ጊዜ ዋናው ተፈላጊ ነገር የምግብን ምርት ከፍ ማድረግ መሆኑንና ፥ በነፋስ ወፍጮው ሥራ ላይ ጊዜያቸውን ካባከኑ ፥ ሁሉም በችጋር እንደሚያልቁ አስረዳ ። እንስሳቱ በሁለት መፈክር ሥር ፥ ማለትም ፥ «ለእስኖቦልና በሳምንት ሦስት ቀን ለሚለው ድምፅ ስጡ» እና «ለናፖሊዎንና ለግርግም ሙሉ ምግብ ለሚለው ድምፅ ስጡ!» በማለት በሁለት ቡድኖች ተደራጁ ። የማንኛውም ቡድን ደጋፊ ያልነበረው ፥ የዕርሻው ቦታ ብቸኛ እንስሳ ፥ ቤንጃሚን ነበር ።

ምግብ ይበልጥ ይትረፈረፋል በሚለውም አሳብ ሆነ ወይም የነፋሱ ወፍጮ ሥራ ያቃልላል የሚሉትን ለማመን አል ፈለገም ። «የነፋሱ ወፍጮ ኖረም አልኖረ ፣ ኑሮ እንደ ነበረ ፣ ማለትም በመጥፎ ሁኔታ ይቀጥላል» ይላል ።

በነፋስ ወፍጮው ላይ ከነበረውም ክርክርም ሌላ ፣ ስለ ዕር ሻው ቦታ የመከላከያ ጉዳይ ሥጋት ነበር ። ምንም እንኳ የሰው ልጆች በከብቶች በረት ጦርነት ላይ የተሸነፉ ቢሆኑም፣ የዕርሻውን ቦታ መልሶ ለመያዝና ሚስተር ጆንስን ለመመለስ ፣ ሌላና ይልቅ ቁርጠኛ የሆነ ሙከራ እንደሚያደርጉ ሙሉ በሙሉ ይታመን ነበር። ይኸንንም የሚያደርጉበት የበለጠ ምክንያት ነበራቸው፤ የሽፍትነታቸው ወሬ በባላገሩ ሁሉ ተዛምቶ ፣ የጎረቤት ዕርሻ ቦታዎችንም እንስሳት ከመቼውም ይበልጥ ሞገደኞችና አልገራ ባዮች አድርገዋቸው ነበረና ነው ። እንደ ተለመደው ፣ እስኖቦልና ናፖሊዮን ባሳብ አልተስማሙም ። ናፖሊዮን እንደሚለው ፣ እን ስሳቱ ማድረግ ያለባቸው ፣ የጦር መሣሪያዎችን ገዝተው ስላጠ ቃቀማቸው ራሳቸውን ማሠልጠን ነው ። እስኖቦል እንደሚ ለው ርግቦችን በብዛት መላክና በሌሎች ዕርሻዎች እንስሳት መካከል ሽፍትነት ማነሣሣት ነው ። እንደኛው እንደሚለው የመከላከያ ኃይላቸውን ካላጠናከሩ ለሽንፈት ይጋለጣሉ ፤ ሌላው እንደሚለው ፣ ቢያለበት ሽፍትነት ከተነሣ ፣ ራሳቸውን መከላከል አያስፈልጋቸውም ። እንስሳቱ መጀመሪያ ናፖሊዮንን አዳመጡ ፤ ቀጥሎም እስኖቦልን ፤ ግን የትኛው ትክክል እንደ ነበረ ሊወስኑ አልቻሉም።በእግርጥም ፣ በወቅቱ ንግግር ሲያደርግ ከነበረው ጋራ ይስማሙ እንደነበረ ራሳቸውም ብዙ ጊዜ ተገን ዝበውታል ።

እነሆ ፣ የእስኖቦል ፕላኖች የተጠናቀቁበት ቀን ደረሰ ። በተከታዩ እሑድ ጉባዔ ፣ የነፋስ ወፍጮው ሥራ ይጀመር ወይን በሚለው ጥያቄ ላይ ድምፅ ሊሰጥበት ነው ። እንስሳቱ በታላቁ መጋዘን አዳራሽ ውስጥ በተሰበሰቡ ጊዜ ፣ እስኖቦል ተነሥቶ ቆመ ፤ ምንም እንኳን የበጎቹ ጩኸት ዐልፎ ዐልፎ ቢያቋርጥም ፣ የነፋሱ ወፍጮ እንዲሠራ የሚደግፍበትን ምክንያቶች አቀረበ ። ከዚያ በኋላ ፣ ናፖሊዮን ተሥነቶ መልስ ሰጠ ። የነፋሱ ወፍጮ እንዳችም ጥቅም የሚሰጥ ስላይደለ ፣ ማንም የድጋፍ ድምፁን እንዳይሰጥ በርጋታ አሳሰበ ፣ ወዲያው ተመልሶ ተቀመጠ ። የተ

ናገረውም ለሰላሳ ሰኮንድ እንኳን አይሆንም ፤ ደግሞም ፣ ንግግሩ ስሜት ቢያሳድር ፣ ባያሳድር ፣ ግድ ያልነበረው ይመስል ነበር ። በዚህ ጊዜ ፣ እስኖቦል ፈጥኖ ተነሥቶ ቆመና ፣ እንደ ገና መጮኽ ጀምረው የነበሩትን በጎች ዝም አሠኝቶ ፣ የነፋስ ወፍጮው ሥራ ድጋፍ እንዲያገኝ በጥልቅ ስሜት በመማጠን ንግግሩን ጀመረ ። እስካሁን ድረስ ፣ እንስሳቱ ስሜታቸው እኩል በኩል የተከፋፈለ ነበር ለማለት ይቻላል ፤ ነገር ግን ፣ የእስኖቦል አንደበተ ርቱዕ ነት ባንድ አፍታ ስሜታቸውን ማረከው ። ከእንስሳቱ ጫንቃ ላይ አስከፊው ሥራ በተነሣ ጊዜ ፣ የእንስሳት ዕርሻ ምን መልክ እን ደሚኖረው ፣ እጅግ እንፀባራቂ በሆኑ ዐረፍተ ነገሮች ሣለላቸው ። አሳቡ አሁን ከሣር ማጨጃዎችና ከእንስሳት መኖ መከተፊያዎች ዐልፎ ተንደርድሮዋል ። ኤሌክትሪክ ፣ ለእያንዳንዱ ጋጣ የኤሌ ክትሪክ ብርሃን ፣ ሙቅና ቀዝቃዛ ውኃ ፣ የኤሌክትሪክ ማሞቂያም ለማደል ከመቻሉም በላይ ፣ የመውቂያ መኪናዎችን ፣ ማረሻ ዎችን ፣ ያፈር መከስከሻዎችን ፣ መዳመጫዎችን ፣ እንደዚሁም አጭዶ ማሠሪያዎችን መኪናዎች ሁሉ ያንቀሳቅሳል ፣ ብሎ አስረ ዳቸው ። ንግግሩን ጨርሶ ካበቃ በኋላ ፣ የድጋፉ ድምፅ ወዴት እንደሚያመዝን የሚያጠራጥር አልነበረም ። ነገር ግን ፣ ልክ በዚህ ወቅት ፣ ናፖሊዎን ተነሥቶ ቆመና ለየት ያለ የግልምጫ አስተያየቱን በእስኖቦል ላይ ተክሎ ፣ ከዚያ በፊት እንደዚህ ሲጮኽ ማንም ባልሰማው ከፍተኛ ቀጭን ድምፅ ጩኸቱን አንባረቀው ።

በዚህ ጊዜ ፣ በጣም አስፈሪ የውሾች ጩኸት ከውጭ ተሰ ማና ፣ በነሐስ የተሸለሙ ያንገት ጠፍሮችን ያሠሩ ፣ ዘጠኝ ወደል ውሾች እየዘለሉ ወደ መጋዘኑ ውስጥ ገቡ ። በቀጥታ ወደ እስኖ ቦል ሮጡ ፤ እርሱም በጥርሳቸው ሳይዘነጥሉት ለጥቂት አመለጠ ። በዚያችም ወቅት ፣ በበሩ ተፈትልኮ ሲወጣ እነሱም ተከተሉት ። ከመጠን በላይ ተደንቀውና ለመናገር ፈርተው ፣ እንስሳቱ ሁሉ በሩ ላይ ተከማችተው የማሳደዱን ትርኢት ይመለከቱ ጀመር ። እስኖቦል ወደ መንገዱ በሚወስደው የግጦሽ ሜዳ ላይ ሮጠ ። ይሮጥ የነበረውም ልክ አንድ ዐሣማ ሊሮጥ ይችል የነበረውን ያህል ብቻ ነው ፤ ግን ውሾቹ ሊደርሱበት ምንም ያህል አልቀራ ቸውም ። ድንገት አዳለጠውና ፣ ሊይዙት ነው የሚል እምነት አሳድሮ ነበር ። ከዚያም እንደ ገና ተነሣና ፣ ከመቼውም በበለጠ ፍጥነት ይሮጥ ጀመር ፤ ከዚያ በኋላ ፣ ውሾቹ እንደ ገና ደረሱበት።

ከውሾቹ አንዱ ደርሶ የእስኖቦልን ጭራ በመንጋጋዎቹ ለቀም አደረገው ፤ እስኖቦል ግን ፣ ጭራውን አወዛወዞ ለጥቂት አስለቀ ቀው ። ከዚያ በኋላ ፣ ስንዝር ያህል ርቀት ሲቀረው ፣ በበለጠ ፍጥ ነት ተፈትልኮ በአጥሩ ቀዳዳ ተሾለከና ካይናቸው ተሠወረ ።

በዝምታና በፍርሐት ስሜት ፣ እንስሳቱ ወደ መጋዘኑ አዳ ራሽ ውስጥ ተመልሰው ገቡ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፣ ውሾቹ እመር እመር እያሉ ተመልሰው መጡ ። በመጀመሪያው ጊዜ ፣ እነዚህ ፍጥረቶች ከየት እንደመጡ ለመገመት የቻለ ማንም አልነበረም ። ነገር ግን ፣ ችግሩ ወዲያው ተፈታ፣ ናፖሊዮን ከእናቶቻቸው ነጥሎ በግል ያሳደጋቸው ቡችሎች ኖረዋል ። ምንም እንኳን ገና ሙሉ በሙሉ ያደጉ ባይሆኑም ፣ በጣም ትላልቅና እንደ ተኩላ አውሬ መሣይ ውሾቹ ነበሩ ። ወደ ናፖሊዮን ተጠጉ ። ሌሎቹ ዎሾች ለሚስተር ጆንስ ያደርጉ በነበረው ዓይነት ለእርሱ ጭራቸውን ይቆሉ እንደ ነበረ ታይቷል ።

ናፖሊዮን ፣ ውሾቹን አስከትሎ ፣ ቀድሞ ሜጀር ንግግሩን ለማድረግ ቆሞበት ወደ ነበረው ከፍተኛው መድረክ ላይ ወጣ ። የእሑድ ቀን ጉባዔዎች ካሁን ወዲያ የቀሩ መሆናቸውን አስታ ወቀ ። አስፈላጊ ካለመሆናቸውም በላይ ፣ ጊዜ የሚያባክኑ ናቸው አለ ። ለወደፊቱ ፣ የዕርሻውን ቦታ የሚመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ የሚወሰኑት ፣ እርሱ ራሱ በሊቀ መንበርነት በሚመራው ባንድ ልዩ የዐሣሞች ኮሚቴ ይሆናል ። እነዚህም በግል ከተሰበሰቡ በኋላ ፣ ውሳኔዎቻቸውን ለሌሎቹ ያስታውቃሉ ። እንስሳቱ ለሰንደቅ ዓላማው ሰላምታ ለመስጠት ፣ «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» መዝሙርን ለመዘመርና ለተከታዩ ሳምንት ትእዛዞቻቸ ውን ለመቀበል ፣ አሁንም ቢሆን እሑድ እሑድ ጠዋት ይሰበ ሰባሉ ፤ ነገር ግን ፣ ከእንግዲህ ወዲያ የክርክር መድረክ አይደር ም ።

ምንም እንኳን የእስኖቦል መወገድ ያስደነገጣቸው ቢሆ ንም ፣ እንስሳቱ በዚህ መግለጫ አልተደሰቱም ። ብዙዎቹ የመ ከራከር ችሎታ ቢኖራቸው ኖሮ ፣ ተቃውሞዋቸውን ባሰሙ ነበር ። ቦክሰርም ሳይቀር ነገሩ ግልጽ ስላልሆነለት ግር ብሎ ታል ። ዦሮዎቹን ወደ ኋላ አቁሞ ፣ የግንባሩን ፀጉር ደጋግሞ አወዛወዘ ፤ አሳቦቹን ለማሰባሰብ ብርቱ ጥረት አደረገ ፤ ነገር

ግን ፣ በመጨረሻው ምን እንደሚል ጠፋው ። ይሁን እንጂ ፣ ከዐሣማዎቹ አንዳንዶቹ ፣ ይበልጥ የማሳመን ችሎታ ነበራቸው ። በመጀመሪያው ረድፍ ተቀምጠው የነበሩ አራት ትንንሽ ዐሣማዎች በቀጭን ድምፅ ጮኸው ተቃውሞዋቸውን አሰሙና ፣ አራቱም ተነሥተው በመቆም ባንድነት ይንጫጩ ጀመር ። ነገር ግን ፣ በናፖሊዎን ዙሪያ ተቀምጠው የነበሩት ውሾች ድንገት በመጓጉር ድምፅ አስፈራሩዋቸውና ፣ ሀሣማዎቹ ጭጭ ብለው ተመልሰው ተቀመጡ ። ከዚያ በኋላ ፣ በጎቹ «አራት እግሮች ጥሩ ፣ ሁለት እግሮች መጥፎ» የሚለውን ጩኸታቸውን ለቀቁት ፤ እስከ ሩብ ሰዓት ያህል ስላላቋረጡ ፣ ማንኛውም የመከራከር ዕድል እንዲያበቃ አደረጉ ።

ከጊዜ በኋላ ፣ አዲሱን አዘገጃጀት ለሌሎች እንዲያስረዳ እስኩዌለር ተላከ ።

«ጓዶች!» አለ ፣ «ይህን ተጨማሪ ሥራ በመውሰድ ፣ ጓድ ናፖሊዎን ስላደረገው መስዋዕት እያንዳንዳችሁ እንደ ተደሰታችሁ እተማመናለሁ ። ጓዶች ፣ መሪነት አስደሳች ነገር እይምሰላችሁ ! እንዲያውም ፣ ትልቅና ከባድ ኃላፊነት ነው ። እንስሳት ሁሉ እኩል መሆናቸውን ከጓድ ናፖሊዎን የበለጠ የሚያምን የለም ። የራሳችሁን ጉዳዮች በራሳችሁ ውሳኔዎች ብትፈጽሙ እጅግ በተደሰታችሁ ነበር ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የተሳሳቱ ውሳኔዎችን ልታሳልፉ ትችላላችሁ ፣ ጓዶች ፤ ከዚያስ የት እንደርሳለን? አሁን እንደተረዳነው ፣ የዚህን ካንድ ወንጀለኛ የማይሻለውን የእስኖቦልን ፣ የማይረባ የነፉስ ወፍጮ አሳብ ደግፉችሁ ብትወስኑስ ኖሮ?»

«ከብቶች በረት ጦርነት ላይ በጀግንነት ተዋግቷል» አለ አንዱ ።

«ጀግንነት በቂ አይደለም ፤» አለ እስኩዊለር።«የበለጠ ዋጋ ያላቸው ታማኝነትና ታዛዥነት ናቸው ። ስለ በረቱ ጦርነትም ቢሆን፣በዚያ ላይ እስኖቦል የተጫወተው ሚና አለመጠን የተጋነነ መሆኑን የምንረዳበት ጊዜ እንደሚመጣ እምናለሁ ። ሥርዓት ፣ ጓዶች ፤ እንደ ብረት የጠነከረ ሥርዓት! ወቅታዊው መፈክር ይህ ነው ። አንዲት የተሳሳተች ርምጃ ብንወስድ ፣ ጠላቶቻችን በላያችን ላይ ገብ እንደሚሉብን እሙን ነው ። በእርግጥ ፣ ጓዶች ፣ ጆንስ ተመልሶ እንዲመጣ አትፈልጉም አይደል?»

አሁንም እንደ ገና ይህ ትችት መልስ አልነበረውም ። በርግጥ ፣ እንስሳቱ ጆንስ እንዲመለስ አይፈልጉም ፤ የእሑድ ጠዋቶቹ ክርክር መድረኮች ለጆንስ ተመልሶ መምጣት ምክን ያት ከሆኑ ፣ የክርክር መድረኮቹ መቆም አለባቸው ። ነገሩን ለማጤን ጊዜ አግኝቶ የነበረው ቦክሰር ፣ የሁሉንም ስሜት የሚ ገልጸውን አሳብ እንዲህ ሲል ተናገረ ፤ «ጓድ ናፖሌዎን እንዲህ ካለ ፣ ልክ መሆን አለበት» ከዚያም ቀን ጀምሮ ፣ «ናፖሌዎን ምን ጊዜም ልክ ነው» የሚለውን የመመሪያ አሳብ መከተል ጀመረ ፤ ከዚህም በተጨማሪ «በበለጠ ትጋት እሠራለሁ!» የሚል የግሉ የሆነ መፈክር ነበረው ።

በዚህ ጊዜ የአየሩ ጠባይ ሻል ብሎ ፣ የጸደይ ዕርሻ ተጀ ምሮ ነበር ። እስኖቦል የነፋስ ወፍጮ ፕላኖቹን ንድፍ ሥሎበት የነበረው ቤት ተዘግቶ ስለ ነበረ ፣ ፕላኖቹ ከወለሉ ላይ ተደም ስሰው ጠፍተዋል ፣ የሚል እምነት አሳድሮ ነበር ። በየእሑድ ዕለት ጠዋት ፣ በአራት ሰዓት ፣ እንስሳቱ በትልቁ መጋዘን አዳ ራሽ ውስጥ እየተሰበሰቡ የሳምንቱን ትእዛዛቸውን ይቀበሉ ነበር ።

በዚህ ጊዜ ፣ ከሥጋው ሁሉ ተላቆ የነበረው ያሮጌው ሜጀር ራስ ቅል ከመቃብሩ ውስጥ ወጥቶ ፣ ከሰንደቁ ሥር ፣ ከጠመን ጃው ጐን በአንድ የግንድ ጉማጅ ላይ ተቀምጦ ነበር ። ከዓላማው መስቀል ሥነ ሥርዓት በኋላ ፣ እንስሳቱ ወደ መጋዘኑ አዳራሽ ከመግባታቸው በፊት ፣ በራስ ቅሉ ፊት እየሰገዱ በሰልፍ ማለፍ ነበረባቸው ።

ባሁኑ ጊዜ ፣ ቀድሞ ያደርጉት እንደ ነበረው ፣ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ሁሉም ባንድነት አይቀመጡም ። ናፖሌዎን ፣ እስኩዊለርና አንድ ሌላ የመዝሙር ድርሰቶችንና ቅኔዎችን የማቀነባበር ልዩ ተሰጦ ከነበረው ሚኒሙስ ከተባለ ዐሣማ ጋር ፣ በዘጠኙ ቡችሎች ተከበው ፣ ከፍ ብሎ በተሠራው መድረክ ላይ ይቀመጣሉ ፤ ሌሎቹ ዐሣማዎች ደግሞ ከኋላቸው ይቀመጣሉ ። ሌሎቹ እንስሳት ፣ ከፊት ለፊታቸው ፣ በትልቁ መጋዘን ዋናው አዳራሽ ውስጥ ይቀመጣሉ ። ናፖሌዎን ፣ በሸካራ ድምፅና በወታደራዊ ቅላጼ የሳምንቱን ትእዛዞች ያነብና ፣ አንድ ጊዜ ብቻ «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘው መዝሙር ከተዘ መረ በኋላ ፣ እንስሳቱ ሁሉ ይበተናሉ ።

እስኖቦል ከተባረረ በኋላ በዋለው በሦስተኛው እሑድ ዕለት ፣ ከዚያ ሁሉ ሁኔታ በኋላ ፣ የነፋስ ወፍጮ መሥራት ያለ በት መሆኑን ናፖሌዎን ባስታወቀ ጊዜ ፣ እንስሳቱ በመጠኑ ሳይደነቁ አልቀሩም ። ናፖሌዎን ፣ ይህ ተጨማሪ ተግባር እጅግ ከባድ ሥራ መሆኑን ለእንስሳቱ ከማስጠንቀቅ በስተቀር ፣ እሳ ቡን ለምን እንደቀየረ ምክንያት አላቀረበም ።

ምናልባትም ፣ መቁንኖቻቸውንም መቀነስ አስፈላጊ ይሆን ይሆናል ። ይሁን እንጂ ፣ ፕላኖቹ ፣ እስከ መጨረሻይቱ ዝርዝር ሳይቀር ፣ ተጠናቅቀዋል ። ባለፉት ሦስት ሳምንታት ውስጥ አንድ የዐሣማዎች ልዩ ኮሚቴ ፣ ይኸንኑ ሥራ ሲያጠናቅቅ ሰንብቷል ። የነፋስ ወፍጮው ሕንፃ ሥራ ፣ ሌሎቹም የተለያዩ የማሻሻል ተግባሮችን ጨምሮ፣ሁለት ዓመት ጊዜ እንደሚፈጅ ተገምቷል ።

ያን ዕለት ማታ ፣ እስኩዊለር ለሌሎቹ እንስሳት እንዳስረ ዳው ፣«እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ የነፋስ ወፍጮውን ጉዳይ ናፖሌ ዎን በመሠረቱ ተቃውሞ አያውቅም።እንዲያውም፣ ከመጀመሪያ ጀምሮ አሳቡን ያመነጨው እርሱ ራሱ ሲሆን ፣ እስኖቦል በእን ቁላሎች መፈልፈያ ቤት ወለል ላይ የሣለው የፕላኑ ንድፍ ፣ በውነቱ ከናፖሌዎን ሰነዶች መኻል ከተሰረቁ ወረቀቶች የተ ገለበጠ ነው ። የነፋስ ወፍጮው በእርግጥም የናፖሌዎን የፈ ጠራ ሥራ ነው ።»

«ታድያ ፣ ለምንድን ነው ፣ ስለዚህ ጉዳይ ብርቱ የተቃ ውሞ አሳብ ያቀረበው?» ሲል ጠየቀ አንዱ ። ይህን ጊዜ እስኩዊለር ክፉኛ እንደ ተጋለጠ ተሰማው ።

«ይኸማ ፣ ጓዶች» አለ ። «የጓድ ናፖሌዎን ብልጠት ነው ። ለምን መሰላችሁ የተቃወመ የመሰለው? አደገኛና መሠሪ ፍጡር የነበረውን እስኖቦልን ለማስወገድ የተጠቀመበት ዘዴ ብቻ ነው ። አሁን እንግዲህ እርሱ ከተወገደ ዘንድ ፣ ያለ እርሱ ጣልቃ ገብነት ፣ የነፋስ ወፍጮውን ሥራ ማከናወን ይቻላል ። ይህ ፣ ታክቲክ! ይባላል» አለ እስኩዊለር ። ቃሉንም እየደጋ ገመ ፣ «ታክቲክ! ጓዶች ፣ ታክቲክ!» በማለት ፣ ላይ ታች ተን ጐራደደ ፤ ጭራውንም በመቁላት ተንከትክቶ ሣቀ ። ይህ ቃል ምን እንደ ሆነ እንስሳቱ አልገባቸውም ፤ ነገር ግን የእስኩዊለር አነጋገር በጣም አሳማኝ በመሆኑና ከእርሱም ጋራ የነበሩት ሦስት ውሾች በማስፈራራት ድምፅ ስላጉረመረሙ ፣ ያለ ተጨ ማሪ ጥያቄ ገለጻዎቹን ተቀብለው ለማመን ተገደዱ ።

# ስ ድ ስ ት

በዚያ ዓመት ውስጥ በሙሉ ፣ እንስሳቱ እንደ ባሮች ነው የሠሩት ። የሆነ ሆኖ ፣ በሥራቸው ይደሰቱ ነበር ፤ በኋላ ለሚከተሉት መሰሎቻቸው ጥቅም እንጂ ፣ ለጥርቅም ሰነፎችና ሌቦች የሰው ዘሮች ጥቅም እንደማይውል በመገንዘብ ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ ብለው አያጉረመርሙም ነበር ።

በጸደይና በበጋ ወራት በሙሉ ፣ በሣምንት ስድሳ ሰዓቶች ሠሩ ፤ ደግሞ በነሐሴ ወር ውስጥ ፣ እሑድ እሑድ ከቀትር በኋላ ጭምር ሥራ እንደሚኖር ናፖሌዎን አስታወቀ ። ይህ ሥራ በሙሉ ፈቃደኝነት የሚሠራ ነው ፤ ግን ፣ ከዚህ ሥራ የሚቀር እንስሳ ግማሽ መቁነኑ ይቀነስበታል ። ይኸውም ሆኖ ፣ አንዳንድ ሥራዎች ሳይከናወኑ እንዲቀሩ ግድ ሆኖዋል ። ሰብሉ ካምናው ትንሽ ቀንሷል ፤ ደግሞም ለሥራሥር አትክልት ተመድበው የነበሩት ሁለቱ ማሳዎች ጦም አድረዋል ፤ ምክንያቱም ፣ በበጋው ወራት ፣ በወቅቱ ሳይታረሱ በመቅረታቸው ነው ። በመጪው የክረምት ወራት ከባድ ችግር ሊያጋጥም ይችል ይሆናል ።

የነፋስ ወፍጮው ሥራ ያልታሰቡ ችግሮችን አስከተለ ። በዕርሻው ክልል ጥሩ የብሓ ድንጋይ ማውጫ ቦታ ነበር ፤ ባንድ መጋዘን ውስጥ ደግሞ ፣ የተትረፈረፈ አሸዋና ሲሚንቶ ተገኘ ፤ ስለዚህ ለግንባታው ሥራ አስፈላጊ የነበሩት ዕቃዎች ሁሉ በዚያው ተገኙ ። ነገር ግን ፣ በመጀመሪያው ወቅት ፣ እንስሳቱ መፍትሔ ሊያገኙለት ያልቻሉት ችግር ፣ ድንጋዩን አመቺ በሆኑ መጠኖች እንዴት መፍለጥ እንደ ነበረባቸው ነው ። ምክንያቱም ማንኛውም እንስሳ በኋላ እግሮቹ ሊቆም ስለማይችል ፣ ሊሠሩባቸው በማይችሉት ፣ በመራጃዎችና በመሳሰሉት መሣሪያዎች ካልሆነ በስተቀር ፣ ሌላ ዘዴ የነበረ አይመስልም ነበር ። ትክክለኛው ዘዴ ለአንዱ የተከሠተለት ከብዙ ሳምንታት ከንቱ ድካም በኋላ ብቻ ነው ። — ማለትም ፣ በግራቪቲ (ስበት ኃይል) መጠቀም ። እንዳሉ ሊጠቀሙባቸው ያልቻሉት ከመጠን በላይ ትላልቅ ቋጥኞች በድንጋይ ማውጫው ቦታ ተቆልለው ይገኙ ነበር ። በእነዚህ ዙሪያ እንስሳቱ ገመዶችን

ጠመጠሙ ፤ ከዚያም በኋላ ሁሉም ባንድነት ፥ ላሞች ፥ ፈረሶች ፥ በጎችና ፥ ገመዱን ለመያዝ የቻለ ማንኛውም እንስሳ ሁሉ ፥ በጣም አስፈላጊ በነበረበት ወቅት ፥ — ዐሣማዎች እንኳን ሳይቀሩ — በመሳተፍ ፥ ተስፋ በሚያስቆርጥ ቀርፋፋ ዘገሜታ ፥ ከድንጋይ ማውጫው ረባዳ ቦታ ወደ ላይ ጐትተው ካወጡ በኋላ ፥ ወደ ታች ተንከባለው እንዲወድቁ በመልቀቅ ይከሰክሱዋቸዋል ። ከዚህ ድካም አንጻር ሲታይ ፥ የተፈለጡትን ድንጋዮች ወደ ላይ ማጋዙ ቀላል ነበር ማለት ይቻላል ። ፈረሶቹ በጭነት ጋሪ እየሞሉ ያግዛሉ ፤ በጎቹ አንዳንዱን ድንጋይ እየጐተቱ ያወጣሉ ፤ ሙርየልና ቤንጃሚንም ቢሆኑ ፥ ያንዲት አሮጊት አስተማሪ ንብረት በነበረች ጋሪ ሥር ተጠምደው ድርሻ እገዛቸውን አበርክተዋል ። የበጋው ወራት ለማለቅ በተቃረበ ጊዜ ፥ የድንጋይ ክምችት ተሰብስቦ ነበርና ፥ በዐሣማዎቹ ተቆጣጣሪነት የግንባታው ሥራ ተጀመረ ።

ዳሩ ግን ፥ ሥራው አድካሚና ፈቅ የማይል ነበር ። ብዙውን ጊዜ ፥ አንዱን ቋጥኝ ብቻ ጎትቶ ወደ ጫፍ ለማውጣት የአንድ ቀን ሙሉ ልፋት ይጠይቅ ነበር ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፥ ለፍተው ላይ ድረስ አውጥተው ሲለቁት ሳይከሰከስ ይቀራል ። ያለ ቦክሰር አንዳችም ውጤት ባልተገኘ ነበር ። የሌሎቹ እንስሳት ሁሉ ጉልበት ቢሰበሰብ የእርሱን ጉልበት አይወዳደርም ። ቋጥኙ ወደ ታች መንሸራተት ሲጀምርና ፥ እንስሳቱ ሁሉ ገደል ገባን ብለው ሲንጫጩ ፥ ከገመዱ ጋር እየታገለና ቋጥኙን በማቆም ዘወትር የሚያድናቸው ቦክሰር ነበር ። አንዳንድ ስንዝር በጣር እየተራመደ ፥ እያለከለከና ፥ መሬቱን በጥፍሮቹ እየቆነጠጠ ፥ አካሉ ሁሉ በላብ ተጠምቆ ሲታይ ፥ እንስሳቱ ሁሉ ባድናቆት ስሜት ይዋጣሉ ። ክሎቨር አንዳንድ ጊዜ ፥ ከመጠን በላይ ራሱን እንዳያደክም ፥ እንዲጠነቀቅ ትመክረዋለች ፤ ቦክሰር ግን አይሰማትም ። ለችግሮቹ ሁሉ በቂ መልስ መስለው ይታዩት የነበሩት ፥ «በበለጠ በርትቼ እሠራለሁ» እና «ናፖሌዎን ምን ጊዜም ትክክል ነው!» የሚሉት ሁለቱ መፈክሮች ናቸው ። ጠዋት ጠዋት በእኩል ሰዓት ፈንታ ፥ ከሦስት ሩብ ሰዓት አስቀድሞ እንዲቀሰቅሰው ካውራ ዶሮው ጋር ተስማምቶ ነበር ። ባሁኑ ጊዜ እምብዛም ትርፍ ጊዜ ያልነበረው ቢሆንም ፥ በትርፍ ጊዜዎቹ ፥ ብቻውን ወደ ድንጋይ ማውጫው ቦታ ኼዶ

አንድ ሸክም የተፈለጡ ድንጋዮችን ብቻውን ተሸክሞ ወደ ነፋሱ ወፍጮ መሥሪያ ቦታ ይወስዳል ።

በዚያ የበጋ ወራት ውስጥ ፣ ምንም እንኳን ሥራቸው ከባድ የነበረ ቢሆንም ፣ እንስሳቱ ምንም ያህል ችግር አልገጠማቸውም ። በጆንስ ጊዜ ከነበረው ምግብ ይበልጥ ባያገኙም ፣ ያነሰ ግን አልነበረም ። የተሻለው ዕድላቸው ፣ ራሳቸውን ብቻ መመገብ እንጂ አምስት አባካኝ የሰው ልጆችን ጭምር መርዳት አልነበረባቸውምና ፣ ሚዛኑን ሊያጋድሉት የሚችሉት ፣ ብዙ ችግሮች ቢያጋጥሙ ኖሮ ነበር ። ደግሞም በብዙ ረገድ ፣ የእንስሳቱ የሥራ አፈጻጸም ዘዴ ይበልጥ የሠለጠነና ድካምን የሚያቃልል ሆኖ ተገኝቷል ። ለምሳሌ ፣ የአረምን ሥራ የመሳሰሉትን ሥራዎች ፣ የሰው ልጆች ከሚችሉት በላይ በሆነ ጥንቃቄ ሊከናወኑ ችለዋል ። ደግሞ ባሁኑ ጊዜ ማንም እንስሳ አይሰርቅ ስለነበር ፣ የግጦሹን ቦታ ከዕርሻው ቦታ ለይቶ ማጠር አስፈላጊ አልነበረም ፤ ይኸውም ሁኔታ በአጥርና በመዝጊያዎች ጥገና ሥራ ይባክን የነበረውን ድካም ሊያቃልል ችሏል ። ቢሆንም ፣ የበጋው ወራት እየተገባደደ ሲኼድ ፣ የተለያዩ ያልታሰቡ እጥረቶች እየተከሠቱ መጥተዋል ። በዕርሻው ውስጥ ፣ ሊመረቱ የማይችሉ ፣ እንደ ላምባ ፣ ምስማሮች ፣ ሲባጎች ፣ የውሻ ብስኩትና ለፈረሶች ኮቴ ጫማዎች መሥሪያ ብረት የመሳሰሉት አስፈለጉ ። ከጊዜ በኋላ ፣ ከሥራ መሣሪያዎችም በስተቀር ፣ የዘር እህልና የአርቲፊሻል ማዳበሪያ ጭምር ሊያስፈልግ ነው ። በመጨረሻም ፣ ለነፋስ ወፍጮው የሚሆን መኪናዎች ። እነዚህ ሁሉ እንዴት እንደሚገኙ ማንም ሊገምት አልቻለም ።

አንድ ቀን እሑድ ጠዋት ፣ እንስሳቱ ትእዛዞቻቸውን ሊቀበሉ በተሰበሰቡ ጊዜ ፣ ስለ አንድ አዲስ ፖሊሲ (አቅዋም) የወሰነ መሆኑን ናፖሊዮን አስታወቀ ። ከእንግዲህ ወዲያ የእንስሳት ዕርሻ ተቋሙ ከሌሎቹ የጐረቤት ዕርሻ ተቋሞች ጋራ የንግድ ለውውጥ ተግባር ይጀምራል ፤ በእርግጥ ፣ ይኸን ለማድረግ የተነሣው ለንግድ ዓላማ ሳይሆን ፣ አንዳንድ ባስቸኳይ ማግኘት ያለበትን ዕቃዎች ለማግኘት ብቻ ነው ። «የነፋስ ወፍጮው ፍላጐቶች ከማንኛውም ነገር በላይ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ይገባል» አለ ። ስለዚህ አንድ ክምር ድርቆሽና ከዘንድሮው የስንዴ ሰብል ከፊሉን ለመሸጥ እየተስማማ መሆኑንና ፣ ደግሞም

ወደፊት ተጨማሪ ገንዘብ ካስፈለገ ፣ ምን ጊዜም በዊሊንግ ዶን ገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን እንቁላሎች በመሸጥ እንዲሟላ ይደረጋል ፤ በማለት አስረዳቸው ። «ዶሮዎቹ » አለ ናፖሊ ዎን ንግግሩን በመቀጠል ፣ «ይህን መስዋዕትነት በጸጋ ሊቀበሉ ይገባቸዋል ፤ ምክንያቱም ፣ ለነፋስ ወፍጮው ሥራ እነርሱ የሚያበረክቱት ልዩ መዋጮ መሆኑ ነውና ።»

አሁንም እንደ ገና እንስሳቱ ፣ አንድ ግልጽ ያልሆነ የመጨ ነቅ ስሜት አደረባቸው ። ከሰው ልጆች ጋራ ከቶ አንዳችም ነገር አለመዋዋል ፤ አንዳችም የንግድ ሥራ አለመሥራት ፤ ከቶ በገን ዘብ አለመጠቀም ፤ ጆንስ ከተባረረ በኋላ ፣ በዚያ የመጀመሪያው የድል ጉባዔ ላይ ከተላለፉት የመጀመሪያዎቹ ውሳኔዎች ውስጥ እነዚህ ነገሮች አልነበሩም ወይ? እንደዚህ ያሉ ውሳኔዎች ተላል ፈው እንደ ነበረ ፣ እንስሳቱ ሁሉ ያስታውሳሉ ፤ ወይም ፣ ሌላው ቢቀር ፣ የሚያስታውሱ ይመስላቸዋል ።

ናፖሊዎን ጉባዔዎችን በሠረዘ ጊዜ ተቃውመው የነበሩት አራቱ ያማማ ግልገሎች ሲፈሩ ሲቸሩ አሁንም የተቃውሞ ድምፅ አሰሙ ፤ ነገር ግን ፣ ከውሾቹ የተሰነዘረው ኃይለኛ የዛቻ ድምፅ ወዲያው ዝም አሠኛቸው ። ከዚያም ፣ እንደ ተለመደው ፣ በጎቹ «አራት እግሮች ጥሩ ፣ ሁለት እግሮች መጥፎ!» የሚለውን ጩኸ ታቸውን እንባረቁትና ፣ ተፈጥሮ የነበረው ሁከት ለጊዜው ተረ ጋጋ ። በመጨረሻም ፣ ናፖሊዎን ጸጥታውን ለማስከበር አንድ እግሩን አነሣና ፣ ማንኛውንም ዝግጅት ሁሉ ያደራጀ መሆኑን አስታወቀ ። እጅግ የተጠላ ነገር በመሆኑ ፣ ከሰዎች ጋር ማንኛ ቸውም ሌሎቹ እንስሳት እንዲገናኙ አያሻም ። መላውን ሸክም በራሱ ጫንቃ ላይ ለመጫን አስቦ ነው ። አንድ ሚስተር ዊምፐር የተባለ ፣ በዊሊንግዶን የሚኖር የሕግ አማካሪ ፣ በእንስሳት ዕር ሻና በውጭው ዓለም መካከል ስለሚኖሩት ጉዳዮች በአገናኝነት ለመሥራት ተስማምቷል ። እርሱም ትእዛዛቹን ለመቀበል በየ ሳምንቱ ሰኞ ጠዋት ወደ ዕርሻው ቦታ ይመጣል ። ናፖሊዎን ፣ የ«እንስሳት ዕርሻ ይኑር!» የሚለውን የተለመደውን መፈክር ጮኾ በማሰማት ንግግሩን አበቃና ፣ «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘው መዝሙር ከተዘመረ በኋላ እንስሳቱ ተበተኑ ።

ከዚያ በኋላ ፣ እስኩዊለር በዕርሻው ግቢ ውስጥ እየዞረ ጉብኝት በማድረግ ፣ የእንስሳቱን መንፈስ አረጋጋው ። በንግድ ሥራ እንዳይሰማሩና በገንዘብ እንዳይጠቀሙ የሚል ውሳኔ ተላ ልፎ ፣ ወይም እንዲያውም አሳቡ እንኳን ቀርቦ እንደሚያውቅ አረጋገጠላቸው ። ምናልባትም በመጀመሪያው ሰሞን እስኖቦል ከነዛው የፈጠራ ወሬ የመነጨ ሳይሆን አይቀርም ። ከእንስሳቱ አንዳንዶቹ አሁንም ጥርጣሬ አደረባቸው ፤ ነገር ግን ፣ እስኩዊለር በብልጠት እንዲህ ሲል ጠየቃቸው ፤ «ጓዶች ፣ ግን ይህን ነገር በሕልማችሁ ያያችሁት ነገር ላለመሆኑ እርግጠኞች ናችሁ? እንዲህ ያለ ውሳኔ ለመተላለፉ አንዳች የጽሑፍ ማስረጃ አላችሁ? የት ቦታ ነው ተጽፎ የሚገኘው?» ስለመሳሳታቸው እርግጠኞች ስለነበሩ ፣እንስሳቱ አመኑ ።

በስምምነቱ መሠረት ፣ በእየሰኞው ዕለት ጠዋት ሚስተር ዊምፐር ወደ ዕርሻው ቦታ ይመጣል ። ሪዞቹ ወደ ጐንና ጐን የተንጨፈረሩ ፣አታላይ መሳይ ፣ ቁመተ አጭር ሰው ሲሆን ፣ የአነስተኛ ንግድ ሥራዎች አማካሪ ቢሆንም ፣ የእንስሳቱ ዕርሻ አንድ ደላላ የሚሻበት ቀን እንደሚመጣ ፣ ከማንም ሌላ ሰው በፊት የተረዳና ፣ ኮሚሽኑን ለማግኘት ያቀደ ሰው ነው ።

እንስሳቱ ሲመጣና ሲኼድ ይመለከቱት የነበረው በመጨ ነቅ ሁኔታ ሲሆን ፣ በተቻለ መጠን ይሸሹት ነበር ። ሆኖም ፣ ባራቱ እግሮቹ የቆመው ናፖሊዎን ፣ በሁለት እግሮቹ ለቆመው ዊምፐር ትእዛዝ ሲሰጥ ማየቱ ራሱ ፣ ልባቸውን በኩራት የሞላ ውና ከአዲሱ ስምምነት ጋራ በከፊል ያስታርቃቸዋል ። ከሰው ዘር ጋራ የነበሩዋቸው ግንኙነቶች ፣ ቀድሞ ከነበረው አሁን ለየት ያለ ነው ። የእንስሳቱ ዕርሻ አሁን እየበለጸገ በመ ምጣቱ የሰው ልጆች ጥላቻቸውን አልቀነሱም ፤ እንዲያውም ፣ ከመቼውም ይበልጥ ጠሉት ። ዕርሻው ውሎ ሲያድር ኪሣራ እንደሚደርስበት ደግሞም ፣ ከሁሉም ይልቅ ፣ የነፋስ ወፍጮው ሥራ እንደማይሳካ እያንዳንዱ የሰው ልጅ እምነት አድሮበት ነበር ። በየመጠጥ ቤቶች ሲገናኙ ፣ የነፋስ ወፍጮው ግንብ እን ደሚወድቅ ፣ ወይም ቢቆምም እንኳን ፈጽሞ ሊሠራ እንደማይ ችል ፣ አንዱ ላንዱ በሥዕል ያስረዳል ። የሆነ ሆኖ ፣ ወደዱም ጠሉ ፣ እንስሳቱ የግል ጉዳዮቻቸውን ያስተዳድሩበት ለነበረው ጥንቃቄ አክብሮትና አድናቆት እንዲያድርባቸው ተገደዱ ።

ለዚህም አንዱ ምልክት ፣ የእንስሳቱን ዕርሻ «የማኖር ዕርሻ» እያሉ መጥራትን ትተው ፣ «የእንስሳት ዕርሻ» በማለት በራሱ ስም መጥራት መጀመራቸው ነው ። የዕርሻ ቦታውን ከማስመለስ የነበረውን ተስፋ ቆርጦ ፣ ወደ ሌላ ቦታ ኼዶ ይኖር የነበረውን የጆንስንም አሸናፊነት የማዕረግ ስም ጭምር ተውት ። ከዊምፐር ጋር ካልሆነ በስተቀር ፣ አሁንም ቢሆን የእንስሳት ዕርሻና የውጭው ዓለም ግንኙነት አልነበራቸውም ። ነገር ግን ፣ እየተደጋገመ ሲወራ እንደሰማው ፣ ናፖሊዎን ከፎክስውዱ ሚስተር ዊልኪግቶን ፣ ወይም ከፒንችፊልድ ሚስተር ፍሬድሪክ ጋር ቁርጠኛ ፣ የንግድ ስምምነት ያደርጋል ፤— እንደ ታየው ፣ ግን ፣ ባንድ ጊዜ ከሁለቱም ጋር ከቶ ተስማምቶ አያውቅም ።

ዐሣማዎቹ ፣ ድንገት ወደ ዕርሻው ባለቤት መኖሪያ ገብተው መኖሪያቸውን በዚያ ያደረጉት በዚህ ጊዜ ገደማ ነው ። ቀደም ሲል በነበሩት ቀኖች ውስጥ ፣ አንድ ይህን የሚቃረን ውሳኔ ተላልፎ እንደ ነበረ እንስሳቱ እንደ ገና አስታወሱ ፤ እስኩዊለር ደግሞ ይህ እንዳልነበረ ሊያሳምናቸው ችሏል ። የዕርሻው አንጐል የሆኑት ዐሣማዎች ፣ የሚሠሩበት ጸጥታ ባለው ቦታ እንዲኖሩ ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን አስረዳቸው ። ከተራ ያሣማ ጋጣ ይልቅ በቤት ውስጥ መኖር ለመሪውም (ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ናፖሊዎንን «መሪ» በሚል የማዕረግ ስም መጥራት ጀምረዋል) ክብር ጭምር ተገቢ መሆኑን ገለጸላቸው ። ቢሆንም ፣ ዐሣማዎቹ በወጥ ቤቱ ውስጥ መመገብና በእንግዳ ቤቱ ውስጥ መዝናናት ብቻ ሳይሆን ፣ በአልጋዎች ላይ የሚተኙ መሆናቸውን ጭምር በሰሙ ጊዜ ፣ ከእንስሳቱ አንዳንዶቹ ተሸበሩ ። ቦክሰር ፣ እንደተለመደው «ናፖሊዎን ምን ጊዜም ትክክል ነው!» በማለት ነገሩን ችላ ብሎ አለፈው ፤ ክሎቨር ግን ፣ ይህን ያልጋዎችን ነገር የሚቃረን አንድ ደንብ መኖሩ ትዝ ብልዋት ወደ መጋዘኑ ታችኛው ግድግዳ ኼዳ ፣ እዚያ ላይ ተጽፈው የነበሩትን ሰባቱን ትእዛዛት ለማንበብ ሞከረች ። አንዳንዱን ፊደል መቁጠር እንጂ ማንበብ ስላልቻለች ፣ ሙርየልን ፈልጋ አመጣች ።

«ሙርየል ፣ እስቲ አራተኛውን ትእዛዝ አንብቢልኝ ። ባልጋ ላይ መተኛት ፈጽሞ የተከለከለ ነው የሚል ነገር የለበትም?»

ሙርየል እንደ ምንም ተጣጥራ አነበበች ።

«እንዲህ ይነበባል» አለች ። «ማንኛውም እንስሳ አንሶላ በተነጠፈበት አልጋ ላይ መተኛት የለበትም» ይላል አለቻት ።

አንሶላ የሚለውን ቃል ባራተኛው ትእዛዝ መኖሩን አለማ ስታወሷ ክሎቨርን ገረማት ፤ ግን ፣ በግድግዳው ላይ ከተጻፈ ፣ አለ ማለት ነው ። ደግሞ እንዳጋጣሚ በዚያው ወቅት ፣ እስኩዊለር ሦስት ውሾች አስከትሎ በዚያ ሲያልፍ ነበር ፣ ማንኛውንም ጉዳይ አስተካክሎ አስረዳት ።

«ጓዶች ፣ እንግዲህ»፣ አለ ። «ዐሣማዎች አሁን በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ አልጋዎች ላይ እንደሚተኙ ሰምታችኋል ፣ አይደል? እኮ ምን አለበት? አልጋዎችን የሚቃወም ደንብ እንዳልነበረ እርግጠኛነቱን የምጠራጠር ይመስላችኋል? አልጋ ማለት አንድ የመኝታ ቦታ ነው ። በአንድ ጋጣ ውስጥ ያለ የሣር ጉዝጓዝ ፣ በመሠረቱ ስናስበው አልጋ ነው ። ደንቡ የሚቃረነው ፣ የሰው ልጆች ፈጠራ የሆነውን አንሶላን ነው ። ከመኖሪያ ቤቱ አልጋዎች አንሶላዎችን አስወግደን በብርድ ልብሶች መኻል ነው የምንተኛው ። ደግሞስ እንዴት ምቹ አልጋዎች መሰልዋችሁ! ግን ፣ ጓዶች ፣ ልንገራችሁ ፤ በዛሬ ጊዜ ካለብን የአእምሮ ሥራ ጋር ሲነጻጸር ከሚያስፈልገን በላይ ምቹ አይደሉም ። ተግባሮቻችንን ለማከናወን ከመጠን በላይ ድካም እንዲሰማን አትፈልጉም አይደል? ጆንስ ተመልሶ እንዲመጣ የሚፈልግ ፣ በእርግጥ ከእናንተ መኻል ማንም የለም ።

እንስሳቱ ወዲያው በዚህ ጉዳይ ላይ እንዳይጠራጠር አረጋገጡለትና ዐሣማዎቹ በአልጋ ላይ ስለመተኛታቸው ጉዳይ ሁለተኛ ተነሥቶ አያውቅም ።

ደግሞም ከዚያ በኋላ አንድ ቀን ፣ ከእንግዲህ ወዲያ ዐሣማዎቹ ከሌሎቹ እንስሳት ፣ በየጠዋቱ አንድ ሰዓት አርፍደው የሚነሡ መሆኑ በተገለጸ ጊዜ ፣ ስለዚህም ጉዳይ አንዳችም ቅሬታ አልቀረበም ።

በተከታዩ ወራት ፣ እንስሳቱ ድካም የተሰማቸው ቢሆንም ፣ ደስተኞች ነበሩ ። ከባድ ዓመት ነው ያሳለፉት ፤ ከፊሉ ድርቆሽና ጥራጥሬ እህሉ ከተሸጠ በኋላ ፣ ለክረምቱ ወራት ፣ በጐተራ

ውስጥ ይህን ያህል የተቅረፈረፈ ምግብ አልነበረም ፤ ግን የነፋስ ወፍጮው ማንኛውንም ነገር የሚያካክስ ነበር ። በዚህ ጊዜ ግማሽ ያህሉ የግንባታው ሥራ ተገባደደ ።

ከሰብሉ መሰብሰቢያ ጊዜ በኋላ ፣ ብሩህና ብራ ጊዜ ስለተ ከተለ ፣ የነፋስ ወፍጮውን ግንባታ አንድ ክንድ ያህል እንኳ ከፍ ለማድረግ ብንችል ብለው በማሰብ ፣ እንስሳቱ ላይና ታች በመኳተን የተፈለጡ ድንጋዮችን በማጓዝ ከሙቼውም የበለጠ ደከመዋል ። በክሰር ሌሊት ጭምር በመውጣት ፣ አንድ ሁለት ሰዓት በጨረቃ ብርሃን ብቻውን ይሠራል።በትርፍ ጊዜያቸው ፣ እንስሳቱ ይህን መሳይ አስደናቂ ሥራ ለመሥራት በመቻላቸው እየተገረሙ ፣ ግማሽ የግንባታው ሥራ በተጠናቀቀው የነፋስ ወፍጮ ግንብ ዙሪያ በመዞር ፣ ጥንካሬውንና ያወጣጡን ቀጥተ ኛነት ያደንቃሉ ። ምንም እንኳን እንደ ተለመደው ፣ አህዮች ረዥም ዕድሜ ይኖራሉ የሚለውን ምስጢራዊ አነጋገሩን ከማ ሰማት ዐልፎ ፣ እንዳችም ሌላ ነገር የማይወጣው ቢሆንም ፣ ስለ ነፋስ ወፍጮው ጽኑ ምኞት እንዲያድርበት የማይፈልግ ፣ አሮ ጌው ቤንጃሚን ብቻ ነው ።

የደቡብ ምዕራብ ቁጡ ነፋሶችን አስከትሎ ፣ የኅዳር ወር መጣ ። በዚህ ጊዜ ወራቱ አለቅጥ ርጥበት የሚበዛው በመሆኑ ሲሚንቶ ማቡካት ስላልተቻለ ፣ የግንባታውን ሥራ ለማቋረጥ ተገደዱ ።በመጨረሻም ፣ አንድ ኃይለኛ ነፋስ በነፈሰበት ሌሊት፣ በዕርሻው ክልል የነበሩትን ቤቶች ከመሠረታቸው ከማናጋቱም በላይ ፣ የመጋዘኑን ቆርቆሮዎች ከጣራው ላይ እየመነገለ ገፈፋ ቸው ። ዶሮዎቹ ደንግጠው ከእንቅልፋቸው በመንቃት ይንጫጩ ጀመር ፤ ምክንያቱም ፣ ሁሉም በሩቁ አንድ የጠመንጃ ተኩስ ድምፅ እንደ ሰሙ ባንድነት አልመው ነበርና ነው ። ጠዋት እንስሳቱ ከጋጣቸው በወጡ ጊዜ ፣ የባንዲራው መስቀያ ስንደቅ ወድቆ ፣ ደግሞም አንድ ትልቅ ዛፍ ከፍራፍሬ አትክልቱ ቦታ ግርጌ ተገርስሶ አዩ ። ይኸን እንደ ተመለከቱ ፣ የእያንዳንዱ እን ስሳ ጉሮሮ ፣ የተስፋ መቁረጥ አሸባሪ ጩኸት አሰማ ። አንድ አሰ ቃቂ ትርኢት ታያቸው ። የነፋስ ወፍጮው ግንብ ፈርሷል ።

ባንድ ስምምነት ወደ ቦታው ተንደርድረው ወረዱ ። አንዳ ንዴ ካልሆነ በስተቀር ፣ ከርምጃ ጉዞ በላይ ሲንቀሳቀስ ታይቶ

አይታወቅ የነበረው ናፖሌዎን ፣ ከሁላቸውም ቀድሞ ሮጠ ። አዎ ፤ የትግላቸው ሁሉ ፍሬ እዚህ ቦታ ላይ ፈራርሶ ፣ ከመሠረቱ ተፈንግሎ ፣ ያን ያህል ደክመው ፈልጠው ያጓዙዋቸው ድንጋዮች በዙሪያው ተበታትነው ወድቀዋል ። ለጊዜው እንዳችም ነገር መናገር ተስኖዋቸው የተበታተኑትን ድንጋዮች አትኩረው በሀዘን እየተመለከቱ ቆመው ቀሩ ። ናፖሌዎን በዝምታ ላይና ታች እየተንጐራደደ ፣ ዐልፎ ዐልፎ መሬቱን ያሸታል ። ጅራቱ ቀጥ ብሎ ግራና ቀኝ በችኮላ ይወዛወዛል ፤ ይህም የከባድ አእምሮ ሥራ ምልክቱ ነበር ። አንድ ነገር በመወሰን ሁኔታ ድንገት ቆም አለ ።

«ጓዶች» አለ ረጋ ብሎ ። «ለዚህ ሁሉ ነገር ኃላፊው ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ? በሌሊቱ ወቅት መጥቶ የነፋስ ወፍጮ አችንን ያፈረሰው ጠላታችን ማን እንደ ሆነ ታውቃላችሁ? እ.ስ.ኖ፣ቦ.ል.!» ብሎ ድንገት እንደ ብራቅ አንባረቀ ። «ይህን የሠራው እስኖቦል ነው! በፍጹም ክፋት ፣ ዕቅዶቻችን እንዳይሳኩ ለማድረግና በውርደት የተባረረበትን ሁኔታ ለመበቀል ፤ ይህ ከሐዲ በሌሊቱ ጨለማ ተገን ተሾልኮ ገብቶ ፣ አንድ ዓመት ያህል ለፍተን የሠራነውን ሥራ አፈራርሶብናል ። ጓዶች ፣ አሁኑኑና በዚህች ወቅት በእስኖቦል ላይ የሞት ፍርድ ብይን ወስኛለሁ ። ለፍርድ ይዞ ለሚያቀርበው እንስሳ ፣ «የእንስሳ ጀግና» ሁለተኛ ደረጃ ኒሻንና ስድስት ኪሎ ፖም ይሰጣል ። አሥራ ሁለት ኪሎ ፖም ደግሞ ፣ በሕይወት ይዞ ለሚያመጣው!»

እስኖቦልም እንኳን ይህን መሳይ ጥፋት አጥፍቶ በመገኘቱ፣ እንስሳቱ ከመጠን ያለፈ ድንጋጤ ተሰማቸው ። የቁጣ ጩኸት ካሰሙ በኋላ ፣ ምን ጊዜም እስኖቦል ተመልሶ ቢመጣ የሚይዙበትን መንገድ እያንዳንዳቸው ያሰላስሉ ጀመር ። ወዲያው ፣ ካኮረብታው ትንሽ ዕልፍ ብሎ በሚገኘው ሣር ውስጥ ፣ ያንድ ዐሣማ ኮቴ ዱካ ተገኘ ። ለጥቂት ርቀት ብቻ ዱካው ታይቶ ፣ ካንዲት የአጥር ቀዳዳ ሲደርስ ጠፋ ። ናፖሌዎን ጐንበስ ብሎ ባፍንጫው አነፈነፈውና የእስኖቦል መሆኑን አበሠረ ። በእርሱ አስተያየት ፣ ምናልባት እስኖቦል የመጣው ከወደ ፎክስውድ ሳይሆን እንዳልቀረ ገመተ ።

ዱካዎቹ ከተመረመሩ በኋላ ፣ «ከዚህ በላይ ጊዜ አናጥፋ ፣ ጓዶች!» አለ ናፖሊዮን ጮክ ብሎ ። «የምንሠራው ሥራ አለ ። ዛሬውኑ ጥዋት የነፋስ ወፍጮውን መልሰን የመገንባት ሥራችንን እንጀምራለን ፤ በክረምቱ ወራት በሙሉ ፣ በዝናብ ሆነ በበጋ ። እንዲህ በከንቱና ሥራችን ፈርሶ እንደማይቀር ለዚህ ችጋራም ከዳተኛ እናስተምራለን ። ልብ አድርጉ ጓዶች ፣ በፕላኖቹ ላይ አንዳችም ለውጥ መደረግ የለበትም ፤ እንዳሉ ነው የምንሠራቸው ። ወደፊት ፣ ጓዶች! የነፋስ ወፍጮው ይኑር! የእንስሳት ዕርሻ ይኑር!»

# ሰ ባ ት

ክረምቱ የከፋ ነበር ። ውሽንፍሩ በረዶ የቀላቀለ ስለነበረ እስከ የካቲት ወር አጋማሽ ድረስ እንኳ ፣ መሬቱ ላይ የተጋገረው በረዶ ሳይቀልጥ ቆይቷል ። የውጭው ዓለም እንደሚመለከታቸው በማስታወስና ፣ ወፍጮው በወቅቱ ሳያልቅ ቀናተኞቹ የሰው ልጆች እንዳይደሰቱና ፣ ድል አደረግን ብለው እንዳይኩራሩ ለማድረግ ፣ የነፋስ ወፍጮውን መልሶ የመገንባቱን ሥራ ፣ እንስሳቱ እንደ ምንም እየተፍጨረጨሩ ለመጨረስ ሞከሩ ።

በጥላቻ ምክንያት የነፋስ ወፍጮውን ግንብ ያፈረሰው እስኖቦል ነው ፣ የሚለውን ሰበብ ፣ የሰው ልጆች እንዳላመኑ አስመስሎ ፣ ግንቡ ሊወድቅ ያበቃው ግንቦቹ አለመጠን ሳስተው (ቀጥነው) በመሠራታቸው ነው ፣ አሉ ። እንስሳቱ ግን በነገሩ አላመኑም ። ሆኖም ፣ የግንቡ ውፍረት ፣ እንደ በፊቱ አሥራ ስምንት ኢንች በመሆን ፈንታ ፣ ባሁኑ ጊዜ በሦስት ጫማ ውፍረት እንዲሠራ ተወሰነ ፤ ስለዚህ ፣ ከበፊቱ በጣም የበለጠ ብዛት ያለው ድንጋይ ያስፈልጋል ማለት ነው ። እስከ ብዙ ጊዜ ድረስ የድንጋይ ማውጫው ቦታ በግግር በረዶ ክምር ተሞልቶ ቆየና ምንም ሊደረግ አልተቻለም ። ከዚያ በኋላ በተከተለው ብርቱ የብርዱ ወራት ፣ መጠነኛ የሥራ ርምጃ ተካኼደ ፤ ነገር ግን ፣ ርኅራኄ የተለየው ከባድ ሥራ ነበርና ፣ እንስሳቱም እንደ ቀድሞው የተስፋ ስሜት አላሳደረባቸውም ። ሁል ጊዜ በብርድ ከመንሰፍሰፋቸውም በላይ ፣ አዘውትረው ይራቡ ነበር ። ምን

ጊዜም ተስፋ አይቆርጡ የነበሩት ቦክሰርና ክሎቨር ብቻ ናቸው ። አገልግሎት ስለሚያስገኘው ደስታና ስለ ሥራ ክቡርነት እስኩ ዊለር በጣም ጥሩ ንግግሮችን ያሰማል ፤ ነገር ግን ፥ ሌሎቹ እንስሳት የበለጠ የመንፈስ ማነቃቂያ ያገኙ የነበሩት ፥ በቦክሰር ጉልበትና ፥ ምን ጊዜም ሳያሰማው ከማይቀረው፥ «በበለጠ ጥንካሬ እሠራለሁ!» በሚለው መፈክር ነው ።

በጥር ወር ላይ የምግብ እጥረት አጋጠማቸው ። የህል መቁነን በጣም ተቀነሰ ፤ ይኸንኑ ለማካካሻ አንድ ተጨማሪ የድንች መቁነን እንደሚሰጣቸው ተነገረ ። የድንቹ አዝመራ ምርት ከተከማቸበት ቦታ በሚገባ ሳይሸፈን በመቅረቱ ፥ አብዛኛው በውርጩ ተበላሽቶ ተገኘ።ድንቾቹ በስብሰውና መልካቸው ተለውጦ ስለነበሩ ፥ ሊበሉ የሚችሉት ጥቂቶች ብቻ ነበሩ ። እስከ ብዙ ቀኖች እንስሳቱ ከእብቅና ከመሳሰሉት በስተቀር ምንም የሚበሉት ነገር አልነበራቸውም ። ችጋር ዐይኑን አፍጥጦ የመጣባቸው ይመስላል ።

ይህን ሁኔታ ከውጭው ዓለም ሸሽጎ ማቆየት እጅግ አስፈላጊ ነበር ። በነፋስ ወፍጮው ግንብ መፍረስ የልብ ልብ አግኝተው ፥ ስለ እንስሳቱ ዕርሻ ቦታ አዳዲስ የውሸት ወሬዎችን የሰው ልጆች እየነዙ ነበር።«እንስሳቱ ሁሉ በረሀብና በበሽታ እየሞቱ ነው ፤ ደግሞም ያለማቋረጥ እርስ በርሳቸው እየተጣሉና መስሎቻቸውን ወደ መብላትና የወለዱዋቸውን ወደ መግደል እያዘነበሉ ነው» ፥ የሚል ወሬ አሁንም እንደገና መሠራጨት ጀመረ ። እውነተኛው የምግብ እጥረት ሁኔታ የታወቀ እንደሆነ ፥ መጥፎ ውጤቶችን እንደሚያስከትል ናፖሌዎን ደኅና አድርጎ ያውቅ ነበርና ፥ በሚስተር ዊምፐር ተጠቅሞ ፥ ተቃራኒ ወሬ እየነዛ እንዲያስተባብል ለማድረግ ወሰነ ። ይሁን እንጂ ፥ አሁን ፥ ቁጥራቸው አነስ ያለ እንስሳት ፥ አብዛኞቹ በጎች ፥ ተመርጠው ፥ ሚስተር ዊምፐር በሚሰማቸው ጊዜ ፥ የእንስሳት የመቁነን መጠን መጨመሩን እንደ ዋዛ ድንገት እንዲያወሩ ትእዛዝ ተሰጣቸው ።

ከዚህም በተጨማሪ ፥ በእህል መጋዘኑ ውስጥ የሚገኙት ባዶ ሊሆኑ ተቃርባው የነበሩት መከተቻ በርሜሎች ፥ እስከ አፋቸው አካባቢ ድረስ በእብቅ ከተሞሉ በኋላ ፥ በቀረው የጥ

ራጥሬ ወይም ሌላ ምግብ እንዲሸፈኑ ናፖሊዎን አዘዘ ። አንድ አመቺ ምክንያት ተፈጠረና ዊምፐርን እየመሩ በመጋዘኑ ውስጥ እንዲያልፍና በርሚሎቹን በጨረፍታ እንዲያይ ተደረገ ። በዚህ ሁኔታ ተታሎ ፣ በእንስሳት ዕርሻ ቦታ እንዳችም የምግብ እጥረት አለመኖሩን ለውጭው ዓለም ማውራቱን ቀጠለ ።

ሆኖም ፣ በጥር ወር መጨረሻ ገደማ ፣ ከየትም ቢሆን ጥቂት እህል ማግኘት አስፈላጊ እንደነበረ በግልጽ ታየ ። በእነዚህ ቀኖች ውስጥ ፣ ናፖሊዎን ብዙ ጊዜ ውጭ አይታይም ፤ ግን ጊዜውን ሁሉ የሚያሳልፈው ፣ በያንዳንዱ በር ላይ አውሬ መሰል ውሾች ዘብ ቆመው በነበረበት ፣ በመኖሪያው ቤት ውስጥ ነው ። ብቅ በሚልበትም ጊዜ ፣ ዘወትር በክብር ሥነ ሥርዓታዊ ሁኔታ ዙሪያውን በከበቡትና ፣ አለቅጥ በተጠጋው በማንኛውም ጥርሳቸውን እያሳዩ በሚያስፈሩት በስድስት ውሾቹ ታጅቦ ነው ። እሑድ እሑድ ጠዋትም ጭምር አይታይም ፤ ግን ትእዛዞቹን በሌሎቹ ዐሣማዎች ፣ አብዛኛውን ጊዜ በእስኩዌለር አማካይነት ይልካል ። እንቁላሎቻቸውን እንደ ገና መጣል የጀመሩት ዶሮዎች ፣ እንቁላሎቻቸውን ማስረከብ እንዳለባቸው አንድ ቀን ጠዋት እስኩዌለር አስታወቀ ። በዊምፐር አማካይነት ፣ በሳምንት የአራት መቶ እንቁላሎች አንድ ውል ናፖሊዎን ተቀብሏል ። የእነዚህ ዋጋ ፣ የበጋው ወራት እስኪደርስና ሁኔታዎችም ቀለል እስኪሉ ድረስ ፣ የሚበቃ እህልና ምግብ ለመግዛት ያስችላል ።

ዶሮዎቹ ይህን በሰሙ ጊዜ አስደንጋጭ ጩኸት በኅብረት አሰሙ ። ይህ መስዋዕትነት የሚያስፈልግበት ጊዜ ሊመጣ እንደሚችል አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ነበር ፤ ግን ፣ እውነትም ይደረጋል ብለው አላመኑም ነበር ። በጸደይ ወራት ታቅፈው ሊፈለፍሏቸው ያሰቡትን እንቁላሎችን ገና መጣል መጀመራቸው ነበርና ፣ አሁን የእንቁላሎቹ መወሰድ የነፍስ ግዳይ ነው ብለው ተቃወሙ ። ጆንስ ከተባረረ ወዲህ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ፣ ሽፍትነትን የመሰለ ነገር ተፈጠረ ። በሦስት ጥቋቁር የሚኖርካ ዘር ጫጩቶች መሪነት ፣ ዶሮዎቹ የናፖሊዎንን ምኞት ለማሰናከል አንድ ቈራጥ ጥረት አደረጉ ። የተጠቀሙበትም ዘዴ ፣ ወደቤቶቹ ከንቾች ላይ በርረው በመውጣት ፣ ከዚያ ወርደው በወለሉ ላይ ይፈርጡ የነበሩትን እንቁላሎቻቸ

ውን በመጣል ነው ። ናፖሊዎን ፈጣንና የጭካኔ ርምጃ ወሰደ ። የዶሮዎቹ መቁነን እንዲቋረጥ አዘዘ ፤ ደግሞም አንዲት ቅንጣት ጥሬ እንኳን ለአንዲት ዶሮ የሰጠ ማንኛውም እንስሳ በሞት እን ዲቀጣ ደነገገ ። እነዚህን ትእዛዞች የሚያስፈጽሙት ውሾቹ ነበሩ ። ዶሮዎቹ ላምስት ቀኖች ተቋቋሙ ፤ ከዚያ በኋላ ፣ ተመል ሰው በየመውለጃ ካርቶናቸው መጣል ጀመሩ ። በመካከሉ ዘጠኝ ዶሮዎች ሞቱና በፍራፍሬዎቹ ተክሎች መካል ተቀበሩ ፤ የሞ ቱቅም በኮክሲዲሲክ በሽታ ነው ተብሎ ተወራ ። ስለዚህ ጉዳይ ዊምፐር ምንም አልሰማም ፤ እንቁላሎቹንም በሚገባ ይረከባል ፤ በሳምንት አንድ ጊዜ የአንድ ባለግሮሰሪ ፒካፕ እስከ ዕርሻው ግቢ ድረስ እየመጣ ጭኖ ይወስዳል ።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ እስኖቦልን ያየው አልነበረም ። ከጐ ረቤት የዕርሻ ተቋሞች ባንዱ ፣ በፎክስውድ ወይም በፒንችፌ ልድ ተደብቆ ይኖራል ይባላል ። ናፖሊዎን በዚህ ወቅት ከሌሎ ቹ ገበሬዎች ጋራ ከበፊቱ በመጠኑ የተሻለ ስምምነት ነበራቸው። አንድ የጥድ ዛፎች ደን ተቈርጦ በነበረበት ጊዜ ፣ ካሥር ዓመታት በፊት ፣ ተቆልለው የነበሩ የዛፍ ግንዶች ክምር ግቢው ውስጥ ይገኝ ነበር ። በጥሩ ውኔታ ደርቀው የጠነከሩ ግንዶች ነበሩና ዊምፐር እንዲሸጣቸው ናፖሊዎንን መከረው ፤ ሚስተር ዊል ኪንግተንና ሚስተር ፍሬደሪክ ፣ ሁለቱም ሊገዙት ጓጉተዋል ። ናፖሊዎን ከሁለቱ ለየትኛው እንደሚሸጥ መወሰን ተስኖት ያመ ነታ ነበር ። ከፍሬዲሪክ ጋራ ሊስማማ በሚቃረብበት ጊዜ ፣ እስኖቦል ተደብቆ የሚኖረው በፎክስውድ ነው የሚል ወሬ ይሰማል ፤ ደግሞ ወደ ፒክሊንግ ሲያዘነብል ፣ እስኖቦል ያለው በፒንችፌልድ ነው የሚገኘው ይባላል ።

በጸደይ ወራት መጀመሪያ ሰሞን ፣ ድንገት አንድ አሸባሪ ነገር ተከሠተ ። እስኖቦል አዘውትሮ በሌሊት እየተደበቀ ወደ ዕርሻው ቦታ ይመጣል! እንስሳቱ በሥጋት ከመጨነቃቸው ብዛት የተነሣ ፣ በየጋጣቸው ውስጥ እንቅልፍ አልወስድ አላ ቸው ።

እንደሚባለው ፣ በየሌሊቱ ወቅት ጨለማን ተገን አድርጎ ፣ ሹልክ ብሎ እየገባ የማይሠራቸው ደባዎች አልነበሩም ። የስ ንዴውን እህል ይሰርቃል ፤ ወተቱን ይደፋል ፤ እንቁላሎቹን

ይሰብራል ፤ የችግኝ ማፍሊያ መደቦችን ይረመርማል ፤ የፍራ ፍሬ ዛፎችን ቅርፊት ይልጣል ። ማንኛውም ጥፋት ተሠርቶ በተ ገኘ ቁጥር ፣ በእስኖቦል ላይ መላከክ የተለመደ ነገር ሆነ ። አንድ መስታወት ተሰብሮ የተገኘ ፣ ወይም አንድ ቦይ ተደፍኖ የተገኘ እንደሆነ ፣ እንዱ ተነሥቶ ይኽን ያደረገው እስኖቦል ሌሊት ተሾ ልኮ መጥቶ ነው ፣ እንደሚል የተረጋገጠ ነበር ። የመጋዘኑም ቁልፍ የጠፋ እንደ ሆነ ፣ እስኖቦል ከውኃ ጉድጓድ ውስጥ እንደ ጨመረው መላው የዕርሻው ነዋሪ ያምን ነበር ። የሚገርመው ነገር ፣ ጠፍቶ የነበረው ቁልፍ ካንዱ የእህል ጆንያ ውስጥ ከተገኘ በኋላ እንኳን ፣ በዚህ ማመናቸውን ይቀጥሉ እንደ ነበረ ነው ። እስኖቦል በሌሊት ተሾልኮ ጋጣቸው ውስጥ ገብቶ ፣ እንቅልፍ ወስዷቸው እንደ ተኙ ፣ ወተታቸውን እንዳለባቸው ላሞቹ ባንድ ድምፅ ገለጹ ። በዚያ የክረምት ወራት አውከው የነበሩት ዐይ ጦችም ከእስኖቦል ጋራ ዐድመው ነው ተባለ ።

ናፖሊዎን ፣ የእስኖቦል ድርጊቶች በሙሉ መመርመር አለ ባቸው የሚል ደንብ አወጣ ። በውሾቹ ታጅቦ ወጣና ፣ ሌሎቹ እንስሳት ባክብሮት ፈንጠር ብለው እየተከተሉት ፣ በዕርሻው ግቢ እየተዘዋወረ በጥንቃቄ ይመረመር ጀመር ። ጥቂት ርምጃ ዎች በተራመደ ቁጥር ቆም ይልና ፣ እርሱ እንደሚለው ፣ በማሽ ተት ሊለያቸው የሚችለውን ፣ የእስኖቦልን ዱካዎች መሬቱ ላይ ያሸታል ። በመጋዘኑ ውስጥ ፣ በላሞቹ በረት ውስጥ ፣ በዶሮዎቹ ቤቶች ውስጥ ፣ በጓሮ አትክልት ቦታ ፣ በየሥርቻ ሁሉ ፣ ደጋግሞ ያነፈንፍና ፣ በያለበት ለማለት ይቻላል ፣ የእስኖ ቦልን ፈለጎች ያገኛል ። አፍንጫውን መሬት ላይ ተክሎ ደጋ ግሞ በኃይል ያነፈነፍና ባስደንጋጭ ድምፅ «እስኖቦል» እዚህ ቦታ መጥቶ ነበር! ጠረኑን አሽትቼ ዐውቄዋለሁ ብሎ ይጮኽል ። «እስኖቦል» የሚለውን ቃል ሲሰሙ ውሾቹ ሁሉ የሚሰቀጥጥ ድምፅ በማሰማት ፣ የውሻ ክራንቻቸውን ያሳያሉ ።

«ጓዶች!» አለ እስኪዊለር ፣ እንጣጥ በማለት እየተቁነጠ ነጠ። «አንድ ከመጠን በላይ አስደንጋጭ ነገር ተገኝቷል (ተከሥ ቷል)። እስኖቦል ፣ ለፒንችፊልዱ ዕርሻ ባለቤት ፣ ለፍሬዲሪክ ራሱን ሸጠ ፤ ፍሬዲሪክም አሁንም እንኳን ሊያጠቃንና የርሻ ቦታችንን ሊነጥቀን እያሸመቀ ነው! የማጥቃቱ ዘመቻ በሚጀ ምርበት ጊዜ እስኖቦል የእርሱ መሪ ሆኖ ሊመጣ ነው ። ግን ከዚ

ያም የባሰ ነገር አለ ። የእስኖቦል መሸፈት ጉዳይ በከንቱነ ትና በግብዝነት ምክንያት ብቻ ያደረገው መስሎን ነበር ።

ነገር ግን ተሳስተናል ፣ ጓዶች ። እውነተኛው ምክንያት ምን እንደ ነበረ ታውቃላችሁ? ሲጀምር ጀምሮ እስኖቦል የጆንስ ዐድመኛ ነበር! ዕድሜ ልኩን የጆንስ ሰላይ ነበረ ። ትቷቸው በኼደውና ገና አሁን ባገኘናቸው ሰነዶች ነገሩ ሁሉ ተረጋግጦ አል ። በእኔ አስተያየት ፣ ይህ ብዙ ነገር ይገልጽልናል ፣ ጓዶች ። ደግነቱ አልተሳካለትም እንጂ ፣ በከብቶች በረት ጦርነት ጊዜ ፣ እንድንሸነፍና እንድንደመሰስ እንዴት ያለ ሙከራ እንዳደረገ ባይናችን አላየንም ወይ?»

እንስሳቱ ከድንጋጤያቸው ብዛት የተነሣ ፣ ድርቅ ብለው ቀሩ ። እስኖቦል የነፋስ ወፍጮውን ግንብ በማፍረስ ከፈጸመው ከፉ ሥራ ፣ ይህ በጣም የከበደ ነው ። ግን ፣ ነገሩ ሙሉ በሙሉ እስኪዋጥላቸው ድረስ ፣ ጥቂት ደቂቃዎች ወስዶባቸዋል ። በከብቶች በረት ጦርነት ጊዜ እስኖቦል ከእነርሱ ፊት ፊት ምንኛ ተንደርድሮ እንደገጠመ ፣ በየግጥሚያውም ላይ እንዴት እንዳጀገናቸውና እንዳደፋፈራቸው ፣ ደግሞም ፣ የጆንስ ጥይት ጀርባው ላይ ባቈሰለው ጊዜ ፣ አንዳፍታ እንኳን እንዳላረፈ ያስ ታውሳሉ ። ወይም የሚያስታውሱ መሰላቸው ። በመጀመሪያው ላይ ፣ ይህን ነገር የጆንስ ወገን ነው ከሚለው አስተሳሰብ ጋራ ለማጣጣም ጥቂት ተቸገሩ ። ጥያቄዎችን የማቅረብ ልማድ ያል ነበረው ቦክሰር እንኳን ግራ ተጋባ ። የፊት እግሮቹን ኮቴዎች ከሥሩ አጣጥፎ ተኛና ዐይኖቹን ጨፈነ ፤ ከዚያም በብርቱ ጥረት አሳቦቹን ተናገረ ፤

«ይህን አላምንም» አለ ። «በበረት ጦርነት ላይ እስኖቦል በጀግንነት ተዋግቷል ። እኔ ራሴ አይቼዋለሁ ። ወዲያው ፣ ከዚያ በኋላ «የእንስሳት ጀግና» አንደኛ ደረጃ ኒሻን አልሸለምነውም ?»

« የእኛ ስሕተት ነበር ፤ ጓድ ። ምክንያቱም ፣ አሁን እንደታየው ፣ ባገኘናቸው የምስጢር ሰነዶች ላይ ተጽፎ ይገኛል ። እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ ያን ያደረገው እኛን አታሎ ለሞት ሊዳርገን በማሰብ ነበር ።»

«ብቻ እኮ ቈስሏል» አለ ቦክሰር «ደሙን ሲያዘራ ሁላች ንም አይተነዋል ።»

«ያ ከተንኮል ዕቅዱ አንዱ ነው !» ብሎ ጮኸ እስኩዊለር። «የጆንስ ጥይት ጨርፋው ነው የኼደችው ።»

«ማንበብ ብትችል ኖሮ ፣ እርሱ ራሱ በእጁ የጻፈውን ላሳይህ እችል ነበር ። የሤራው ዕቅድ ፣ ባንድ አሥጊ ወቅት እስኖቦል የሽሽት ምልክት ሰጥቶ ለመሸሽና ዕርሻውን ለጠላት ትቶ ለመኼድ ነበር ። ይኸውም ዕቅዱ ሊሳካለት ምንም ያህል አልቀረውም ነበር ፤ —እንዲያውም ልንገራችሁ ፤ ጓዶች ፤ ጀግናው መሪያችን ጓድ ናፖሌዎን ባያድነን ኖሮ ፣ በእርግጥ በተሳካለት ነበር ። ልክ ጆንሰና የእርሱ ሰዎች ወደ ግቢያችን ውስጥ በገቡ ጊዜ ፣ እስኖቦል ድንገት እንዴት ፊቱን አዙሮ ፈርጥጦ እንደ ሸሸና ፣ አንዳንዶቹ እንስሳት እንደተከተሉት አታስታውሱም ? ደግሞስ ፣ በዚያች ሽብርና ፍርሀት በሁሉም ላይ ዐድሮ በነበረበትና ሽንፈት የደረሰብን በመሰለን ወቅት ፣ ጓድ ናፖሌዎን «ሞት ለሰው ልጆች !» ብሎ በመፎከር ተንደርድሮ ኼዶ በጆንስ ቅልጥም ላይ ጥርሶቹን እንዴት እንደተከለ ጭምር አታስታውሱም? እርግጠኛ ነኝ ይኸን ታስታውሳላችሁ !» ብሎ ጮኸ እስኩዊለር ፣ ካንዱ ጐን ወደ ሌላው እየተፈናጠረ ።

በዚህ በተብራራ ሁኔታ አሁን እስኩዊለር በገለጸላቸው ጊዜ ፣ እንስሳቱ የሚያስታውሱት መሰላቸው ። የሆነ ሆኖ ፣ በጦርነቱ የሥጋት ወቅት እስኖቦል መሸሹን አስታውሱ ፤ ቦክሰር ግን ፣ አሁንም በመጠኑ ጭንቀት ይሰማዋል ።

«በመጀመሪያው ጊዜ እስኖቦል ከዳተኛ እንደ ነበረ አላምንም» አለ በመጨረሻ ። «ከዚያ ወዲህ ያደረገው የተለየ ነው ። ነገር ግን ፣ በከብቶች በረት ጦርነት ላይ ጥሩ ጓድ እንደ ነበረ አምናለሁ ።»

«የእኛ መሪ ፣ ጓድ ናፖሌዎን» አለ እስኩዊለር ፤ በጣም ዝግ ብሎና አጠንክሮ በመናገር ። «በማያጠራጥር ሁኔታ እንደ ተናገረው ፣ በማያጠራጥር ሁኔታ ፣ ጓድ ! እስኖቦል ከመጀመሪያ ጀምሮ የጆንስ ሰላይ ነበር — አዎን ፣ ደግሞ ሽፍትነቱ ከመታሰቡ ጊዜ በፊት ጀምሮ ።»

«አ ፤ ይኸ የተለየ ነው !» አለ ቦክሰር ። «ጓድ ናፖሌዎን ይኸን ካለ ፣ ትክክል መሆን አለበት ።»

«ትክክለኛው ሁናቴ ይኸ ነው ፣ ጓድ !» አለ እስኩዊለር ፤ ነገር ግን በእነዚያ ትንንሽ ዐይኖቹ ቦክሰርን እንደ ገላመጠው ታይቷል ።

ሊኼድ ዞር ካለ በኋላ ፣ ቆም ብሎ ፣ ባሳማኝ አነጋገር በመቀጠል ፤ «እዚህ ዕርሻ ክልል ውስጥ ላለ ለያንዳንዱ እንስሳ የማስጠንቀቅው ፣ ዐይኖቹን ከፍቶ በጣም ማስተዋል ያለበት መሆኑን ነው ። ምክንያቱም ፣ በዚህች ወቅት ፣ አንዳንድ የእስኖቦል ሰላዮች በመኻከላችን ያደፈጡ እሉና ነው !»

ካራት ቀኖች በኋላ ፥ በረፋድ ምሽት ሰዓት ፣ እንስሳቱ ሁሉ ባጥር ግቢው እንዲሰበሰቡ ፣ ናፖሌዎን አዘዘ ፤ ሁሉም ባንድነት በተሰበሰቡ ጊዜ ፥ ናፖሌዎን ሁለቱንም ኒሻኖቹን አንጠልጥሎ (ምክንያቱም በቅርብ ጊዜ ፣ «የእንስሳ ጀግና አንደኛ ደረጃ» ኒሻንና «የእንስሳ ጀግና ሁለተኛ ደረጃ» ኒሻኖቹን ለራሱ ሸልሞ ነበር) ። ዘጠኝ ትላልቅ ውሾቹ በዙሪያው እየዘለሉና ፣ እንስሳቱን ሁሉ በፍርሀት በሚያንቀጠቅጥ ሁኔታ እያጓሩ አጅበውት ፣ ከመኖሪያው ቤት ብቅ አለ ። አንድ አሠቃቂ ነገር እንደሚከተል አስቀድመው ያወቁ ይመስል ፣ ሁሉም በያሉበት አቀርቅረው በጸጥታ ቆሙ ፤ ከዚያ በኋላ ፣ በቀጭን ድምፅ ጩኸት አሰማ ። ወዲያው ውሾቹ ወደ ፊት እመር ፣ እመር ብለው ፣ የአራት ዐሣማዎችን ጕሮዎች ነክሰው ፣ በሥቃይና በፍርሀት እያስጮሁ ከናፖሌዎን እግሮች ሥር አቀረቡዋቸው ። የዐሣማዎቹ ጕሮዎች ደሙ፤ ውሾቹ ደም ቀመሱና ለጥቂት ጊዜ እንደ እብደት ቃጣቸው ። ከነዚያ ሦስቱ ፣ ቦክሰር ላይ ሲወረወሩ ፣ ሁሉም ተገረሙ ። ቦክሰር አመጣጣቸውን አየና ትልቁ ኮቴውን አንሥቶ አንዱን ውሻ ካየር ላይ ቀልቦ ከመሬቱ ጋራ አጣበቀው ። ውሻው በመማጠን ሁኔታ ሲጮኽ ፣ ሌሎቹ ሁለቱ ጅራታቸውን ሸጕጠው ሸሹ ። ቦክሰር ፣ « ውሻውን ጨፍልቄ ልግደለው ወይስ ልልቀቀው » በማለት አኳኋን ፣ ናፖሌዎንን ተመለከተ ። የናፖሌዎን ስሜት መለዋወጥ በፊቱ ላይ ታየና ፣ ወዲያው በቁጣ ጮኸ ፣ ቦክሰር ውሻውን እንዲለቀው አዘዘ ። ይኸን ጊዜ ቦክሰር ኮቴውን አነሣና ውሻውም ተገጣጥቦና እያለቀሰ ሹክክ ብሎ ኼደ ።

በዚህ ጊዜ ውካታው ጋብ አለ ። አራቱ ዐሣማዎች ፣ በመ ልካቸው ላይ ሁሉ የጥፋተኝነት ምልክት እየተነበበ ፣ እየተን ቀጠቀጡ ቆመው ይጠብቃሉ ። ናፖሌዎን ጥፋቶቻቸውን እንዲ ናዘዙ አዘዛቸው ። እነዚህ ዐሣማዎች ፣ ናፖሌዎን የእሑድ ጠዋት ጉባዔዎችን በሠረዘ ጊዜ ተቃውሞ አቅርበው የነበሩት ናቸው ። ከተባረረ ጊዜ ጀምሮ ከእስኖቦል ጋራ ግንኙነት እንደ ነበራቸው ፣ የነፋስ ወፍጮውን በማፍረስ ከእርሱ ጋራ የተባበሩ መሆናቸውን፣ ደግሞም ፣ የእንስሳቱን ዕርሻ ለሚስተር ፍሬድሪክ ለማስረከብ ፣ ከእርሱ ጋራ ስምምነት ማድረጋቸውን ፣ ያለ ምንም ተጨማሪ ግፊት ተናዘዙ ። በተጨማሪም እስኖቦል ፣ ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምሮ የጆንስ ሰላይ እንደ ነበረ በምስጢር የነገራቸው መሆኑን ገለጹ ። ኑዛዜያቸውን እንደ ጨረሱ ፣ ውሾቹ ወዲያው አንገታቸውን ተለተሉ ። አረድዋቸው ። ከዚያም ሌላ እንስሳ የሚናዘዘው ነገር እንዳለው ናፖሌዎን ባስፈሪ ድምፅ ጠየቀ ።

በሽፍትነት ሙከራ ጊዜ ፣ የዐድማው መሪዎች የነበሩት ሦስቱ ዶሮዎች አሁን ወደ ፊት ቀረቡና ፣ እስኖቦል በሕልማቸው ታይቶዋቸው እንደ ነበረና ፣ የናፖሌዎንን ትእዛዞች እንዲቃወሙ አነሣሥቶዋቸው እንደ ነበረ ተናገሩ ። እነሱም ጭምር ታረዱ ።

ከዚያ በኋላ ፣ አንዲት ዳክዬ ወደ ፊት ቀረበችና፣ ባለፈው የስ ብል ስብሰባ ጊዜ ፣ስድስት የስንዴ ዘለላዎች ሰርቃ በሌሊት ወቅት የበላች መሆንዋን ተናዘዘች ።

ከዚያ በኋላ ፣ አንዲት በግ በመጠጥ ውኃው ውስጥ የሸናች መሆንዋን ተናዘዘች ፤ ይኸንንም ያደረገችው ፤ እርሷ እንዳለ ችው ፣ እስኖቦል ገፋፍቷት ነው ፣ ሁለቱ ሌሎች በጎች ደግሞ ። አንድ ፣ በተለየ የናፖሌዎን አፍቃሪ ተከታይ የነበረውን አሮጌ በግ ፣ ጉንፋን ይዞት ሳለ ፣ ባንድ የቆሻሻ ቃጠሎ ዙሪያ በማሳደድ የገደሉት መሆናቸውን ተናዘዙ ። ሁለቱም እዚያ ቦታ ላይ ታረዱ ።

የኑዛዜው ትረካና የግድያው ድርጊት በዚህ ሁኔታ ሲቀ ጥል ውሎ ፣ በናፖሌዎን ፊት የሬሳዎቹ ክምር ተቆለለ ፤ ጆንስ ከተባረረ ጊዜ ጀምሮ በዚያ ቦታ ተረስቶ በነበረው የደም ሽታ አየሩ ተበከለ ።

ሁሉም ከተፈጸመ በኋላ ፣ ዐሣማዎቹና ውሾቹ ሲቀሩ ፣ የተረፉት እንስሳት ሹክክ ብለው ባንድነት ተገለሉ ። በፍርሀትና በሀዘን ተዋጡ ። የትኛው እንደሚብስ ግራ ገባቸው — ከእስኖ ቦል ጋራ ያደሙት እንስሳት ክህደት ፣ ወይስ አሁን ባይናቸው

የተመለከቱት የጭካኔ ቅጣት ። በድሮ ጊዜ ፣ ይኸንኑ ያህል የሚዘገንን የደም መፍሰስ ትርኢቶች ብዙ ጊዜ ታይቷል ፤ ግን በእርስ በርሳቸው መኻል አሁን የተፈጸመው ከዚያኛው በጣም የባሰ መስሎ ለሁሉም ታያቸው ። ጆንስ ዕርሻውን ትቶ ከኼደ ጊዜ ጀምሮ ፣ እስከዚች ዕለት ድረስ ፣ አንድም እንስሳ ሌላውን እንስሳ ገድሎ አያውቅም ነበር ። አንዲት ዐይጥ እንኳን አልተገ ደለችም ነበር ። ግማሽ የግንባታ ሥራው አልቆ ወደ ቆመበት ፣ የነፋስ ወፍጮው ይገኝበት ወደ ነበረው ትንሹ ኮረብታ አመሩና እንዲሞቃቸው የፈለጉ ይመስል ፣ ሁሉም ተጠጋግተው ፣ ባንድ ነት ተኙ ፤ ክሎቨር ፣ ሙርየል ፣ ቤንጃሚን ፣ ላሞቹ ፣ በጎቹ ፣ የዳክ የዎቹና የዶሮዎቹ መንጎች በሙሉ ፣ ናፖሌዎን እንስሳቱ እንዲሰ በሰቡ ከማዘዙ በፊት ፣ ድንገት ተሠውራ ከነበረችው ከድመቲቱ በስተቀር ፣ ዐልፎ ዐልፎ የመገረም ህምህምታ በቀጭን ድምፅ እያሰማ ፣ ከወዲያ ወዲህ ይንቆራጠጣል ። በመጨረሻ እንዲህ አለ ፤

«ነገሩ አይገባኝም ። እንደዚህ ያሉ ነገሮች በእኛ ዕርሻ ውስጥ ይደርሳሉ ብዬ ባላመንኩ ነበር ። ከእኛው ከራሳችን በተ ፈጠረ እንዳች ስህተት ምክንያት መሆን አለበት ።

«እኔ እንደሚታየኝ ፣ መፍትሔው በበለጠ ጥረት መሥራት ነው ። ከእንግዲህ ወዲያ ፣ በየጠዋቱ አንድ ሙሉ ሰዓት አስቀ ድሜ እነሣለሁ ።»

በሥግሪያ ኮቴውን እያስጮኸ ወደ ድንጋይ ማውጫው አመራ ። ሁለት ተከታታይ የድንጋይ ጭነቶችን ሰብስቦ ፣ ወደ መኝታው ከመኼዱ በፊት ፣ ወደ ነፋስ ወፍጮው ቦታ ጐትቶ አደረሳቸው ።

እንስሳቱ በክሎቨር ዙሪያ ተጠጋግተው በጸጥታ ተኝተዋል ። የተኙበት ኮረብታ ባሻገሩ ያለውን ገጠር በሰፊው ያሳያል ። አብዛኛው የእንስሳቱ ዕርሻ ክልል — እስከ ዋናው ጐዳና የተንጣ ለለው ረዥም የግጦሽ ቦታ ፣ የድርቆሽ ሣሩ ሜዳ፣ደኑ ፣ የመጠጥ ውኃው ኩሬ፣የስንዴ ዘሩ አረንጓዴ ቡቃያ እጅብ ብሎ የበቀለበት፣ የታረሰው መሬትና ፣ ከየጭስ መውጫው ጭስ የሚያምቧልሉት

የርሻው ክልል ቤቶች ቀያይ ጣራዎች ወሊል ብለው ይታዩዋቸ ዋል ። ብሩህ የጸደይ ወራት ምሽት ነበረ ። ሣሩና ያበቡት ቁጥቋ ጦዎች ፣ አግድም በተፈነጠቁት የፀሐይ ጮራዎች ወርቅማ ውበት ተጐናጽፈዋል ። የዕርሻው ቦታ ከመቼውም ይልቅ ፣ ደግሞም እያንዳንዱ ስንዝር መሬት የገዛ ራሳቸው ንብረት መሆ ኑን በመደነቅ አኳኋን አስታወሱ ፤ እንዴት ያለ የሚያጓጓ ቦታ መስሎ ለእንስሳቱ ታያቸው ። ክሎቨር ከኮረብታው ቁልቁል ስትመለከት ፣ ዐይኖችዋ እንባ አቀረሩ ። አሳቦችዋን በቃላት ለመግለጽ ብትችል ኖሮ ፣ እንዲህ ባለች ነበር ፤ ከብዙ ዓመታት በፊት የሰውን ልጅ ለመገልበጥ በተነሣሡበት ጊዜ ዐልመውት የነበረው ይኸን አልነበረም ። አሮጌው ሜጀር ለሽፍትነቱ የማ ነሣሻ ንግግር ባደረገላቸው ዕለት ማታ ፣ ተመኝተውት የነበረው ይኸን መሳዮቹን የፍርሀትና የእልቂት ትርኢቶችን አልነበረም ። እርሷ ራስዋ ስለ መጪው ጊዜ የነበራት ሥዕል ቢኖር ፣ ከረሀብና ካለንጋ ነጻ የሆነ ፣ ሁሉም እኩል የሆኑበት ፣ እያንዳንዱ እንደ ችሎታው የሚሠራበት ፤ በሜጀር ንግግር ምሽት እርሷ ራስዋ የባዘኑትን ዳክዬዎች በፊት እግሮችዋ እንደ መከተችላቸው ሁሉ ፣ ጉልበተኛው ለደካማው መከታ የሚሆንበት የእንስሳት ማኅበር ነበር ። በምትኩ ፣ ለምን እንደሆነ ቢታውቀውም ማንም አሳቡን ለመግለጽ ከማይችልበት ጊዜ ፣ አውሬዎች የሆኑ ፣ ሲያጓሩ የሚያስፈሩ ውሾች በያለበት የሚዘዋወሩበት ጊዜና የሚዘገንኑ ወንጀሎቻቸውን ዘክዝከው ከተናዘዙ በኋላ ፣ ጓዶች ተዘነጣጥለው ከሚጣሉበት ጊዜ ደርስዋል ። የሽፍትነትም ሆነ የትእዛዝ መጣስ አሳብ አልነበራትም ። ይህም ሁሉ ሆኖ ፣ በጆንስ ጊዜ ከነበረው ኑሮዋቸው በጣም የተሻለ እንደሆነ ታውቃለች ። ደግሞም ፣ ከሌላው ሁሉ አስቀድሞ የሰው ልጆች መመለስ ሁኔታ መከላከል ያስፈልጋል ። የመጣው ቢመጣ በታማኝነትዋ ጸንታ ፣ በበለጠ ትጋት በመሥራት ፣ የሚሰጣትን ትእዛዞች እየ ፈጸመችና የናፖሌዎንን መሪነት ተቀብላ ትቆያለች ። ግን ግና ፣ እርሷም ሆነች ሌሎቹ እንስሳት ሁሉ የተመኙትና የደከሙት ለዚህ አልነበረም ።

የነፋስ ወፍጮውን የሠሩትና ከጆንስ ጥይቶች ጋራ የተጋ ፈጡት ለዚህ አልነበረም ። ምንም እንኳን አሳብዋን የምትገል ጽባቸው ቃላት ቢያጥራት ፣ አሳቦችዋ ይኸን መሳይ ነበሩ ።

በመጨረሻም ፣ ልታገኛቸው ለተሳናት ቃላቶቿ ይዝ ማካካሻ ቢሆንልኝ በሚል ስሜት «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘውን መዝሙር መዘመር ጀመረች ። በዙሪያዋ ተኝተው የነበሩት ሌሎች እንስሳትም አብረዋት በመዘመር ፣ ሦስት ጊዜ ደጋግመው በጣም ጥዑም አድርገው ፣ ግን በዝግታና በሀዘን ስሜት ፣ ከዚያ በፊት ዘምረውት በማያውቁት ሁኔታ ዘመሩት ።

ልክ ሦስተኛውን ጊዜ ዘምረው እንደ ጨረሱ ፣ እስኩዊለር አንድ ብርቱ ጉዳይ ሊነግራቸው እንደመጣ በሚመስል ሁኔታ ፣ በሁለት ውሾች ታጅቦ ፣ ቀረባቸው ። ጓድ ናፖሌዎን ባወጡት ልዩ ድንጋጌ ፤ «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘው መዝሙር የተሠረዘ መሆኑን አስታወቃቸው ። ካሁን ወዲያ ይህን መዝሙር መዘመር ተከልክሏል ።

እንስሳቱ ተደነቁ ።

«ለምን ?» ጠየቀ ሙርየል ።

«ከእንግዲህ ወዲያ የሚያስፈልግ አይደለም ፣ ጓዶች» አለ እስኩዊለር ፤ ፍርጥም ብሎ ። «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘው መዝሙር የሽፍትነቱ ወቅት መዝሙር ነበር ። አሁን ግን ሽፍትነቱም ተፈጽሟል ። ዛሬ በከሀዲዎች ላይ የተወሰደው የቅጣት ርምጃ የመጨረሻው ድርጊት ነው ። የውጭውም ሆነ የውስጥ ጠላት ተሸንፎዋል ። ወደፊት በሚመጡት ቀናት የተሻለ ማኅበር እንዲኖር የነበረንን ናፍቆት «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» በተሠኘው መዝሙር ገልጸናል ። ግን ያ ማኅበር አሁን ተቋቁሟል ። ይህ መዝሙር ከእንግዲህ ወዲያ አንዳችም ዓላማ የሌለው መሆኑ ግልጽ ነው ።»

ምንም እንኳን ፍርሀት ዐድሮባቸው የነበሩ ቢሆንም ፣ አንዳንዶቹ እንስሳት ምናልባት ተቃውሞዋቸውን ባሰሙ ነበር። ግን ፣ በዚህ ወቅት ፣ በጎቹ ያን የተለመደውን «አራት እግሮች ጥሩ ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ» የሚለውን ጩኸታቸውን ጀመሩና ፣ ለብዙ ደቂቃዎች ባለማቋረጣቸው ክርክሩ እንዲያበቃ አደረገው ።

ስለዚህ ፣ ከዚያ በኋላ ፣ «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘ መዝሙር ተሰምቶ አያውቅም ።

በዚያ ፊንታ ሚኒሙስ የተባለው ባለቅኔ ፥ ሌላ መዝሙር አውጥቶ ነበር ፤ ይኸውም እንዲህ ሲል ይጀምራል ፤

«የእንስሳት ዕርሻ ፤ የእንስሳት ዕርሻችን ፤

«ጉዳት ላይደርስብሽ ይፈሳል ደማችን !»

ይኸውም ፥ ከባንዲራው መስቀል ሥርዓት በኋላ ፥ በየእሑድ ጠዋት ይዘመር ነበር ። ነገር ግን ፥ ቃላቱም ሆኑ ጣዕመ ዜማው «የእንግሊዝ ንስሳት ሆይ» እንደ ተሠኘው መዝሙር ለእንስሳቱ የሚጥም ሆኖ አልተገኘም ።

## ስ ም ን ት

ከጥቂት ቀኖች በኋላ ፥ የሞት ርምጃው አሳድሮባቸው የነበረው የፍርሀት ስሜት ጋብ ባለ ጊዜ ፥ «ማንኛውም እንስሳ ማንኛውንም ሌላ እንስሳ መግደል የለበትም» የሚል ድንጋጌ በሰባቱ ትእዛዛት ፥ በስድስተኛው ቁጥር መኖሩን ከእንስሳቱ አንዳንዶቹ አስታወሱ ፤ ወይም የሚያስታውሱ መሰላቸው ። ምንም እንኳን በዐሣማዎቹ ፥ ወይም በውሾቹ ፊት ሊያነሣው የሚወድ (የሚደፍር) ማንም ያልነበረ ቢሆንም ፥ የተፈጸመው የግድያ ተግባር ከዚህ ጋር የሚጣጣም መስሎ አልታያቸውም ። ስድስተኛውን ትእዛዝ ቤንጃሚን እንዲያነብላት ክሎቨር ብትጠይቀው ፥ ቤንጃሚን እንደተለመደው ፥ በእንደዚህ ያሉት ጉዳዮች ውስጥ ጥልቅ ማለት የማይወድ መሆኑን ስለገለጸላት ፥ ሙርየልን ፈለገችና ሙርየል ስድስተኛውን ትእዛዝ አነበበላት ። እንዲህ ይላል ፥ «ማንኛውም እንስሳ ማንኛውንም ሌላ እንስሳ መግደል የለበትም—ያለ ምክንያት» እንዴት እንደ ሆነ እንጃ እንጂ ፤የመጨረሻዎቹ ሁለት ቃላት ከእንስሳቱ አእምሮ ጠፍቷል ። ግን አሁን ፥ ትእዛዙ አለመጣሱን ተረዱ ፤ ምክንያቱም ፥ ከእስኖቦል ጋራ ዐድመው የነበሩትን ከሀዲዎች ለመግደል በቂ ምክንያት እንደ ነበረ ግልጽ ነውና ነው ።

በዓመቱ ውስጥ በሙሉ ፥ እንስሳቱ ባለፈው ዓመት ከሠሩት በበለጠ ድካም ጥረው ሠርተዋል ። ከቀድሞው እጥፍ ውፍ

ረት የነበራቸውን የነፋስ ወፍጮውን ግንቦች መልሶ ለመሥራትና በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ለመጨረስ — ከመደበኛው የርሻ ሥራ ጭምር — ከባድና አስደናቂ ሥራ ነበር ። አንዳንድ ጊዜ ለእንስሳቱ እንደ መሰላቸው ፣ ከጆንስ ጊዜም ለበለጡ ሰዓቶች የሚሠሩ መሆናቸውና የሚያገኙትም ምግብ ከዚያን ጊዜ የተሻለ እንዳልነበረ ነው ። በየእሑድ ጠዋት ፣ እስኩዊለር አንድ ረዥም ዝርዝር የተጻፈበትን ወረቀት በኮቴው ረግጦ ይዞ ፣ እያንዳንዱ ዓይነት የምግብ እህል ምርት ፤ በሁለት መቶ ከመቶ ፣ በሦስት መቶ ከመቶ ፤ ወይም እንደ ነገሩ ሁኔታ ፣ ባምስት መቶ ከመቶ እጅ ያደገ መሆኑን ያነብላቸዋል ። እንስሳቱ የማያምኑበት አንዳችም ምክንያት አልነበራቸውም ፤ በተለይም ፣ ከሽፍትነቱ በፊት የነበሩት ሁኔታዎች እንዴት እንደ ነበሩ በጣም ግልጽ ሆኖ ስለማ ይታወሳቸው ነበር ። የሆነ ሆኖ ፣ የቁጥሮቹ ጋጋታ ቀርቶ የበለጠ ምግብ ቢያገኙ እንደሚሻላቸው ተረድተውታል ።

ባሁኑ ጊዜ ትእዛዞቹ ሁሉ የሚተላለፉት በእስኩዊለር ፣ ወይም ካሣማዎቹ ባንዱ አማካይነት ሆነዋል ። ናፖሌዎን ራሱ ባሥራ አምስት ቀኖች ውስጥ ካንድ ጊዜ በላይ በአደባባይ የማ ይታይበት ወቅት ነበር ። ብቅ በሚልበትም ጊዜ የሚከተሉት አጃቢዎቹ ውሾቹ ብቻ አልነበሩም ፤ ፊት ፊቱ የሚጓዝና ፣ ናፖ ሌዎን ንግግር ከማድረጉ በፊት ኩኩሉ—ኩ ! በማለት እንደ አንድ ጥሩምበኛ የሚያገለግል አንድ ጥቁር አውራ ዶሮ ነበር ።

በመኖሪያ ቤቱም ውስጥ ቢሆን ፣ ናፖሌዎን የሚኖረው ከሌሎቹ በተለዩ አፓርታማዎች ውስጥ ነው ይባላል ። ምግቡንም የሚበላው በሁለት ውሾች አሳላፊነት ሲሆን ፣ የሚበላበት አንድ «ክራውን ደርቢ» የሚባል ከባለ መስታወቱ የምግብ ቤት ቁም ሣጥን ውስጥ የተገኘ ልዩ ሰሐን ነበረው ። ደግሞም እንደ ተነገረው ፣ በሌሎቹ ሁለት የክብረ በዓሎች ቀን ብቻ ሳይ ሆን ፣ ጠመንጃው በየዓመቱ ለናፖሌዎን የልደት ቀንም እንዲተ ኮስ መግለጫ ተሰጥቷል ።

ባሁኑ ጊዜ ፣ ናፖሌዎን የሚጠራው በስሙ ብቻ መሆኑ ቀርቷል ፤ ምን ጊዜም እርሱ የሚጠቀሰው ፣ የሥነ ሥርዓትን መንገድ በተከተለ ፣ «መሪያችን ፣ ጓድ ናፖሌዎን» በማለት ነው ። ዐሣማዎቹ ደግሞ ለእርሱ የሚያወጡለት ስም ፣ «የእንስሶች ሁሉ

አባት ፡ የሰው ዘር አስደንጋጭ» እና የመሳሰሉትን የማዕረግ ስሞች ነው ። በንግግሮቹ ወቅት ፡ እስኩዊለር ስለ ናፖሌዎን ብልኅነት ፡ ስለ እርሱ ልበ ሩኅሩኅነትና በየትም ቦታ ለሚገኙት እንስሳት ሁሉ ፡ በተለይም በሌሎቹ ዕርሻ ተቋሞች ውስጥ ፡ በድንቁርናና በባርነት ለሚኖሩት ያልታደሉት እንስሳት ሳይቀር ስላለው ፍቅር ባነሣ ቁጥር ፡ እንባው በጉንጮቹ ላይ ሲኰል ይታያል ። ማንኛውንም መልካም ውጤትና መልካም ዕድል ሁሉ ናፖሌዎን እንዳስገኘው መቁጠር የተለመደ ሆኖዋል ። እንድዋ ዶሮ ለሌላዋ ፡ «በመሪያችን ፡ በጓድ ናፖሌዎን አመራር በስድስት ቀኖች ውስጥ አምስት እንቁላሎችን ለመውለድ በቃሁ» ፤ ብላ ስትናገር ብዙ ጊዜ ይሰማል ፤ ወይም ሁለት ላሞች የኩሬውን ውኃ እየጠጡ ሲደሰቱ ሳሉ ፤ «የጓድ ናፖሌዎን አመራር ምስጋና ይግባውና ፡ ይህ ውኃ ምንኛ ይጣፍጣል !» ብለው ይደነቃሉ ። ከዚህ ቀጥሎ እንደሚነበበው ፡ «ጓድ ናፖሌዎን» በሚል አርእስት ፡ ከሚኒሙስ የተደረሰው ግጥም ፡ በዕርሻው ውስጥ የነበረውን ስሜት ባጠቃላይ የሚገልጽ ነው ፤

ያባት አልባዎች ወዳጅ ሆይ !
የደስታችን ምንጭ ሆይ !
የማዕዳችን ጌታ ሆይ !
እንደ እሳት ነፍሴ ትግል የለም ወይ!
ገራምና አዛኞች ዐይኖችህ ሲታይ!
እንደምታበራ ብሩህዋ ፀሐይ!
አ ፡ ጓድ ናፖሌዎን ሆይ !
እኛ ፍጡሮችህ የምንወደውን ፤
በቀን ሁለተዜ ሞልተን ሆዳችንን ፤
እንመገባለን በጣም ተደስተን ፤
ንጹህ ገለባ ላይ እንተኛለን ዐርፈን ።

ትንሹ ትልቁ እንስሳት በሙሉ ፤
በጋጣቸው ገብተው በሰላም ያርፋሉ ፤
ጥበቃህ ለሁሉም ይዳረስ የለም ወይ !
አ ፡ ጓድ መሪያችን ናፖሌዎን ሆይ !

ግልገል በነበረኝ ገና የሚጠባ ጡት ፤
በጨቅላነት ጊዜው ከማደጉ በፊት ፤

ታማኝ ላንተ እንዲሆን እኔ ባስተማርሁት ፤
እቶንም ሲፈታ እንዲል ባሠኘሁት ፤
«ጓድ ናፖሌዎን» !

ይህን ግጥም ናፖሌዎን አጸደቀውና ከሰባቱ ትእዛዛት ትይዩ ባለው ፥ በትልቁ መጋዘን መጨረሻው ግድግዳ ላይ እንዲጻፍ አደረገ ። ከበላዩ ፥ እስኩዊለር በነጭ ቀለም የሣለው የናፖሌዎን ምስል ተሰቀለ ።

በዚሁም መካከል ፥ በዊምፐር ወኪልነት ናፖሌዎን ፥ ከፍሬድሪክና ከፒልኪንግተን ጋራ ፥ የተወሳሰቡ ድርድሮችን እያደረገ ነበር ። የማንቃዎቹ ክምር ገና አልተሸጠም ። ከሁለቱ ይበልጥ ጉጉት ያደረበት ፍሬድሪክ ነው ፤ ነገር ግን ፥ ተገቢውን ዋጋ አልሰጥ አለ ። በዚሁ ጊዜም ፥ የነፋስ ወፍጮው መሠራት አስ ቆጪ ቅናት አሳድሮበት ስለነበረ ፥ ፍሬዲሪክና የእርሱ ሠራተ ኞች የእንስሳት ዕርሻን አጥቅተው የነፋስ ወፍጮውን ግንብ ለማፈራረስ እንደሚያሤሩ አዲስ ጭምጭምታ ተሰማ ። እስና ቦል አሁንም በፒንችፊልድ ዕርሻ እንዳደባ መኖሩ ይታወቃል ። በበጋው ወራት አጋማሽ ላይ ፥ ሦስት ዶሮዎች ቀርበው ፥ በእስ ኖቦል አነሣሽነት ፥ ናፖሌዎንን ለመግደል መሸመቃቸውን ተና ዝዘዋል የሚል ወሬ ስለሰሙ እንስሳቱ ደነገጡ ። ወዲያው ዶሮ ዎቹ በሞት ተቀጡና ፥ ለናፖሌዎን ደኅንነት ተጨማሪ የጥንቃቄ ርምጃዎች እንዲወሰዱ ተደረገ ። ሌሊት ሌሊት አራት ውሾች ባልጋው ዙሪያ ፥ በየጠርዙ አንዳንድ ዘብ እንዲቆሙ ተደረገ ። ምግቡን ሁሉ ከመብላቱ አስቀድሞ ፥ ተመርዞ እንዳይሆን ለማ ረጋገጥ ፥ አንዲት ፒንኬይ የምትባል ልጅግር ዐሣማ እንድትቀ ምስ ታዘዘችለት ።

በዚያው ሰሞን ገደማ ፥ ናፖሌዎን የማንቃውን ክምችት ለሚስተር ፒልኪንግተን ሊሸጥ የተስማማ መሆኑ ተወራ ፤ ደግ ሞም በእንስሳት ዕርሻና በፎክስውድ መካከል አንዳንድ ምር ቶችን ለመለዋወጥ አንድ ቋሚ ስምምነት ጭምር ሊያደርግ ነው ። በናፖሌዎንና በፒልኪንግተን መካከል የነበሩት ግንኙነቶች ይካኼዱ የነበሩት በዊምፐር አማካይነት ቢሆንም ፥ ባሁኑ ጊዜ ወደ ወዳጅነት የተቃረቡ ነበሩ ። እንስሳቱ ፒልኪንግተንን በሰው ልጅነቱ አያምኑትም ነበር ፤ ነገር ግን ፥ ይፈሩትና ይጠ

ሉት ከነበረው ከፍሬዲሪክ እጅግ አብልጠው ይመርጡታል ። የበጋው ወራት እየተገባደደና የነፋስ ወፍጮውም ሥራ እየተ ጠናቀቀ ሲኼድ ፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንድ የጥቃት ጦርነት እንደሚካኼድባቸው የተነዛው ወሬ እየተባባሰ መጣ ።

ፍሬድሪክ ፣ ሁሉም ጠመንጃ የያዙ ፣ ሀያ ሰዎችን አስከትሎ ሊመጣባቸው እንደሚያስብና ፣ የእንስሳትን ዕርሻ ባለቤትነት ሰነድ በእጁ ካገባ በኋላ ፣ እንዳችም ጥያቄ እንዳይቀርብበት፣ለዳኞቹና ለፖሊስ ገና ድሮ ጉቦ የሰጠ መሆኑ ተወራ ። ከዚህም በላይ ፣ ፍሬዲሪክ በራሱ እንስሳት ላይ ስለሚፈጽማቸው የጭካኔ ተግባሮች በጣም የሚያስደነግጡ ታሪኮች ከፒንችፊልድ በኩል ተነዙ ። አንድ ያረጀ ፈረስ ገርፎ ገደለ ፤ ላሞቹን በችጋር ገደለ ፤ አንዱን ውሻ እቶን ውስጥ ጥሎ ገደለ ፤ በጥፍሮቻቸው ላይ የምላጭ ስብርባሪዎችን አሥሮ ፣ አውራ ዶሮዎችን በማናከስ ማታ ማታ ራሱን ያስደስታል ። በጓዶቻቸው ላይ እነዚህ ነገሮች መፈጸማቸውን ሲሰሙ ፣ የፒንችፊልድን ዕርሻ ለመውጋትና የሰው ልጆችን አባረው እንስሳቱን ነጻ ለመውጣት እንዲፈቅድላቸው ይጮኹሉ ። እስኩዊለር ግን ከችኩልነት ተግባሮች እንዲቆጠቡና በጓድ ናፖሌዎን የጦር ስልት ላይ እምነታቸውን እንዲጥሉ ይመክራቸዋል ።

ቢሆንም ፣ በፍሬዲሪክ ላይ የነበራቸው ጥላቻ እየተባባሰ ኼደ። አንድ እሑድ ዕለት ጠዋት ፣ ናፖሌዎን በመጋዘኑ ዐዳራሽ ውስጥ ተገኝና የጣንቃውን ክምችት ለፍሬዲሪክ ለመሸጥ አንዳችም ጊዜ እንዳላሰበ ገለጸ ፤ «እንደ እርሱ ካሉት ጠማማዎች ጋራ የንግድ ውለታ መዋዋል ነ ብርን እንደማዋረድ የሚቆጠር ነው ፣» አለ ። ስካሁንም ገና የሽፍትነቱን ወሬ በማሠራጨት ላይ ይሰማሩ የነበሩት ርግቦች ፎክስውድ ውስጥ የትም ቦታ እግራቸው እንዳያርፍ ተከለከሉ ፤ ደግሞም «ሞት ለሰው ዘር» የሚለውን የቀድሞውን መፈክር ትተው ፣ «ሞት ለፍሬዲሪክ» በሚል እንዲተኩት ታዘዙ ። በበጋ ወራት ማለቂያ ሰሞን ፣ ደግሞ ሌላ የእስኖቦል ተንኮል ድርጊት ተጋለጠ ። የስንዴው ሰብል በአረም ተዋጠና ፣ በስንዴው ዘር ውስጥ እስኖቦል ፣ በተለመደው የሌሊት ዙረቶቹ ባንዱ ቀን ፣ ያረም ዘር ደባልቆበት ተገኘ ።

የሚራውም ምስጢር ተካፋይ ሆኖ የነበረው አንድ አውራ ዳክዬ ፣ ጥፋቱን ለእስኩዊለር ተናዞ ፣ ወዲያው መርዛም የአን

ጆሪ ፍሬዎች ውጦ ራሱን ገደለ ። እስኖቦል መቼም መች «የእን
ሰሳ ጀግና ፣ አንደኛ ደረጃ» ኒሻን ፣— እስከዚያን ጊዜ ድረስ
ያምኑ እንደ ነበረው — ተሸልሞ እንደማያውቅ ጭምር ለእን
ሰሳቱ አሁን ተገለጸላቸው ። ይህ ፣ ከከብት በረት ጦርነት በኋላ ፣
ባንድ ወቅት እስኖቦል ራሱ የነዛው አፈ ታሪክ ብቻ ነው ።
እንኳን ኒሻን ሊሸለም ቀርቶ ፣ እንዲያውም በጦርነቱ ላይ ስላ
ሳየው የፈሪነት ተግባር ወቀሳ ደርሶበታል ። አሁንም እንደ ገና ፣
አንዳንዶቹ እንሰሳት ይኸን ነገር የሰሙት በመደናገር ስሜት
ነበር ፤ ነገር ግን ፣ እስኩዊለር ትዝታዎቻቸው የተሳሳቱ መሆና
ቸውን በቶሎ ሊያሳምናቸው ቻለ ።

በመጪው ወራት ፣ አስገራሚ በሆነና እጅግ በሚያደክም
ጥረት - ምክንያቱም የሰብል ስብሰባውም ሥራ በዚሁ ወቅት ፣
ባንድ ሰሞን መፈጸም ስለ ነበረበት — የነፋስ ወፍጮው ግን
ባታ ሥራ አለቀ ። የመኪናው ዕቃዎች ገና መገጠም ስለ ነበረ
ባቸው ፣ ስለ ግዢያቸው የሚደራደረው ዊምፐር ነበር ፤ የግንቡ
ሥራ ግን ተጠናቅቋል ። ማንኛውንም ችግር ሁሉ ተቋቁመው ፣
ምንም እንኳን ልምድ ባይኖራቸው ፣ በኋላቀር መሣሪያዎች
ተጠቅመው ፣ መጥፎ ዕድልና የእስኖቦልንም የተንኮል ደባዎ
ችን አሸንፈው ፣ ሥራው ልክ በተወሰነው ቀን አለቀ ! በድካም
ዝለው ፣ ግን ልባቸው በኩራት ተሞልቶ ፣ ከመጀመሪያው ግን
ባታም ለእነርሱ ዓይን ይበልጥ ውብ መስሎ በሚታየው በተደ
ናቂው ሥራቸው ዙሪያ እንስሳቱ ደጋግመው ዞሩ ። ከዚህም
በላይ፣የግንቡ ውፍረት የቀድሞውን እጥፍ ያክላል።አሁንስ ፈንጂ
ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምንም ሊያፈርሰው አይችልም ። ሥራው
የቱን ያህል እንዳደከማቸው ፣ ምን ምን ተስፋ አስቆራጭ ሁኔ
ታዎችን አሸንፈው እንዳለፉ ሲያስታውሱ ፣ ደግሞም ፣ የነፋስ
መዘውሮቹ በሚዞሩበትና ዲናሞዎቹ በሚሠሩበት ጊዜ
በኑሮዋቸው ላይ የቱን ያህል ታላቅ ልዩነት እንደሚፈጠር ሲያ
ስቡ ይኸን ሁሉ ሲያስቡ ፣ ድካሙ ከላያቸው ላይ ተገፈፈና የድል
አድራጊነት ጩኸት እያሰሙ በግንቡ ዙሪያ ፈነጩ ። ናፖሌዎ
ንም ራሱ በውሾቹና ባውራ ዶሮው ታጅቦ የተጠናቀቀውን ሥራ
ሊጐበኝ ወረደ ። እንስሳቱ ስላሳዩት መልካም የሥራ ውጤት
በራሱ ስም ምሥራች አቀረበላቸውና የነፋሱ ወፍጮ « ናፖሌ
ዎን ወፍጮ » ተብሎ እንዲሰየም አስታወቃቸው ።

ከሁለቱ ቀን በኋላ ፣ እንስሳቱ ለልዩ ስብሰባ ወደ መጋዘኑ አዳራሽ ተጠሩ ። የማንቃውን ክምችት ለፍሬዲሪክ የሸጠው መሆኑን ናፖሌዎን ባስታወቃቸው ጊዜ ፣ በድንጋጤ ክው ብለው ቀሩ ። ነገ የፍሬድሪክ ዕቃ መጫኛ ጋሪዎች መጥተው እየጫኑ ማጋዝ ይጀምራሉ ። ከፒልኪንግተን ጋር የወዳጅነት ግንኙነት የመሠረተ ያስመስል በነበረበት ጊዜ ሁሉ ፣ ናፖሌዎን ውስጥ ውስጡን ከፍሬድሪክ ጋር ምስጢራዊ ስምምነት ሲያደርግ ቆይቷል ።

ከፎክስውድ ጋር የነበሩት ግንኙነቶች ሁሉ ተቋረጡ ፤ የስድብ መልእክቶች ለፒልኪንግተን ተላኩ ። ርግቦቹ ወደ ፒንችፊልድ ዕርሻ መኼዳቸውን እንዲያቋርጡና «ሞት ለፍሬድሪክ» የሚለውን መፈክር «ሞት ለፒልኪንግተን» በሚል መፈክር እንዲለው ጉ ተነገራቸው ። በዚሁ ጊዜ ፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የእንስሳትን ዕርሻ ለመውጋት ጦርነት ይነሣል ተብሎ የተወራው ወሬ ፈጽሞ ሐሰት መሆኑንና ፣ ፍሬድሪክ በራሱ እንስሳት ላይ ይፈጽማል የተባለው ወሬ እጅግ የተጋነነ መሆኑን ፣ ናፖሌዎን ለእንስሳቱ አረጋገጠላቸው ። ምናልባት እነ ዚህ ሁሉ ወሬዎች የመነጩት ከእስኖቦልና ከርሱ ወኪሎች ሳይሆን አይቀርም ። ስለዚህ አሁን እንደተገለጸው ፣ እስኖቦል ለካ ተደብቆ የሚኖረው በፒንችፊልድ ዕርሻ ክልል አልነበረም ፤ እንዲያውም በመሠረቱ ፣ በሕይወቱ እዚያ ደርሶ አያውቅም ፤ እርሱ የሚኖረው እንደሚነገረው እጅግ በመንደላቀቅ ፣ በፎክስውድ ነው ፤ ደግሞም እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ ካለፉት ብዙ ዓመታት ጀምሮ የፒልኪንግተን ተጠዋሪ ነበር ።

ዐሣማዎቹ በናፖሌዎን ብልጠት እጅግ ታላቅ የደስታ ስሜት ዐደረባቸው ። «ከፒልኪንግተን ጋራ የተወዳጀ አስመስሎ ፣ ፍሬድሪክ ዋጋውን በሣያ ፓውንድ ከፍ እንዲያደርግ አስገድዶታል » አለ እስኩዊለር ፤ «ማንንም ፣ ፍሬድሪክንም ቢሆን የማያምን መሆኑን ባስመሰከረ ጊዜ ነው ። ፍሬድሪክ ዋጋውን ሊከፍል የፈለገው ፣ እንድ ብጣሽ ወረቀት በሚመስል ፣ ቼክ በሚባል የተስፋ ሰነድ ብጤ ነበር ። ናፖሌዎን ግን አልተበለጠለትም ። ዋጋው ፣ በባለ አምስት ፓውንድ ኖቶች ፣ ጣንቃዎቹን ከማስረከቡ በፊት ፣ በቅድሚያ እንዲከፈል ጠየቀ ። ፍሬድሪክ በቅድሚያ

ከፍሏል ፤ ገንዘቡም ለነፋስ ወፍጮው የሚያስፈልጉትን የመ
ኪና ዕቃዎች ለመግዛት የሚበቃ ያህል ነው ።»

በዚሁ መኸከል ፣ ማንቃው በጋሪ በጥድፊያ እየተጋዘ ነበር ። ማንቃው በሙሉ ተግዞ ከተወሰደ በኋላ ፣ የፍሬዲሪክ ባንክ ኖቶችን እንስሳቱ እንዲያዩ ሌላ ልዩ ስብሰባ በመጋዘኑ ዐዳራሽ ውስጥ ተካኼደ ።

ፊቱ በደስታ ፈክቶና ፣ ሁለቱንም ኒሻኖቹን ደረቱ ላይ አንጠልጥሎ ፣ በመድረኩ ላይ ከተነጠፈው የማር ጉዝጓዝ ላይ ናፖሌዎን ጉብ ብሏል ፤ ከመኖሪያው ቤት ፣ ወጥ ቤት ውስጥ በተገኘውአንድ የሸክላ ሰሐን ላይ ገንዘቡ ተከምሮ ካንድ ጐን በኩል ተቀምጥዋል ። እንስሳቱ አንድ ባንድ ተሰልፈው ባይናቸው ሙሉ እያዩት ዐለፉ ፤ ቦክሰር ደግሞ አፍንጫውን አስጠግቶ ኖቶቹን እንደማሽተት ሲል ፣ እነኛ ስስ ነጫጭ ነገሮች በትንፋሹ ተርገብግበው ተንኰሻኰሹ (ኰሽታ አሰሙ) ።

ከሦስት ቀናት በኋላ ፣ አንድ በጣም አስደንጋጭ ትርምስ ተፈጠረ ። ዊምፐር ፣ ፊቱ ከልክ በላይ ገርጥቶ ፣ በብስክሌቱ እየበረረ መንገዱን ዐልፎ መጣ ፤ ብስክሌቱን ግቢው ውስጥ አሽቀንጥሮ ጥሎ ፣ በቀጥታ ወደ መኖሪያው ቤት ውስጥ ተንደርድሮ ገባ ። ከዚያ ቀጥሎ ፣ ከናፖሌዎን እፓርታማ ውስጥ በንዴት የማጓራት ድምፅ ተሰማ ። ስለደረሰው ሁኔታ ፣ ወሬው እንደ ሰደድ እሳት ባንድ አፍታ በዕርሻው ክልል ውስጥ ተሠራጨ ። የባንክ ኖቶቹ ሕገ ወጥ ገንዘቦች ናቸው ! ፍሬድሪክ ማንቃዎቹን በብላሽ (ያለ ዋጋ) ወሰደ ! ናፖሌዎን ወዲያው እንስሳቱ እንዲሰበሰቡ አስጠራቸውና ፣ ቁጣ በተሞላበት አስደንጋጭ ጩኸት በፍሬድሪክ ላይ የሞት ቅጣት ፍርድ ወሰነ ። «ፍሬድሪክ ከተያዘ በኋላ ፣ ከነነፍሱ መቀቀል አለበት ፤» አለ ። በዚሁ ጊዜ ፣ ከዚህ የክህደት ተግባር በኋላ ፣ የባሰ ነገር የሚመጣ መሆኑን አስጠነቀቃቸው ። ፍሬድሪክና ጭፍሮቹ በማንኛውም ወቅት ፣ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ይጠበቅ የነበረውን የጥቃት ርምጃ ሊወስዱባቸው ይችላሉ ። ወደ ዕርሻው ክልል በሚያስገቡት በሮች ሁሉ ዘቦች ተመደቡ ። በተጨማሪም ፤ ከፖልኪንግተን ጋራ ጥሩ ግንኙነትችን መልሶ ለመመሥረት ያስችል ይሆናል ተብሎ የተገመተ ፣ አስታራቂ መልእክት ይዘው አራት ርግቦች ወደ ፎክስውድ ተላኩ ።

ልክ በማግሥቱ አጥቂው ጦር መጣ ። ፍሬደሪክና ጭፍሮቹ ገና ድሮ ባለ አምስት ብረት በሩን ዘልቀው የገቡ መሆናቸውን የወሰን ጥበቃ ዘቦች ገሥግሠው መጥተው ዜናውን በተናገሩበት ወቅት ፣ እንስሳቱ ቁርስ ላይ ነበሩ ። እንስሳቱ በድፍረት ተነሥተው ሊገጥሙዋቸው ኼዱ ፤ ነገር ግን ፤ ይህ ጦርነት ፣ በከብት በረት ጦርነት ጊዜ እንዳገኙት ቀላል ድል የሚያስገኝ አልነበረም።

የመጡት አሥራ አምስት ሰዎች ሲሆኑ ፣ ከእነርሱም መኻከል ስድስቱ ያህል ጠመንጃ የያዙ ነበሩና ፣ አንድ አምሳ ያርድ እንደቀረቡ ተኩስ ከፈቱባቸው ። እንስሳቱ አስደንጋጩን የተኩስ ጩኸትና የጥይቶቹን እርሳስ ንድፊያ ለመቋቋም ስላልቻሉ ፣ ምንም እንኳን ናፖሌዎንና ቦክሰር ሊያደፋፍሯቸው የሞከሩ ቢሆንም ፣ በፍጥነት ወደ ኋላ ተመልሰው ተባረሩ ። ከፊሎቹ ቆስለዋል ። በዕርሻው ግቢ ውስጥ ከነበሩት ቤቶች ውስጥ ተሸሽገው በየሽንቁር ጭላንጭሎች ወደ ውጭ ይሰልሉ ጀመር ። መላው የግጦሹ መሬት ፣ የነፋስ ወፍጮውም ሳይቀር ፣ በጠላት እጅ ወድቋል ። ለጊዜው ናፖሌዎንም ጭምር ግራ የተጋባ መሰለ። አንዳችም ቃል ሳይተነፍስ ፣ ጭራውን ወደ ላይ ገትሮ እያወዛወዘ ፣ ላይና ታች ተንጐራደደ ። ዕዝን ያሉ አይታዎቹ ወደ ፎክስውድ አቅጣጫ ይወረወራሉ ። ፒልኪንግቶንና ጭፍሮቹ ቢረዱዋቸው ኖሮ ፣ እስካሁን የዛሬው ቀን ድል በተገኘ ነበር ። ነገር ግን በዚህ ወቅት ፣ ትናንት ተልከው የነበሩት አራት ርግቦች ተመልሰው መጡ ፣ ከእነርሱም አንዱዋ ፣ ከፒልክንግተን የተላከ አንድ ቁራጭ ወረቀት ይዛለች ። በወረቀቱ ላይ በእርሳስ የተጻፈ እንዲህ የሚሉ ቃላት ነበሩ ፤ «ዋጋህን አገኘህ ።»

ወዲያውም ፍሬደሪክና ጭፍሮቹ በነፋስ ወፍጮው ግንብ ዙሪያ ቆመው ነበር ። እንስሳቱ ተመለከትዋቸውና በሀዘን ስሜት ተንሾካሾኩ ። ከሰዎቹ መኻከል ሁለቱ ድጅኖና መዶሻ ይዘው ቀረቡ ። የነፋስ ወፍጮውን ግንብ አፈራርሰው ሊጥሉ ነው ።

«የማይቻል ነው !» ብሎ ጮኸ ፣ ናፖሊዎን ። «ግንቡን የሠራነው በወፍራሙ ስለሆነ ፣ እንዲህ በቀላሉ የሚፈርስ አይደለም ። ባንድ ሳምንት ጊዜም ሊያፈርሱት አይችሉም ። አይዞን ጓዶች !»

ቤንጃሚን ግን የሰዎቹን እንቅስቃሴዎች እትኩሮ ይመለ ከታል ። ሁለቱ ሰዎች በመዶሻና በመራጃ ከግንቡ ሥር በኩል አንድ ሽንቁር እየሰረሰሩ ነው ። ቀስ ብሎና በመደሰት እኳኋን ሊባል ይቻላል ፤ ቤንጃሚን ለምቦጩን እነቃነቀ ። «መቼ እጣ ሁት» አለ ። «ምን እየሠሩ እንደሆነ አይታያችሁም ? ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፣ በዚያ ሽንቁር ውስጥ የፈንጂ ዱቄት ሊጨምሩ ነው ።»

እንስሳቱ በፍርሀት እንደ ተዋጡ ጠበቁ ። ከተሸሸጉባቸው ቤቶች ለመውጣት መሞከር አሁን የሚቻል አልነበረም ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሰዎቹ ወደያቅጣጫው ሲሮጡ ታዩ ። ከዚያ በኋላ ፣ ጉሮ የሚያደነቁር የፍንዳታ ጩኸት አስተጋባ ።

ርግቦቹ ወደ ሰማይ በረሩ ፤ እንስሳቱም ሁሉ ፣ ከናፖሌዎን በስተቀር ፣ በሆዳቸው ተዘርረው ዐንገታቸውን ቀበሩ ። ተመል ሰው በተነሡ ጊዜ ፣ የነፋስ ወፍጮው ግንብ ቆሞበት ከነበረው ቦታ ላይ ከባድ የጥቁር ጭስ ደመና ሲያንዣብብ ተመለከቱ ። ነፋሱ ቀስ በቀስ ወዲያ አገለለው ። የነፋስ ወፍጮው ግንብ ወድሞአል !

ይህን እንደ ተመለከቱ እንስሳቱ ድፍረታቸው ተመለሰላ ቸው ። ቅድም ዐድሮባቸው የነበረው የፍርሀትና የተስፋ መቁ ረጥ መንፈስ በዚህ አሠቃቂና ወራዳ ተግባር ተዋጠ ። ለመበቀል ኃይለኛ ጩኸት እሰሙና ፣ ሌላ ትእዛዝ ሳይጠብቁ ባንድነት ለማጥቃት ወደ ፊት ገሥግሠው ወደ ጠላት አመሩ ። በዚህ ጊዜ ፣ እንደ በረዶ በላያቸው ላይ ይዘንቡ የነበሩትን ጨካኝ የጥይት እርሳሶች ከምንም አልቆጠሩዋቸውም ። ጭካኔ የተሞላ በት መራራ ጦርነት ነበር ። ሰዎቹ እያከታተሉ ሲተኩሱ ቆይ ተው ፣ እንስሳቱ በተጠጉዋቸው ጊዜ ፣ በዱላና በከባድ መጫሚ ያዎቻቸው ይቀጠቅጡዋቸው ጀመር ። አንዲት ላም ፣ ሦስት በጎችና ሁለት ዳክዮዎች ተገደሉ ፤ አብዛኞቹም ቆሰሉ ። ከደጀን ሆኖ ጦሩን ይመራ የነበረው ናፖሌዎን ሳይቀር ፣ የጅራቱን ጫፍ አንዲት የጥይት እርሳስ ጨርፋዋለች ። ግን ሰዎቹም ቢሆኑ በቦክሰር ኮቴዎች እናታቸውን ተመትተዋል ፤ ሌላው አንዱ ፣ ሆዱ ላይ ባንዲት ላም ቀንድ ተወግቷል ፤ ሌላው ደግሞ ፣ ሱሪ ውን ሞሊና ብሉቤል ቀዳደውበታል ።

በቁጥቋጦዎች ሥር ተደብቀው ፣ ከሰዎቹ ኋላ ከበባ እንዲያደርጉ ታዘው የነበሩት የናፖሌዎን የክብር ዘብ ፣ ዘጠኙ ውሾች ድንገት ብቅ ብለው ባጓሩባቸው ጊዜ ፣ ሰዎቹ ብርክ ያዛቸው የመከበብ አደጋ ሊደርስባቸው እንደሚችል ታያቸው ። ማም ለሚ መንገዱ ከመዘጋቱ በፊት እንዲያመልጡ ፣ ፍሬድሪክ ለሰዎቹ ጮኸ እስጠነቀቀና ወዲያው ፣ ያ ፈሪው ጠላት ሁሉ እግሬ አውጭኝ ብሎ ሸሸ ።

እንስሳቱ እስከ ሜዳው ግርጌ ድረስ አባረሩዋቸውና ፣ በሾኹ እጥር ሥር ለመሹለክ በሚፍጨረጨሩበት ወቅት ፣ የመጨረሻዎቹን እርግጫዎቻቸውን አቀመሱዋቸው ።

ድል አደረጉ ፤ ነገር ግን ደክሚቸዋል ፤ ደማቸውንም ያዘሩ ። እያነከሱ ዝግ ብለው ወደ ዕርሻቸው ግቢ ተመለሱ ። በዕርሻው ግቢ በየሣሩ ላይ ተረፍርፈው የነበሩትን የጓዶቻቸውን ሬሳዎች ሲመለከቱ ፣ እንዳንዶቹ እንባቸውን ሊገቱ አልቻሉም ። የነፋስ ወፍጮው ግንብ ተሠርቶበት ቆሞ ከነበረው ቦታ በደረሱ ጊዜ ፣ በሀዘን ተውጠው ላንዳፍታ በዝምታ ተክዘው ቆሙ ። አዎ ፤ በቦታው የለም ፤ የድካማቸው ፍሬ ሁሉ ወድሟል ማለት ይቻላል ! መሠረቱ ሳይቀር በከፊል ፈራርሷል ። መልሰው ለመሥራት በሚፈልጉበት ጊዜ ፣ እንደ ቀድሞው በወዳደቁት ድንጋዮች ሊጠቀሙ አይችሉም ። በዚህኛው ጊዜ ድንጋዮቹም ጭምር ድራሻቸው ጠፍትዋል ። የፍንዳታው ኃይል ከብዙ ሜትሮች ርቀት አሽቀንጥሮ በታተናቸዋል ። የነፋስ ወፍጮውም ግንብ በዚያ ቦታ ከቶ እንዳልነበረ ሆንዋል ።

ወደ ዕርሻው ግቢ ሲቃረቡ ፣ ባልታወቀ ምክንያት በጦርነቱ ወቅት ጠፍቶ የነበረው እስኩዊለር ፣ ጡብ ጡብ እያለ ወደ እነርሱ በመምጣት ጅራቱን እየቆላ በፈገግታ ቀረባቸው ። ከወደ ዕርሻው ቤቶች አቅጣጫ የእንድ ጠመንጃ ክብረ በዓላዊ ተኩስ ድምፅ ተሰማ ።

«ይህ የምን ተኩስ ነው ?» ሲል ጠየቀ ፣ ቦክሰር ።

«የተቀዳጀነውን ድል ለማክበር ነዋ !» ብሎ ጮኸ እስኩዊለር ።

«የምን ድል ?» አለ ቦክሰር ። ጉልበቶቹ ደም እያዘሩ ነበር ፤ አንድ ሚማው ወልቆዋል ኮቴውም ተሰንጥቋል ፤ ደግሞም እንድ ደርዘን ያህል የጥይት እርሳሶች በኋላ እግሮቹ ውስጥ ተሰግ ስገውበታል ።

«የምን ድል አልክ ፣ ጓድ ? ጠላትን ከመሬታችን—ከተቀ ደሰችው የእንስሳት ዕርሻ—አባረን አስወጥተን የለም እንዴ?»

«ግን እኮ የነፋስ ወፍጮውን ግንብ አፈራርሰውታል ። ሁለት ዓመት ሙሉ የደከምንበትን አውድመውታል !»

«ምን አለበት ? ሌላ የነፋስ ወፍጮ ግንብ እንሠራለን ። ከፈለግንም ስድስት የነፋስ ወፍጮ ግንቦችን እንገነባለን ። በፈ ጸምነው ታላቅ ድርጊት ልትደሰት ይገባል ፣ ጓድ ። ጠላት ይህ ችን አሁን ቆመን የምንገኝባትን መሬት ወርሮ ይዞብን ነበር ። አሁን ግን — ለጓድ ናፖሌዎን አመራር ምስጋና ይድረሰውና እያንዳንዷን ስንዝር መሬታችንን አስመልሰን ይዘናል !»

«እንግዲያውስ ቀድሞም የራሳችን የነበረውን ነዋ ያስመ ለስነው ?» አለ ቦክሰር ።

«የእኛ ድል ይኸው ነው» አለ እስኩዊለር ።

እያነከሱ ወደ ግቢያቸው ገቡ ። በቦክሰር የኋላ እግሮች ውስጥ ተሰግስገው የነበሩት የጥይት እርሳሶች እየቆጠቆጡ ያሳምሙታል ። ከመሠረቱ እንሥቶ የነፋስ ወፍጮውን መልሶ የመገንባቱ ሥራ ወደፊት የሚጠብቀው መሆኑ ካሁኑ ታወሰ ውና ፣ መንፈሱን ያጠናክር ጀመር ። ነገር ግን ፣ ዕድሜው አሥራ አንድ ዓመት እንደሞላና ከእንግዲህ ወዲያ ጡንቻዎቹ እንደ ቀድሞ ጠንካራዎች እንደማይሆኑ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ፣ አሁን ትዝ አለው ።

ነገር ግን እንስሳቱ አረንጓዴው ባንዲራ ሲውለበለብ ባዩ ጊዜ ፣ ጠመንጃውም እንደገና ሲተኮስ በሰሙ ጊዜ—ባጠቃላይ የተተኮሰው ሰባት ጊዜ ነበር—ደግሞም ናፖሌዎን ለፈጸሙት አኩሪ ተግባር እያመሰገናቸው ያሰማውን ዲስኩር በሰሙ ጊዜ ፣

በእርግጥም ታላቅ ድል ማድረጋቸውን አመኑ ። የተገደሉትም እንስሳት በክብር ሥርዓት ተቀበሩ ። በሬሳ መኪናነት የቀረበ ውን ጋሪ የጐተቱት ቦክሰርና ክሎቨር ሲሆኑ ፣ ናፖሌዎንም ሥርዓተ ጉዞውን ፊት ፊት ይመራ ነበር ። ክብረ በዓሉ ሁለት ሙሉ ቀን ተከበረ ፤ መዝሙሮች እየተዘመሩ ፣ ዲስኩሮች እየተደ ሰኩሩ ፣ ጠመንጃውም እየተደጋገመ ሲተኮስ ዋለ ፤ ደግሞም ለእ ያንዳንዱ እንስሳ አንድ አንድ የፖም ስጦታ ከመስጠትም በላይ ፣ አምሣ አምስት ግራም ጥሬ ለእያንዳንዱ አእዋፍና ፣ ሦስት ሦስት ብስኩት ለእያንዳንዱ ውሻ ታደለ ። ጦርነቱ «የነፋስ ወፍጮ ጦርነት» ተብሎ እንዲሰየም መግለጫ ተሰጠ ፤ ናፖሌ ዎን ለራሱ የሰጠውን «የአረንጓጔው ባንዲራ ኒሻን» ተብሎ የተሰየመውን አዲስ ኒሻን ፈጠረ ። የባንክ ኖቶቹ አሳዛኝ ጉዳይ ፣ ባጠቃላዮቹ የፈንጠዚያ ስሜቶች ተውጦ ተረሳ ።

በመኖሪያ ቤቱ ምድር ቤት የመጠጥ ማኖሪያ ጓዳ ውስጥ ፣ አንድ ሣጥን ዊስኪ ዐሣሞቹ ያገኙት ከዚህ ጥቂት ቀኖች በኋላ ነው ። ወደ መኖሪያ ቤቱ ውስጥ በገቡበት ሰሞን ችላ ብለውት ነበር ።

ያን ዕለት ማታ ፣ አንድ ከፍተኛ የዘፈን ድምፅ ከወደ መኖሪ ያው ቤት ሲያስተጋባ ተሰማ ፤ ሁሉንም የገረማቸው ደግሞ ፣ የዘፈኑ ጣዕመ ዜማ «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘውን መዝሙር የሚያስታውስ መሆኑ ነው ። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ገደማ ፣ ናፖሌዎን የሚስተር ጆንሰን አንድ አሮጌ ክብ ባርሜጣ አድርጎ ፣ በጓሮ በር ወጥቶ ፣ በግቢው ውስጥ ሜዳ ላይ ዙሪያውን በፍጥነት ሲጋልብ ቆይቶ ፣ እንደ ገና ወደ ቤቱ ውስጥ ሮጦ እንደ ገባ በግልጽ ታይቷል ። ጠዋት ግን ፣ የመኖሪያው ቤት ጸጥታ ሰፈነበት ። አንድም ዐሣማ የሚንቀሳቀስ አይመስ ልም ነበር ። እስኩዊለር ብቅ ባለ ጊዜ ፣ ሦስት ሰዓት ገደማ ሆኖዋል ፤ እየተንቈራሰሰና ሀዘን ተጭጭኖት ፣ ዐይኖቹን መግ ለጥ ተስኖት ፤ ጅራቱን ተ ላው አዝለፍልፎ ሲታይ ፣ ሁለንተ ናው ከባድ ሕመም ያደረበት ይመስል ነበር ። እንስሳቱን አንድ ላይ ሰበሰባቸውና ፣ ሊነግራቸው የሚፈልገው አንድ አስደንጋጭ ወሬ እንዳለው ገለጸላቸው። «ጓድ ናፖሌዎን በጣር ላይ ይገኛል!»

የሰቆቃ ዋይታ አስተጋባ ። ከመኖሪያው ቤት በሮች ውጭ ድርቆሽ ተጐዘጐዘና እንስሳቱ ኮቴያቸው እንዳይሰማ በእግር

ቻቸው ሚና ተራመዱ ። መሪያቸውን ሞት ቢነጥቃቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እርስ በርስ እየተንሾካሸኩ ዐይኖ ቻቸው እንባ አቀረሩ ። እስኖቦል ፣ ዕቅዱ እንደ ምንም ተሳክቶ ለት ፣ በናፖሌዎን ምግብ ውስጥ መርዝ ለመጨመር እንደቻለ ወሬው ተዛመተ ። በአምስት ሰዓት እስኩዊለር ሌላ መግለጫ ለማስማት መጣ ። «በምድር ላይ እንደ መጨረሻ ድርጊቱ በመቁጠር ፣ ጓድ ናፖሌዎን አንድ ተደናቂ ድንጋጌ አውጥቷል ፤ አልኮል የጠጣ ፣ በሞት እንዲቀጣ ።»

ቢሆንም ፣ ወደ ማታው ሰዓት ፣ ናፖሌዎን እንደ መሻል ያለው መሆኑ ተገለጠ ። በማግሥቱ ጠዋት ደግሞ ፣ በመዳን ላይ መሆኑን እስኩዊለር መጥቶ ነገራቸው ። በዚያው ቀን ማምሻ ላይ ፣ ናፖሌዎን በሥራው ላይ ተገኘ ፤ ደግሞ በተከታዩ ቀን ፣ ስለ መጠጥ አጠማመቅና ስለ እረቂ አወጣጥ የሚያስረዳ አንዳንድ እነስተኛ መጻሕፍት ከዊሊንግተን ገዝቶ እንዲያመጣ ለት ዊምፐርን ያዘዘ መሆኑ ተሰማ ። ካንድ ሳምንት በኋላ ፣ በጡረታ ለሚገለሉ እንስሳት የግጦሽ ቦታ ይሆናል ተብሎ ታስቦ ተከልሎ የቆየው ፣ ከፍራፍሬ አትክልቶች በታች የነበረው እነስተኛ መስክ እንዲታረስ ናፖሌዎን አዘዘ ። የግጦሽ ማሩ ስለተሟጠጠ እንደ ገና የማር ዘር ሊዘሩበት ነው ተብሎ ተወርቶ ነበር ፤ ነገር ግን ፣ ናፖሌዎን ገብስ ሊያዘራበት እንደ ሆነ ወዲያው ታወቀ ።

በዚህ ሰሞን ገደማ ፣ ማንም ሊረዳው ያልቻለ አንድ አስገራሚ ሆናቴ ተከሠተ ። አንድ ቀን ሌሊት ፣ ወደ እኩለ ሌሊት ገደማ ፣ ኃይለኛ የመንኰታኰት ድምፅ በግቢው ውስጥ ስለተሰማ ፣ እንስሳቱ ሁሉ ከየጋጣዎቻቸው ግር ብለው ወጡ ። የጨረቃው ብርሃን ወለል ብሎ የሚያበራበት ሌሊት ነበር ። ሰባቱ ትእዛዛት ከተጻፉበት ከትልቁ መጋዘን የመጨረሻው ግድግዳ ግርጌ ፣ አንድ መሰላል ለሁለት ተገምሶ ወድቋል ። እስ ኩዊለር ፣ ለጊዜው ሕሊናውን ስቶ ፣ ባጠገቡ ተዘርርሮዋል ፤ ባቅ ራቢያው ደግሞ አንድ ፋኖስ ፣ አንድ የቀለም መቀቢያ ብሩሽና አንድ የተደፋ የነጭ ቀለም ቆርቆሮ ወድቀው ይታያሉ ። ውሾቹ ወዲያው በእስኩዊለር ዙሪያ ከበቡና መራመድ እንደቻለ ወደ መኖሪያው ቤት አጅበውት ተመለሱ ። ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ ፣ ከቤንጃሚን በስተቀር ፣ ከእንስሳቱ ማንኛቸውም ሊገባቸው የጡረታ ዕድሜያቸው ለደረሰ እንስሳት ግጦሽ ቦታ ሆኖ ይከለ

አልቻለም ፤ እርሱም ገባኝ በማለት አኳኋን ለንቦጩን አንቃንቀ ፤ ነገር ግን ምንም አልተናገረም ።

ከጥቂት ቀኖች በኋላ ግን ፣ ሙሪየል ሰባቱን ትእዛዛት ለራሰዋ ባነበበች ጊዜ ፣ እንስሳቱ ተሳስተው ያስታወሱት አሁንም አንድ ነገር መኖሩን አስተዋለች ። አምስተኛው ትእዛዝ «ማንኛውም እንስሳ አልኮል መጠጣት የለበትም» የሚል መስሎዋቸው ነበር ፤ ነገር ግን ፣ የረሱዋቸው ሁለት ቃላት ነበሩ ። በእውነቱ ትእዛዙ የሚለው ፤ «ማንኛውም እንስሳ አልኮል «ከመጠን በላይ» መጠጣት የለበትም» ነው ።

## ዘጠኝ

የተሰነጠቀው የቦክሰር ጥፍር ለመዳን ብዙ ጊዜ ፈጀበት የክብረ በዓሉ ሥርዓት በተፈጸመ ማግሥት ፣ የነፋስ ወፍጮውን መልሶ የመገንባቱን ሥራ ጀመረ ። ቦክሰር የአንድ ቀን እንኳን ዕረፍት ወስዶ ከሥራ ለመቅረት አልፈለገም ፤ ደግሞም ሕመም እንደሚሰማው ላለማሳየት ቁርጥ ፈቃድ አደረገ ። ኮቴው በጣም ያሠቃየው እንደ ነበረ ማታ ማታ ለክሎቨር በግል ይነግራት ነበር ። ክሎቨር ራሷ እያኘከች በምታዘጋጃቸው የቅጠላቅጠል መድኃኒቶች ኮቴውን እያጀለች ታክመዋለች ፤ ደግሞም እርስዋና ቤንጃሚን የሥራ ድካሙን እንዲቀንስ ሁለቱም ይመክሩታል ። «የአንድ ፈረስ ሳንባዎች ለዘላለም አይቆዩም» አለቻው ። ቦክሰር ግን አይሰማትም ። እርሱ እንደሚናገረው ፣ ያለው አንድ ምኞት ብቻ ነው — የጡረታ ዕድሜው ከመድረሱ በፊት ፣ የነፋስ ወፍጮው ሥራ ለመገባደድ ተቃርቦ ማየት ።

በመጀመሪያው ወቅት ፣ የእንስሳት ዕርሻ ሕጎች ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታወጁ ፣ የጡረታ ዕድሜ ለፈረሶችና ለዐሣማዎች ፣ ባሥራ ሁለት ዓመት ፤ ለላሞች ፣ በአሥራ አራት ዓመት ፤ ለውሾች ፣ በዘጠኝ ፤ ለበጎች ፣ በሰባት ፤ እና ለዶሮዎችና ለዳክዮዎች ፣ በአምስት ዓመት እንዲሆን ተወስኖ ነበር ። ነጻ የጡረታ መብቶች እንዲኖሩም ስምምነት ነበር ። እስካሁን ድረስ በጡረታ የተገለለ አንድም እንስሳ አልነበረም ፤ ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፣ ተደጋግሞ በጉዳዩ ላይ ክርክር ተደርጎበታል ። ከፍራፍሬ አትክልቶች ዕርሻ በታች ያለው አነስተኛ ሜዳ ለገብስ ማሳ ከተከለለ ወዲህ ፣ ከሰፊው የግጦሽ መስክ አነስተኛው ክፍል ታጥሮ ፣

ላል፣ የሚል ወሬ ተሠራጨ። እንደ ተነገረውም ፣ ለአንድ ፈረስ የጡረታ አበል በቀን ሦስት ፓውንድ ጥሬና ፣ በክረምት ወራት አሥራ አምስት ፓውንድ ድርቆሽ ፣ ደግሞም ሲቻል ፣ አንድ ካሮት ወይም አንድ ፖም በሕዝብ በዓላት ቀኖች ይጨመርለታል የሚል ነው ። የቦክሰር አሥራ ሁለተኛው የልደት በዓል የሚው ለው በሚቀጥለው ዓመት የበጋ ወራት መጨረሻ ላይ ነው ።

በዚሁም መካከል ኑሮው ከባድ ሆኖ ነበር ። የክረምቱ ወራት እንዳለፈው ክረምት ብርዳም ሆነ ፤ የምግብ እጥረት ደግሞ የባሰ ሆነ ። አሁንም እንደ ገና የሁሉም መቁነን ተቀነሰ ፤ ከዐሣማዎቹና ከውሾቹ በስተቀር ። እስኩዊለር እንዳስረዳቸው አለቅጥ የጠበቀ የመቁነን እኩልነት ከእንስሳዊነት መርሆ የሚቃረን በሆነ ነበር ። የሆነ ሆኖ ፣ ምንም ዓይነት ሁኔታ ቢከ ሠት ፣ እንደ እውነቱ ሲታይ ፣ የምግብ እጥረት የሌለባቸው መሆ ኑን ለማሳመን እንዳችም ችግር አልገጠመውም ።

ለጊዜው ፣ በእርግጥ ፣ የመቁነን መስተካከል እንዲደረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ። (እስኩዊለር በዚህ ጉዳይ ሲናገር «መስተካከል» በማለት እንጂ «መቀነስ» በሚለው ቃል አይ ጠቀምም) ፤ ግን ከጆንስ ጊዜ ሲወዳደር የተደረገው መሻሻል በጣም ከፍተኛ ነው ። በተንጫረረ ፈጣን ድምፅ አኃዞችን በማ ንበብ ፣ በጆንስ ጊዜ ይሰጣቸው ከነበረው ይበልጥ አጃ ፣ ይበልጥ ድርቆሽ ፣ ይበልጥ የሥራሥር ምግብ ፣ ባሁኑ ጊዜ እንደሚሰጣ ቸው ፣ የሥራ ሰዓቶች እንደተቀነሱ ፣ የመጠጥ ውኃቸው የተሻለ ጥራት እንዳለው ፣ ከልጆቻቸው አብዛኞቹ በለጋ ዕድሜያቸው እንደማይቀጩና በየጋጣቸውም ውስጥ የበለጠ ሣር ተጐዝጉዞ ላቸው ከተባዮች ሥቃይ እንደ ዳኑ ፣ በዝርዝር በመግለጽ ያሳም ናቸዋል ። እንስሳቱ የነገራቸውን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ያምናሉ ። እውነቱን ለመናገር ፣ ጆንስም ሆነ የእርሱ ድርጊቶች ሁሉ ከሁ ላቸውም አእምሮ ተሠርዞ ነበር ለማለት ይቻላል ። ባሁኑ ጊዜ ኑሮ ያልተሟላና ችግር የበዛበት መሆኑን ፣ ብዙውን ጊዜ እንደሚራቡና በብርድ እንደሚሠቃዩ ፣ በመኝታም ጊዜ ካልሆነ በስተቀር አብዛኛውን ጊዜ እንደሚሠሩ ያውቃሉ ። ነገር ግን በድሮ ጊዜ የባሰ እንደ ነበረ አይጠረጠርም ። እንደዚህ በማመ ናቸው ደስ ይላቸዋል ። ከዚህም በተረፈ ፣ በዚያ ጊዜያት ተገኘ

ዎች (ባሮች) ነበሩ ፤ አሁን ግን ነጻ ናቸው ፤ እስኩዊለር ከማመ ልከት እንዳልቦዘነ ሁሉ ፣ ይህ ነው ፣ ዋናው ልዩነት ።

ባሁኑ ጊዜ የበላተኛው ቁጥር ጨምሮዋል ። በመጪው ወራት ፣ አራቱ ሴት ዐሣማዎች ሁሉም ባንድ ሰሞን ወለዱ ፤ ባንድነት የአራቱ ግልገሎች ብዛት ሰላሳ አንድ ነበሩ ። የዐሣማ ግልገሎቹ ሁሉ መልክ ቡሬማ ነበርና ፣በዕርሻው ቦታ የነበረው ብቸኛው ያሣማ ኮርማ ናፖሌዎን ስለነበረ፣ አባታቸው ማን እን ደሆነ ለመገመት አዳጋች አልነበረም ። ወደፊት የቤት መሥሪያ ጡብና ሣንቃዎች በተገዙ ጊዜ ፣ በዕርሻው ግቢ ውስጥ አንድ ተማሪ ቤት እንደሚሠራ ተገለጸ ። ለጊዜው ፣ የዐሣማዎቹን ግልገሎች ናፖሌዎን ራሱ በወጥ ቤቱ ክፍል እያስተማራቸው ነው ። የሰውነት እንቅስቃሴ ልምምዳቸውን ባትክልቱ ውስጥ ያካኼዳሉ፤ ከሌሎቹ ታዳጊ እንስሳት ጋራ እንዲጫወቱ አይፈቀድ ላቸውም ። በዚሁ ጊዜ ገደማ ፣ አንድ ዐሣማና አንድ ሌላ እንስሳ በመንገድ ላይ ሲገናኙ፣ ሌላው እንስሳ መንገድ እንዲለቅ የሚል ደንብ ጭምር ወጥቶ ነበር ፤ በተጨማሪም ዐሣማዎች ሁሉ ፣ ትናንሾችም ሆኑ ትላልቆቹ ፣ እሑድ እሑድ ቀን ፣ አረንጓዴ ሪባኖች በጅራታቸው ላይ እንዲያሥሩ መብት ተሰጥቶዋቸዋል ።

በዚህ ዓመት የዕርሻ ተቋሙ መልካም ክንውኖችን ፈጽ ምዋል ፤ ግን አሁንም ቢሆን የገንዘብ እጥረት ነበረበት ። ለት ምህርት ቤቱ መሥሪያ ጡቦች ፣ አሸዋና ኖራ መገዛት ነበረባቸው ፤ ደግሞም ለነፋስ ወፍጮው የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎች ለመ ግዣ ፣ እንደገና ገንዘብ መቆጠብ መጀመር ነበረበት ፤ ከዚያም ለቤት ውስጥ መብራት የፋኖስ ላምባና ሻማዎች ያስፈልጋሉ ፤ ለናፖሊዎንም ማዕድ ስኳር ያስፈልጋል ፤ (ያወፍራቸዋል በሚል ሰበብ ሌሎቹ ዐሣማዎች ይህን እንዳይመገቡ ከልክሏል) ። ደግ ሞም የሥራ መሣሪያዎች ፣ ምስማሮች ፣ ሲባጎ ፣ ከሰል ፣ ሽቦ ፣ ቁርጥራጭ ብረታ ብረት ፣ የውሻ ብስኩትና የመሳሰሉት የተለመ ዱት መተኪያዎች ሁሉ ያስፈልጋሉ ። አንድ ክምር ድርቆሽና ከፊሉ የድንች አዝመራ ተሸጠ ፤ እንደዚሁም የዕንቁላሉ ሽያጭ ውል በሳምንት ወደ ስድስት መቶ እንዲያድግ ተደረገ ፤ ስለዚህ ፣ በዚያ ዓመት ውስጥ ዶሮዎቹ የቁጥራቸውን ሚዛን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ምንም ያህል ጫጩቶች ሊፈለፍሉ አልቻሉም ። በታኅሣሥ ወር ተቀንሶ የነበረው የመቁነን መጠን ፣ እንደገና

በየካቲት ወር እንዲቀነስ ተደረገ ፤ ላንባም ለመቆጠብ ሲባል ፣ በጋጣዎች ውስጥ የፋኖስ መብራቶች ማብራት ተከለከለ ። ዐሣማዎቹ ግን ፣ በቂ ድሎት የነበራቸው ይመስላሉ ፤ እንዲያውም ፣ ሌላው ቢቀር ፣ እየወፈሩ ኼደዋል ።

በየካቲት ወር መጨረሻ ገደማ፣አንድ ቀን ከቀትር በኋላ፣ከዚያ በፊት እንስሳቱ አሽትተውት የማያውቁት ዓይነት አንድ ሞቅ ያለ፣ ጣፋጭ የሚያጓጓ ሽታ፣በጆንስ ጊዜ ሥራውን አቋርጦ ከነበረውና፣ ከወጥ ቤቱ ወዲያ ከነበረው ከትንሹ የመጠጥ መጥመቂያ ቤት ተነሥቶ ግቢውን አወደው ። «አሻሮ ቁሌት ሽታ ነው» አለ አንዱ ። እንስሳቱ በጉጉት እየሩን እሽተቱና ለራት የተቆላ የገብስ ዱቄት (በሶ) እየተዘጋጀልን ይሆናል ብለው አሰቡ። ግን ምንም የተቆላ የገብስ ዱቄት (በሶ) አልታየም ፤ እንዲያውም በተከታዩ እሑድ ዕለት እንደተገለጸው ፣ ከእንግዲህ ወዲያ ፣ ገብሱ ሁሉ ለዐሣማዎች የተመደበ መሆኑ ተነገረ ። ከፍራፍሬዎች አትክልት ወዲያ ካለው የተመረተ ገብስ ነበርና ባሁኑ ጊዜ እያንዳንዱ ዐሣማ በቀን እንዳንድ ግማሽ ሊትር የቢራ መቁነን ፤ ለናፖሌዎን የዚህ እጥፍ እንደሚሰጠው ወሬው ወዲያው ተዛመተ ። ለናፖሌዎን የሚቀርብለት ፣ «ክራውን ደርቢ» በተባለው ዓይነት የሸርባ ማቅረቢያ ሰሐን ሆኖ ነው ።

ነገር ግን መቻል የነበረባቸው ችግሮች ቢከሠቱም ቅሉ ፣ ያሁን ጊዜ ኑሮዋቸው ከድሮው እጅግ የላቀ ክብር ያለው በመሆኑ ይካካሳል ። ብዙ መዝሙሮች ይዘመራሉ ፤ ብዙ ዲስኩሮች ይደሰኮራሉ ፤ ብዙ የክብረ በዓል ሰልፎች ይካኼዳሉ ። «ድንገተኛ» (ስሜት አነሣሺው) የተሠኘ ሰላማዊ ሰልፍ በሳምንት አንድ ጊዜ እንዲካኼድ ናፖሌዎን አዝዞ ነበር ፤ በተወሰነው ሰዓት እንስሳቱ ሥራቸውን ያቆሙና በወታደራዊ አሰላለፍና ርምጃ ፣ ዐሣማዎቹ ከፊት ፊት እየመሩ ፣ ከዚያም ፈረሶች ፣ ከዚያ ለጥቆ ላሞች ፣ ከዚያ በጎች ፣ ከዚያም ዶሮዎችና ዳክዮዎች ሆነው ቅጥር ግቢውን ይዞራሉ ።

ውሾቹ በሰልፉ ጐን ያጅባሉ ፤ ከሁሉ ግንባር ቀድሞ የሚመራው ፣ ጥቁሩ የናፖሌዎን አውራ ዶሮ ነው ። ቦክሰርና ክሎቨር ሁል ጊዜ ለሁለት የሚያነግቡት አንድ አረንጓጌ ዐላማ ፣ በላዩ ላይ የኮቴና የቀንድ ምስል የተሳለበት ሆኖ «ረጅም ዕድሜ ለንድ ናፖሊዎን !» የሚል ጽሑፍ ከግርጌው ይገኝበታል ። ከዚያ በኋላ

ለናፖሊዮን ክብር የተደረሱ ግጥሞች ይነበባሉ ፤ የምግብ ሰብል ምርቶችም በምን ያህል እንዳደጉ ዝርዝር መግለጫ በማቅረብ ፥ እስኩዊለር ንግግር ያደርጋል ፤ በበዓላትም ቀኖች ሁሉ ጠመን ጃው ይተኰሳል ። ስሜት አነሣሺውን ድንገተኛ ሰላማዊ ሰልፍ ከማንም የበለጠ የሚወዱት በጎቹ ስለነበሩ ፣ «ጊዜ ማጥፋት ነው ፤ በብርድ ላይ ተገትረን ዋልን» በማለት ማንኛውም ተቃ ውሞ ያቀረበ እንደ ሆነ (ዐሣማዎች ወይም ውሾች በሌሉበት ቦታ ጥቂት እንስሳት ያደርጉ እንደነበረው ሁሉ) ፥ በጎቹ «አራት እግሮች ጥሩ ፤ ሁለት እግሮች መጥፎ !» የሚለውን ኃይለኛ ጩኸት በማሰማት ጸጥ ያሠኛሉ ። ባጠቃላይ ግን ፥ እነዚህ ክብረ በዓሎች እንስሳቱን አስደስቷቸው ነበር ። የሆነ ሆኖ ፥ በእርግጥም የራሳቸው ጌቶች መሆናቸውንና የሚሠሩትም ሥራ ለራሳቸው ጥቅም መሆኑን እንዲያስታውሱ የመደረጉ ሁኔታ የሚያጽናና ሆኖ አግኝተውታል ። ስለዚህ ፥ መዝሙሮች ፥ የሰልፉ ክብረ በዓሎች ፥ እስኩዊለር የሚዘረዘርላቸው አኃዞች ፥ የጠመንጃው ተኩስ ማስገምገም ፥ ያውራ ዶሮው ጩኸት ፥ ምናልባት ፥ ቢያንስ ከፊሉን ጊዜ ፥ ሆዳቸው ባዶ እንደ ነበረ እንዲረሱት ረድተዋቸዋል ።

በሚያዝያ ወር ውስጥ ፥ የእንስሳት ዕርሻ ሪፑብሊክ መሆ ንዋ ታወጀና አንድ ፕሬዚዳንት እንዲመረጥ አስፈለገ ። የቀረ በው አንድ ዕጩ ብቻ ነበር ፤ ናፖሊዮን ፤ እርሱም በሙሉ ድምፅ ተመረጠ ። በዚያው ቀን እንደ ተነገረው ፥ እስኖቦል ከጆንስ ጋራ ያካኼዳቸው ስለነበሩት ሤራዎች የሚገልጽ አዳዲስ ሰነዶች ተገኝተዋል ። አሁን በተገለጸው ሁኔታ ከሆነ ፥ ካሁን ቀደም እንስሳቱ መስሎዋቸው እንደነበረው ፥ እስኖቦል «የከብት በረት ጦርነት» በእንስሳቱ ላይ ሽንፈት እንዲያስከትል ለማሤር የሞ ከረ ብቻ ሳይሆን ፥ በግልጽ ከጆንስ ወገን ሆኖ መዋጋቱ ተደርሶ በታል። በእርግጥ የሰዎቹ ጦር ኃይሎች እውነተኛው መሪ የነበ ረው እርሱ ነው ፤ የማጥቃቱን ጦርነት በጀመረበት ወቅት ያሰማው መፈክር ፥ «ለሰው ልጆች ረጅም ዕድሜ !» የሚል ነው ። በእስኖቦል ጀርባ ላይ የነበረው ፥ እስካሁንም ጥቂቶቹ እንስሳት የሚያስታውሱትን ቁስል ያደረሱበት የናፖሊዮን ጥርሶች ናቸው።

በቢጋ ወራት አጋማሽ ላይ ፥ ሞዝስ የተባለው ቁራ ፥ ለብዙ ዓመታት ተለይቶ ከቆየ በኋላ ፥ ድንገት ተመልሶ ወደ ዕርሻው

መጣ ። ፈጽሞ አልተለወጠም ፤ አሁንም ቢሆን ምንም ሥራ አይሠራም ፤ ደግሞም ስለ «ስኳር ከረሜላ ተራራ» ሲናገር እንደ ድሮው በመጨነቅ ስሜት ነው ። ባንድ ጉቶ ላይ ዐርፎ ፣ ጥቁር ክንፎቹን እያርገበገበ ፣ ለሚያዳምጡት ሁሉ ፣ ለብዙ ሰዓታት ንግግር ያደርጋል ። «ጓዶች ፣ እዚያ ላይ» ይላል ፣ አክብሮት በተሞላበት ርጋታ ፣ በትልቁ ማንቁሩ ወደ ሰማዩ እያመለከተ— «እዚያ ላይ ፣ ከዚያም ከምታዩት ጥቁር ደመና ወዲያ— «የስኳር ከረሜላ ተራራ» የሚገኘው እዚያ ነው ፤ እኛ ምስኪን እንስሳት ከድካማችን ተላቀን ለዘላለም የምናርፍበት የደስታ አገር እዚያ ነው !» እንድ ጊዜ ወደ ሰማይ መጥቶ በበረረበት ወቅት እዚያ ተገኝቶ እንደ ነበረና መጨረሻ የሌላቸው የለምለም ግጦሽ ሜዳዎች ፣ ዳር ዳራቸው ላይ በኑግ ኬክና ባንኳር ስኳር ከምር ተሞልተው ማየቱን ጭምር ይናገራል ። ከእንስሳቱ ብዙዎቹ ያምኑታል ። እንደሚያስቡት ፣ ያሁኑ ኑሮዋቸው በረሀብና በሥራ ድካም የሚሠቃይ ነው ፤ በሌላ ስፍራ የተሻለ ዓለም እንዲኖር ትክክልና ርቱዕ አይደለምን ? እንዱ ግራ የሚያጋባው ነገር ፣ ዐሣማዎቹ በሞዝስ ላይ የነበራቸው አስተያየት ነው ። ስለ «ስኳር ከረሜላ ተራራ» እርሱ የሚያወራቸው የውሸት ታሪኮች ናቸው ፣ ብለው ሁሉም ያወግዛሉ ፤ ሆኖም ግን ፣ ሳይሠራ በየቀኑ እንድ ስኒ ቢራ እየተሰጠው ፣ በዕርሻው ውስጥ እንዲኖር ፈቀደውለታል ።

ኮቴው ከዳነለት በኋላ ፣ ቦክሰር በሥራው ላይ ከመቼውም የበለጠ ጥረት ያሳያል ። በእርግጥ ፣ እንስሳቱ ሁሉ በዚያ ዓመት እንደ ባሪያዎች ነው የሠሩት ። ከመደበኛው የዕርሻ ሥራና የነፋስ ወፍጮውን መልሶ ከመገንባት ሥራ በተጨማሪ፣ በመጋቢት ወር ተጀምሮ የነበረውን ፣ ለታዳጊዎቹ ዐሣማዎች የሚሆነውን ተማሪ ቤት መሥራት ነበረባቸው ። ያለ ምግብ ለረጅም ሰዓቶች መሥራቱ አንዳንድ ጊዜ በጣም ይከብዳቸዋል ። ቦክሰር ግን ምን ጊዜም እያመነታም ፤ አይለግምም ። የእርሱ ጉልበት እንደ ድሮው እንዳልሆነ ፣ በንግግርም ሆነ በተግባር አመልክቶ አያውቅም ። ጥቂት ተለውጦ የነበረው መልኩ ብቻ ነው ፤ ቆዳው ማብረቅረቁን ከድሮው ቀንሷል ፤ እኒያ ትላልቅ ዳሌዎቹ ተኮማትረው ያነሱ ይመስላሉ ። «የቦክሰር አካል በጸደይ ወራት ይመለስለታል» ይላሉ ሌሎቹ ፤ ነገር ግን ፣ የጸደይ ወራትም መጣ ፤ ቦክሰር ግን ክብደት አልጨመረም ። አንዳንድ ጊዜ ወደ ድንጋይ

ማውጫው ጫፍ በሚወስደው አቀበት ላይ ከትላልቅ ቋጥኞች ክብደት ጋር ጉንቻዎቹ ሲታገሉ ሲታይ ፣ ለመቀጠል ያለው ፍላጎት እንጂ ፣ በእግሮቹ ለመቆም የሚያስችለው አንዳችም ጉልበት ያልነበረው ይመስላል ።

በእንደዚህ ያሉት ጊዜያት ፣ ከንፈሮቹ «በበለጠ ጥንካሬ እሠራለሁ» በማለት ሁኔታ ሲላወሱ ይታያሉ ፤ የቀረ ድምፅ አልነበረውም ። ክሎቨርና ቤንጃሚን ለጤናው እንዲጠነቀቅ አሁንም እንደ ገና መከሩት ፤ ቦክሰር ግን አልሰማቸውም ፤ አልተጠነቀቀም ። ያሥራ ሁለተኛው ዓመት የልደት ቀኑ እየተ ቃረበ ነው ። በጡረታ እስኪገለል ድረስ ፣ በቂ የድንጋይ ክም ችት እስካኖረ ድረስ፣ ምንም ነገር ቢደርስበት ግድ አልነበረውም።

በበጋው ወራት ፣ አንድ ቀን ረፋድ ምሽት ላይ ፣ ቦክሰር አንዳች አደጋ ደርሶበታል ፤ የሚል ወሬ በዕርሻው ግቢ ውስጥ ተሠራጨ ። አንድ ጋሪ ሙሉ ድንጋይ ወደ ነፋስ ወፍጮው መሥሪያ ቤታ ጐትቶ ለማድረስ ብቻውን ወጥቶ ነበር ። እውነ ትም ወሬው ርግጠኛ ኖርዋል ። ከጥቂት ደቂቃዎች በ፦ላ ርግቦቹ እንዲህ የሚል ወሬ ይዘው እየተቻኰሉ መጡ ፤ «ቦክሰር ወድ ቋል ! በጐኑ ተጋድሞ መነሣት አቅቶታል !»

በዕርሻው ግቢ ውስጥ ከነበሩት እንሰሳት ግማሾቹ ያህል ፣ የነፋስ ወፍጮው ቆሞ ወደ ነበረበት ኮረብታ ገሠገሡ ። በጋሪ መጐተቻ ጋድሚያ ዕንጨቶች መኻከል ፣ ዐንገቱን ዘርግቶ ፣ ራሱን እንኳን ማቅናት ተስኖት ፣ ቦክሰር እዚያ ተጋድሟል ። ዐይኖቹ ተጋርደዋል ፤ ጐንና ጐኖቹ በላብ ተጠምቀዋል ። አንዲት ቀጭን የደም ፍሳሽ ካፉ ፈስሳለች ። ክሎቨር ባጠገቡ ተንበረ ከከች ።

«ቦክሰር !» ብላ በመጮኽ ፣ «ምንህን ነው ?» ብላ ጠየ ቀችው ።

«ሳንባዎቼን ነው» አለ ቦክሰር ፣ በተዳከመ ድምፅ ። «ግድ የለም ። የነፋስ ወፍጮውን ሥራ ያለ እኔ ልትጨርሱት የምት ችሉ ይመስለኛል ። በቂ ድንጋይ ክምችት ተጠራቅምዋል ። ያም ሆነ ይህ ፣ ካንድ ወር በላይ አልቆይም ነበር ። እውነቱን

ለመናገር ፣ የጡረታዬን ጊዜ በናፍቆት ስጠባበቅ ነበር ። ደግሞም ቤንጃሚንም እያረጀ ስለሆነ ምናልባት ጡረታ እንዲወጣ በዚሁ ጊዜ ይፈቀድለትና ጓደኛ ይሆነኛል ።»

«አሁኑኑ ቶሎ ዕርዳታ ማግኘት አለብን ፤» አለች ክሎቨር ። «እንዳችሁ ሩ ኑና የደረሰውን ሁኔታ ለእስኩዊለር ንገሩ ።»

ሌሎቹ እንስሳት ሁሉ ለእስኩዊለር መልእክቱን ለማድረስ ወዲያው እየሮጡ ወደ መኖሪያው ቤት ኼዱ። ክሎቨር ብቻ ቀረች፤ ቤንጃሚን ደግሞ በቦክሰር አጠገብ ተጋድሞ እንዳችም ቃል ሳይተነፍስ ፣ በረጅም ጭራው ዝንቦችን ያባርርለታል ።

ከአንድ ሩብ ሰዓት በኋላ ፤ በርኅራኄና ባሳቢነት ሙሉ ስሜት ፣ እስኩዊለር ብቅ አለ ። ጓድ ናፖሌዎን ፣ በዕርሻው ክልል ውስጥ እጅግ ታማኝ ከሆኑት ሠራተኞች ባንዱ ላይ የደረሰውን ይህን አደጋ የሰማው በጥልቅ ሀዘን ስለሆነ ፣ በዊልንግዶን ከሚ ገኙት ባንድ ሆስፒታል ውስጥ እንዲታከም ቦክሰርን ለመላክ አስቀድሞ ዝግጅቶችን ያደረገ መሆኑን ተናገረ ። እንስሳቱ ሁሉ በ ዚህ ነገር ትንሽ የመጨነቅ ስሜት ዐደረባቸው ። ሞሊና እስኩ ዊለር ካልሆኑ በስተቀር ፣ ከዕርሻው ክልል ውጭ የኼደ እንስሳ አልነበረም ፤ ደግሞም የታመመው ጓዳቸው ከሰው ልጆች እጅ ውስጥ እንዲገባ የማድረጉ አሳብ ጥሩ መስሎ አልታያቸውም ። ይሁን እንጂ ፣ በዊልንግዶን የሚገኘው የእንስሳት ሐኪም ፣ ለቦክሰር እዚህ ከሚደረግለት ክብካቤ የተሻለ ሕክምና ሊያደር ግለት እንደሚችል እስኩዊለር አሳመናቸው ። ከዚያም ፣ ካንድ እኩል ሰዓት ገደማ በኋላ ፣ ቦክሰር በመጠኑ በተሻለው ጊዜ ፣ እንደምንም ተጣጥሮ በእግሮቹ ቆመና ክሎቨርና ቤንጃሚን ምቹ የገለባ ጉዝጓዝ መተኛ እዘጋጅተውለት ወደ ነበረው ጋጣ ተመ ልሶ እያነከሰ ለመኼድ ቻለ ።

ለተከታዮቹ ሁለት ቀኖች ቦክሰር በጋጣው ውስጥ ቆየ ። ዐሣማዎቹ በመታጠቢያው ቤት ውስጥ ከነበረው ትልቅ ሣጥን ውስጥ ያገኙትን ቀይማ መድኃኒት በትልቅ ጠርሙስ ልከው ነበርና ክሎቨርም በቀን ሁለት ጊዜ ከምግብ በኋላ ለቦክሰር በጋጣው ውስጥ ትሰጠው ነበር ። ማታ ማታ ቤንጃሚን ዝንቦችን ከላዩ ላይ እያባረረለት ሳለ ፣ ክሎቨርም ከጋጣው ውስጥ ከእርሱ

አጠገብ ተጋድሞ ታነጋግረዋለች ። ቦክሰር በደረሰው ሁኔታ ማዘን እንደማይገባው ያምናል። በጥሩ የዳነ እንደ ሆነ፣ለተጨማሪ ሦስት ዓመታት እንደሚኖር ያስባል ። ደግሞም ከትልቁ የግጦሽ ሣር ሜዳ ጠርዝ ላይ ሊያሳልፋቸው የሚጠባበቃቸውን የጸጥታ ቀኖች በጉጉት ይመኛል ። ያን ጊዜ ለማጥናትና እእምሮውን ለማዳበር ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ፣ ጊዜ ይኖረዋል ። ምኞቱ ፣ እርሱ እንደሚለው ፣ የተቀረውን የሕይወቱን ዘመን ለማዋል የሚፈልገው ፣ ቀሪዎቹን ሃያ ሁለት የፊደል ሆሄያት በማጥናት ይሆናል ።

ቢሆንም ፣ ቤንጃሚንና ክሎቨር ከቦክሰር አጠገብ ሊገኙ ይችሉ የነበሩት ከሥራ ሰዓት ውጭ ብቻ ነበርና ፣ እንድ የጭነት ጋሪ ሊወስደው የመጣውም እኩለ ቀን ላይ ነው ። እንስሳቱ ሁሉ በዐሣማዎች ተቆጣጣሪነት የቀይ ሥር አትክልት አረሞችን በማረም ሥራ ላይ ተሠማርተው ሳሉ ፣ ቤንጃሚን በኃይል እያናፋ ከወደ ቤቶቹ አቅጣጫ በግልቢያ ሲመጣ ተገርመው ተመለከቱ። ቤንጃሚን እንደዚያ ስሜቱ ሲቀሰቀስ ፣ በእርግጥም እንደዚያ ሲጋልብም የተመለከቱት ለመጀመሪያ ጊዜያቸው ነበር ።

«ቶሎ በሉ ፤ . . . ቶሎ ኑ !» ብሎ ጮኸ ። «ፈጥናችሁ ኑ! ቦክሰርን ይዘውት ሊኼዱ ነው!»ከዐሣማዎቹ ትእዛዝ ሳይጠብቁ ፣ እንስሳቱ ሥራቸውን ጥለው ወደ ዕርሻው ቤቶች ፈረጠጡ ። እውነትም በቅጥር ግቢው ውስጥ በሁለት ፈረሶች የሚጐተት ጐንና ጐኑ ላይ የተጻፈበትን እንድ ትልቅ ሽፍን የጭነት ጋሪ ቆሞ አዩ ፤ ከነጂው ቦታ ላይ ፣ እንድ ብልጣብልጥ መልክ ያለው ፣ ክብ ባርሜጣ ያደረገ ሰው ተቀምጦዋል ። የቦክሰር ጋጣ ደግሞ ባዶ ነው ።

እንስሳቱ በጭነት ጋሪው ዙሪያ ተሰበሰቡና «ቦክሰር ደኅና ሁን !» ብለው ባንድነት ጮኹ ፤ «ደህና ሰንብት !»

«ሞኞች ! ቂሎች !» እያለ በመጮኽ ቤንጃሚን ፣ በኮቴዎቹ መሬቱን እየመታ በእንስሳቱ ዙሪያ ይዘላል ። «ሞኞች ! በጭነት ጋሪው ጐን ላይ የተጻፈውን ለምን አትመለከቱም ?»

ይኸን ጊዜ ፣ እንስሳቱ ረጋ ብለው ይንሾካሾኩ ጀመር ። ሙርየል ፊደሎቹን እየቆጠረች ማንበብ ጀመረች ። ቤንጃሚን

ግን ፣ ወደ ጕን ገፈተራትና ጸጥታ በሰፈነበት ወቅት መኻል ፣ እንዲህ ሲል አነበበ ፤

«አልፍሬድ ሲመንድስ ፤ ፈረስ አራጅና ሙጫ ቀቃይ ፤ ዊልንግዶን ። የቆዳና ያጥንት ምግብ ነጋዴ ። የውሾች ምግብ አቅራቢ «ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ አይገባችሁም ? ቦክሰርን ወደ አራጆች እየወሰዱት ነው !»

እንስሳቱ ሁሉ የድንጋጤ ጩኸት አስተጋቡ ። በዚህ ጊዜ ጋሪ ነጅው ፈረሶቹን ባለንጋው ሾጥ አደረጋቸውና ጋሪውን በኩሩ ስግሪያ እየጐተተቱ ከገቢው ውጭ ለመኼድ አመሩ ። እንስሳቱ ሁሉ ላንቃቸው እስኪሰነጠቅ በመጮኽ ተከተሉ ። ክሎቨር እንደምንም ተጋፍታ ወደ ፊት ቀደመች ። ጋሪውም ፍጥነት ጨመረ ። ክሎቨር እነዚያ ግዙፍ እግሮችዋን ቀስቅሳ በሽምጥ ጋለበች ። «ቦክሰር !» ብላ ጮኸች ። «ቦክሰር ! ቦክሰር ! ቦክሰር !» ከውጭ የነበረውን ጩኸት የሰማ ይመስል ፣ ከግንባሩ ከላይ ጀምሮ እስከ አፍንጫው የሚወርደው ቦቅማ መሥመር የተጋደመበት የቦክሰር ፊት ከጭነት ጋሪው በስተኋላ መስኮት ታየ ።

«ቦክሰር !» ብላ በተንጫረረ ድምፅ ጮኸች ክሎቨር ። «ቦክሰር ! ውጣ ! ቶሎ ! ወደ መገደያህ እየወሰዱህ ነው !»

እንስሳቱ ሁሉ ፤ «ቦክሰር ! ቶሎ ብለህ ውጣ ! ውጣ !» የሚለውን ጩኸት አስተጋቡ ። ነገር ግን የጭነት ጋሪው ፍጥነት እየጨመረ ይከንፍ ነበርና እየራቃቸው ኼደ ። ክሎቨር ምን እንደ ነገረችው ቦክሰር ይግባው አይግባው አልታወቀም ። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፊቱ ከመስኮቱ ላይ ጠፋና በጭነት ጋሪው ውስጥ አንድ አስደንጋጭ ኳኳታ ይሰማ ጀመር ። ከዚያ ወጥቶ ለማምለጥ እየተወራጨ ሲራገጥ ነበር ። ግን ፣ ወየው ! ጕልበቱ ከዳውና ፣ የኰቴው ኳኳታ ድምፅ እየደከመ ኼደ አከተመ ። እንስሳቱ ተስፋ በመቁረጥ ጋሪውን የሚጐትቱትን ሁለት ፈረሶች እንዲቆሙ መማጠን ጀመሩ ። «ጓዶች ፣ ጓዶች !» እያሉ ጮኹ ። «የገዛ ወንድማችሁን ወደ መሞቻው አትውሰዱት !» ነገር ግን ፤ እንያ ደንቆሮቹ አውሬዎች ምን እንደሚከተል ፈጽሞ ያልተረዱ ነበሩና ጆሮዎቻቸውን ወደ ኋላ ቀስረው ርምጃቸውን

ይብስ አፋጠኑ ። የቦክሰር ፊት በመስኮቱ ተመልሶ አልታየም ። ባይዘገይ ኖሮ ፣ ከእንስሳቱ አንዱ ወደ ፊት ቀድሞ በመሮጥ ፤ የግቢውን ባለ አምስት ብረት መዝጊያ ሊዘጋ ታስቦ ነበር ፤ ግን ወዲያው የጭነት ጋሪው መዝጊያውን ዐልፎ ወጣና በጕዳናው ተሽቆልቁሎ ተሠወረ ። ቦክሰር ከዚያ በኋላ ከቶ አልታየም ።

ምንም እንኳን ላንድ ፈረስ ሊደረግለት የሚገባው ክብካቤ ሁሉ የተደረገለት ቢሆንም ፣ ከሦስት ቀን በኋላ በዊሊንግዶን ሆስፒታል መሞቱ ተነገረ ። እስኩዊለር ወሬውን ለሌሎቹ ለመ ንገር መጣ ። የቦክሰር ሕይወት ባለፈባቸው በመጨረሻዎቹ ሰዓቶች ፣ ራሱ በቦታው ተገኝቶ እንደ ነበረ ነገራቸው ።

«በሕይወቴ ካየሁት ሁሉ በላይ አሳዛኝ ትርኢት ነበር !» አለ እስኩዊለር ፤ አንድ ኮቴውን አንሥቶ እንባውን እየጠረገ ። «እስከ መጨረሻይቱ ደቂቃ ድረስ ከሞት አልጋው አጠገብ ነበርሁ ። በመጨረሻውም ፣ ለመናገር እንኳን ተስኖት ደክሞ በነበረበት ወቅት ፣ የነፋስ ወፍጮው ሥራ ከማለቁ በፊት መሞቱ ብቻ የሚያሳዝነው መሆኑን በዦሮዬ ነገረኝ ። «ጓዶች ፣ ወደ ፊት !» ብሎ አንሾካሾከልኝ ። «በሽፍትነቱ ስም ወደ ፊት ! ረጅም ዕድሜ ለእንስሳት ዕርሻ ! ረጅም ዕድሜ ለጓድ ናፖሊዮን ! ናፖሊዮን ምን ጊዜም ልክ ነው ።» በመጨረሻም የተናገረው ልክ እነዚህን ቃላት ነው ፤ ጓዶች ።»

እዚህ ላይ የእስኩዊለር ሁኔታ ድንገት ተለዋወጠ ። ለጥ ቂት ጊዜ ዝም አለና ፣ ንግግሩን ከመቀጠሉ በፊት እነዚያ ትና ንሽ ዓይኖቹ በጥርጣሬ አመለካከት ግራ ቀኝ ተንቀዠቀዡ ።

ቦክሰር በተወሰደ ጊዜ አንድ የተዛባና የሞኝነት ወሬ እንደ ተነዛ መረዳቱን ነገራቸው ። «ቦክሰርን የወሰደው የጭነት ጋሪ «የፈረሱ አራጅ» የሚል ጽሑፍ ጐኑ ላይ ተጽፎበት እንደ ነበረ አንዳንዶቹ እንስሳት ተመልክተው ነበርና እንዲያውም ወደ አራጆች እንዲወሰድ ርግጠኞች ሆነው ነበር ። ማንኛውም እንስሳ ይኸን ያህል ደንቆሮ ይሆናል ብሎ ለማመን የሚያዳግት ነው ለማለት ይቻላል ፤» አለ እስኩዊለር ። «በእርግጥ ፤» ብሎ ድንገት ጮኸና ጭራውን እየቆላ ግራና ቀኝ በመንቆራጠጥ ፤

«በእርግጥ ተወዳጁ መሪያችን ፥ ጓድ ናፖሊዎን እንዲዚህ ያለ ወራዳ ድርጊት እንደማይፈጽም መች አጣችሁትና ነው ? ነገር ግን ሁኔታውን በቀላሉ ለማስረዳት ይቻላል ። የጭነት ጋሪው ቀድሞ የአንድ አራጅ ንብረት ሲሆን ፥ የእንስሳት ሐኪሙ ከገዛው በኋላ ፥ ገና ጽሑፉን አላጠፋውምና ነው። ስሕተቱ የተከሠተው በዚህ የተነሣ ነው ።»

ይህን በሰሙ ጊዜ እንስሳቱ ከመጠን በላይ እፎይታ ተሰማቸው ። ደግሞም ቦክሰር በሞት አልጋው ላይ ስለ ተደረገለት ዝርዝር ሁኔታ ፥ ታላቅ ክብካቤና ናፖሌዎንም ስለመድኃኒቶቹ ውድነት አንዳች ቅሬታ ሳያድርበት እንዴት ያሉ ውድ መድኃኒቶች እንደ ተሰጡት በተጨማሪ በዘረዘረላቸው ጊዜ ፥ ጥርጣሬዎቻቸው ሁሉ ተወገዱና ፥ ተወዳጅ ጓዳቸው ፥ ሌላው ቢቀር ፥ ተደስቶ የሞተ መሆኑን በማወቃቸው ተጽናኑ ።

በተከታዩ እሑድ በተደረገው ስብሰባ ላይ ናፖሊዎን ራሱ ተገኝቶ ስለ ቦክሰር ሞት ክብር አንዲት አጭር ንግግር አሰማ ። ያሳዛኝ ጓዳቸውን አስከሬን አምጥቶ በዕርሻው ውስጥ ለመቅበር አልተቻለም ፥ አላቸው ፤ ነገር ግን ከዕርሻው ግቢ አትክልት ትልቅ ያበባ ጉንጉን አሠርቶ በመላክ በቦክሰር መቃብር ላይ እንዲቀመጥ ማዘዙን ገለጸላቸው ። ደግሞም ከጥቂት ቀኖች በኋላ ፥ ዐሣማዎቹ ለቦክሰር ክብር አንድ ታላቅ ግብዣ ለማዘጋጀት ያቀዱ መሆኑን ነገራቸው ። ናፖሊዎን በንግግሩ መደምደሚያ ፥ ቦክሰር አብልጦ ይወዳቸው የነበሩት ሁለቱን መፈክሮች፤ «ይበልጥ በርትቼ እሠራለሁ» እና «ጓድ ናፖሌዎን ምን ጊዜም ትክክል ነው» የተሠኙትን በማስታወስ ፥ እነዚህንም መፈክሮች እያንዳንዱ እንስሳ እንደ ግሉ በመቁጠር ሊፈጽማቸው የሚገባ መሆኑን አስገንዘባቸው ።

ግብዣው እንዲደረግ በተወሰነው ቀን ፥ ከዊልንግዶን አንድ የጭነት ጋሪ መጥቶ አንድ ትልቅ ሣጥን በመኖሪያ ቤቱ አራገፈ ። ያን ዕለት ምሽት በጩኸት የተሞላ ዘፈን ሲሰማ አመሽና በመጨረሻው ላይ የከረረ ጠብ አስከትሎ የመስታወት ስባሪ ድምፅ የመሰለ ነገር ተሰምቶ ተፈጸመ ። በማግሥቱ ከመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ከዕኩለ ቀን በፊት ማንም አልተንቀሳቀሰም ፤ ደግሞም ፥ ዐሣማዎቹ ከየት እንዳመጡት ያልታወቀ ገንዘብ አግኝ

ተው አንድ ሌላ ሣጥን ዊስኪ ለግላቸው ገዝተው እንደ ነበረ ወሬው ተዛመተ ።

## ዐ ሥ ር

ዓመታት ዐለፉ ። ወራቶቹ እየመጡ ኼዱ ፤ አጫጭሮቹ የእንስሳቱ ዕድሜዎች ነጐዱ ። ከክሎቨር ፣ ከቤንጃሚን ፣ ከቁራው ከሞዝስና ከጥቂቶቹ ዐሣማዎች በስተቀር ፣ ከሽፍትንነቱ ጊዜ በፊት የነበሩትን የድሮ ጊዜ ቀኖች የሚያስታውስ ማንም ያልነበረበት ጊዜ መጣ ።

ሙርየል ሞትዋል ፤ ብሎቤል ፣ ጄሲ እና ፒንቸር ሞተዋል ። ጆንስም ሞትዋል —በሌላው ክፍለ ሀገር፣ባንድ የሰካራሞች ቤት ውስጥ ነው የሞተው ። እስኖቦልም ተረስቷል ። ክሎቨር ባሁኑ ጊዜ ፣ መተጣጠፊያዎችዋ የደረቁና ዓይኖችዋ የተሞጫሞጩ ፣ አንዲት የገረጀፈች ግዙፍ ባዝራ ሆናለች ። የጡረታ ዕድሜዋ ካለፈ ሁለት ዓመት ሆኖታል ፤ ነገር ግን ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ እስከ ዛሬ ድረስ ጡረታ የወጣ አንድም እንስሳ አልነበረም ። የጡረታ ዕድሜያቸው ለደረሰ እንስሳት ለግጦሽ ስፍራ ይከለላል ተብሎ የነበረው ቦታ ወሬው ከተረሳ ቆይቷል ። ናፖሌዎን ባሁኑ ጊዜ አንድ መቶ አምሣ ኪሎ የሚመዝን ሙሉ ዕድሜ ያለው ግዙፍ ያሣማ ኮርማ ሆኖዋል ። እስኩዊለር በጣም ከመወፈሩ የተነሣ ዐይኖቹን እንኳን እንደ ልብ ለመግለጥ ተስኖታል ። አሮጌው ቤንጃሚን ብቻ ወደ አፍና አፍንጫው አካባቢ ይልቅ ነጣ ከማለቱ በስተቀር ከቀድሞው አልተለወጠም ፤ ደግሞም ፣ በክስር ከሞተ ጊዜ ጀምሮ ፣ ከመቼውም ይልቅ ዝምተኛና አይጠዴ (አኩራፊ) ሆኖዋል ።

ምንም እንኳን ፣ በፊተኞቹ ዓመታት ተጠብቆ የነበረውን ያህል ብዙ ባይሆንም ፣ ባሁኑ ጊዜ በዕርሻው ቦታ ላይ በርካታ ፍጡሮች ነበሩ ። ብዙ እንስሳት ተወልደዋል ፤ እነዚህም ሽፍትነቱን ባፈ ታሪክ ብቻ የሰሙ ሲሆኑ ፣ ሌሎች የተገዙት ደግሞ እዚህ ቦታ ከመምጣታቸው በፊት እንዲህ ያለ ነገር ሰምተው የማያውቁ ነበሩ ። ዕርሻው ባሁኑ ጊዜ ፣ ከክሎቨር በተጨማሪ ፣ ሦስት ፈረሶች ነበሩት ። ጥሩ ቁመና የነበራቸው እንስሳት ፤ ሥራ ወዳዶችና ጥሩ ጓዶች ቢሆኑም ፣ በጣም ደንቆሮዎች ነበሩ ።

ማንኛቸውም ከ «ለ» ወዲያ ፊደላቱን ለመማር አልቻሉም ። ስለ ሽፍትነቱና ስለ እንስሳዊነት የተነገራቸውን ሁሉ ፣ በተለይም ፣ እንደ እናታቸው ይቈጥሩዋት ከነበረችው ከክሎቨር የተነገራቸውን ፣ አሜን ብለው ይቀበላሉ ፤ ነገር ግን ፍቺው ምን እንደ ሆነ አጣርተው ማወቃቸው ያጠራጥራል ።

ዕርሻው አሁን ይበልጥ የበለጸገና በተሻለ ሁኔታ የተደራጀ ሆንዋል ፤ ከሚስተር ፒልኪንተን በተገዙ ሁለት የዕርሻ ማሳዎች ጭምር ተስፋፍቷል ። ከዚያ ሁሉ ድካም በኋላ ፣ የነፋስ ወፍጮው ሥራ በደኅና ሊጠናቀቅ ቻለና ዕርሻው አሁን ፣ ያንድ መውቂያ መኪናና ያንድ የድርቆሽ ማንሻ ባለቤት ሆነ ፤ ደግሞም ሌላ ልዩ ልዩ አዳዲስ ቤቶች ተጨምረውለታል ። ዊምፐር እንድ የቅንጦት ጋሪ ለግሉ ገዛ ። ይሁን እንጂ የነፋሱ ወፍጮው እንደ ታሰበው ለኤሌክትሪክ ማመንጫነት አላገለገለም ። የበቆሎ ዱቄት በመፍጨት ጥሩ ትርፍ ያስገኝ ጀመር ። አሁንም ሌላ ተጨማሪ የነፋስ ወፍጮ በመሥራት እንስሳቱ በብርቱ እየደከሙ ነበር ፤ እንደሚባለው ፣ ያ ሲያልቅ ዲናሞዎቹ ይተከላሉ ። ነገር ግን ፣ ያኔ እንስሳቱ እንዲያልሙ እስኖቦል አስተምሮዋቸው የነበሩት ድሎቶች — በየጋጣው የኤሌክትሪክ ብርሃንና ሙቅና ቀዝቃዛ ውኃ ፣ ደግሞም በሳምንት ሦስት ቀን የዕረፍት ጊዜ የተባለው ሁሉ ከነወሬውም ቀርቷል ። ይኸን የመሳሰሉት አስተሳሰቦች ከእንስሳዊነት መንፈስ ጋር የሚቃረኑ ናቸው በማለት ናፖሌዎን አውግዞታል ። እርሱ እንደሚለው ፣ እውነተኛው ደስታ የተመሠረተው ጠንክሮ በመሥራትና በኑሮ ቁጥብነት ላይ ነው ።

በእርግጥ ፣— ለዐሣማዎቹና ለውሾቹ ካልሆነ በስተቀር ፣ እንስሳቱን ራሳቸውን ይበልጥ ባለጸጎች ባያደርጋቸውም — ዕርሻው እንደ ምንም ይበልጥ የበለጸገ ይመስላል ። ይህ የሆነበትም አንዱ ምክንያት ፣ ምናልባትም ያን ያህል በርካታ ዐሣማዎችና ውሾች ስለ ነበሩ ይሆናል ። የራሳቸው የሆነ ያሠራር ፈሊጥ አልነበራቸውም ለማለት አይደለም ። እስኩዊለር ምን ጊዜም ሳይታክት እንደሚያስረዳው ሁሉ ፣ የዕርሻውን ሥራ በመቆጣጠርና በማደራጀት ረገድ ማለቂያ የሌለው ሥራ አለባቸው ። ይኸንንም ሥራ አብዛኛውን ክፍል ሌሎች እንስሳት ሊሠሩ በቂ ዕውቀት የላቸውም ። እስኩዊለር ሲያስረዳቸው ፣

ለምሳሌ «ፋይሎች» ፣ «ዘገባዎች» ፣ «ቃለ ጉባዔዎች» ፣ «ማስታወሻዎች» የተባሉትን ምስጢራዊ ነገሮችን በማዘጋጀት ዐማማዎቹ በየቀኑ ለአያሌ ሰዓቶች በመሥራት ይደክማሉ ። እነዚህም ነገሮች በሰፋፊ ሉክ ወረቀቶች ላይ ጥቅጥቅ ተደርገው ከተጻፉ በኋላ ፣ ወዲያው እቶን ክምር ውስጥ ተጨምረው ይቃጠላሉ ። «ይህም ፣» ይላል እስኩዊለር ሲያስረዳቸው ፣ «ለዕርሻ ተቋሙ ደኅንነት እጅግ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ነው ።» ነገር ግን ፣ አሁንም ቢሆን ዐሣማዎቹም ሆኑ ውሾቹ በሥራቸው አንዳችም ምግብ አያመርቱም ነበር ፤ ቍጥራቸው ግን በጣም የላቀ ነው ፤ የምግብ ፍላጎታቸውም ምን ጊዜም ጥሩ ነው ።

ለሌሎቹ እንደ ሆነ ፣ ኑሮዋቸው ፣ እነሱ እንደሚያውቁት ፣ ሠርክ እንደ ነበረው ነው ። ሁል ጊዜ ይራባሉ ፤ በገለባ ላይ ይተኛሉ ፤ ከኩሬው ውኃ ይጠጣሉ ፤ በዕርሻ ማሳዎች ይሠራሉ ፤ በክረምት ወራት ብርዱ ፣ በበጋ ወራት ዝንቦቹ ያስቸግሩዋቸዋል ። ከመካከላቸው ሽምግል ያሉት ፣ አንዳንድ ጊዜ ፣ ያኔ ገና በሽፍትነቱ ቀኖች እቅራቢያ ሰሞን ፣ ከጆንስ መወገድ ቅርብ ጊዜ በኋላ ፣ ኑሮዋቸው ምን ይመስል እንደ ነበረ ለማስታወስ የደበዘዘ አእምሮዋቸውን ያስጨንቃሉ ። ሊያስታውሱ አይችሉም ። ያሁኑን ኑሮዋቸውን ሊያነፃፅሩበት የሚችሉበት ምንም ነገር አልነበረም ፤ ሁሉም ነገር ከዕለት ወደ ዕለት እየተሻሻለ የሚመጣ መሆኑን ፣ ያሳንዳች ጥርጣሬ ያመለክቱ ከነበሩት የእስኩዊለር አኃዞች በስተቀር ፣ ሌላ የሚያነፃፅሩበት ነገር አልነበረም ። እንስሳቱ ችግሩ የማይፈታ ሆኖ አገኙት ፤ በማንኛውም ረገድ ፣ ባሁኑ ጊዜ ፣ ይኸን መሳዩን ጉዳይ ለማመዛዘን ጊዜ አልነበራቸውም ። የረጅም ዕድሜውን ኑሮ ዝርዝር ሁኔታዎች ሊያስታውሱና ሊያረጋግጥ የሚችለው አሮጌው ቤንጃሚን ብቻ ነበር ፤ እርሱ እንደሚለው ፣ ሁኔታዎች መቼም መች እየተሻሻሉ አልኼዱም ፤ አይኼዱምም — ረሀብ ፣ ችግርና ሀዘን ፣ እንደ እርሱ አባባል ፣ የማይለወጥ የኑሮ ሕግ ነውና ።

ይኸም ሁሉ ሆኖ ፣ እንስሳቱ ምን ጊዜም ተስፋ አልቆረጡም ። ከዚህም በላይ ፣ የእንስሳቱ ዕርሻ አባላት የመሆናቸውን የክብርና የልዩ መብት ስሜታቸውን ላንድ አፍታ እንኳን አላጡም ። በመላው አገር—በመላው እንግልጣር :— የእንስሳት

ንብረት የሆነውና በእንስሳት የሚመራው ዕርሻ የእነርሱ ብቻ ነው ።

ከእነርሱ አንዳቸውም ፣ በዕድሜ አነስተኞቹም ቢሆኑ ፣ ካሥርና ከሃያ ማይልስ ከሚርቁ ዕርሻዎች የተገዙት አዲስ መጤ ዎቹም ቢሆኑ ፣ ይኸን ነገር ያደንቃሉ ። ደግሞም ጠመንጃው ሲተኮስ ሲሰሙ ፣ አረንጓዴው ዓላማ በሰንደቁ ጫፍ ላይ ሲው ለበለብ ሲመለከቱ ልባቸው በማይሞት ኩራት መንፈስ ያብ ጣል ። የንግግሩ አርእስት ፣ ሁልጊም ወደ ድሮው የጀግንነት ወኔ ፣ ጆንስ ወደ ተባረረበት ጊዜ ፣ ሰባቱ ትእዛዛት ወደ ተጻፉ በት ጊዜ ፣ ወራሪዎቹ የሰው ልጆች ወደ ተሸነፉበት ጊዜ ይለ ወጣል ።

ከድሮ ሕልሞች አንድም የተረሳ አልነበረም ። አስቀድሞ እስኖቦል የተነበየው ፣ በሰው ዘር የማይረገጡት የእንግሊዝ አገር አረንጓዴ መስኮች በሚኖሩበት ጊዜ የሚቋቋመው የእን ሰሳት ሪፑብሊክ እንደሚቋቋም አሁንም እየታመነበት ነበር ። አንድ ቀን መድረሱ አይቀርም ፤ በቶሎ ላይሆን ይችላል ፤ አሁን ባሉት እንስሳት ዕድሜ ላይሆን ይችላል ፤ ግን መድረሱ የማ ይቀር ነው ። «የእንግሊዝ እንስሳት ሆይ» የተሠኘው ጣዕመ ዜማ እንኳን በድብቅ እዚህና እዚያ ሳያንጐራጉሩት አልቀረም ይሆናል ፤ ያም ሆነ ይህ ፣ ምንም እንኳን ጮክ ብሎ ለመዘመር ማንም ባይደፍርም ፣ ሁሉም ያውቁት እንደ ነበር እሙን ነው ። ኑሮዋቸው የችግር ኑሮ የነበረና ተስፋዎቻቸው ሁሉ አልተፈ ጸሙላቸው ይሆን ይሆናል ፤ ነገር ግን እንደ ሌሎቹ እንስሳት እንዳልነበሩ ይረዳሉ ። ቢራቡም ፣ ጨቋኞቹን የሰው ልጆች በመመገባቸው ምክንያት አልነበረም ፤ በሥራ ቢደክሙም ፣ ሌላው ቢቀር ፣ የሚሠሩት ለራሳቸው ነበር ። ከመካከላቸው በሁለት እግሮቹ የሚኼድ ፍጡር የለም ። ማንም ፍጡር ሌላ ውን ፍጡር «ጌታ» ብሎ የሚጠራ የለም ። እንስሳት ሁሉ እኩል ነበሩ ።

አንድ ቀን ፣ በበጋው ወራት መጀመሪያ ሰሞን ፣ እስኩ ዊለር በጎቹ እንዲከተሉት አዘዛቸውና ከዕርሻው ቦታ ራቅ ወዳለ፣ አንድ የልምጭ ዛፎች ጫካ ውስጥ ወሰዳቸው ። በጎቹ ሙሉውን ቀን በእስኩዊለር ተቈጣጣሪነት ሣር ሲግጡ ዋሉ ። ማታ ራሱ

ወደ መኖሪያው ቤት ተመልሶ መጣ ፤ ነገር ግን ፣ ጊዜው ሞቃት ስለ ነበረ ፣ በጎቹ እዚያው ሰነበቱና በዚህ ጊዜ ውስጥ ሌሎቹ እንሰሳት እንዳቸውንም አላይዋቸውም ። በየቀኑ እስኩዊለር አብዛኛውን ጊዜ ከእነርሱ ጋራ ሲያሳልፍ ሰነበተ ። እርሱ እንደ ተናገረው ፣ ግለኛነት የሚያስፈልገው አንድ አዲስ መዝሙር እያስተማራቸው ነበር ።

በጎቹ ልክ ከተመለሱ በኋላ ነበር ፣ አንድ የደስደስ በነበ ረው ምሽት ፣ እንሰሳቱ ሥራቸውን ጨርሰው ወደ ዕርሻው ቤቶች ሲመለሱ ሳሉ ፣ ከወደ ምድረ ግቢው በኩል የአንድ ፈረስ አሸባሪ ጩኸት የሰሙት ። የክሎቨር ድምፅ ነበር ። እንደ ገና ጮኸችና እንሰሳቱ ሁሉ በግልቢያ ወደ ግቢው ፈረጠጡ ። ከዚያ ክሎቨር ያየችውን ጉድ ተመለከቱ ።

በኋላ እግሮቹ የሚራመድ አንድ ዐሣማ ነበር ።

አዎን ፣ እስኩዊለር ነበር ። በዚያ አቋቋም ያን በጣም ትልቅ ክብደቱን መሸከም ያቃተው ይመስል ፣ ትንሽ በመታ ወክ ሁኔታ ፣ ዳሩ ግን ሚዛኑን በትክክል ጠብቆ ፣ ግቢው ውስጥ ሲንሸራሸር ነበር ። ደግሞ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዐሣማዎች መንጋ ባንድ ረድፍ ተቀጣጥለው በኋላ እግሮቻቸው እየተረማመዱ ከመኖሪያ ቤቱ በር ተግተልትለው ወጡ ። ጥቂቶቹ ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ ይራመዳሉ ፤ አንድ ሁለቱ ትንሽ ይንገዳገዳሉ ፤ እንዲያውም ምርኩዝ የሚያስፈልጋቸው ይመስሉ ነበር ፤ ነገር ግን ሁሉም በተሳካ ሁኔታ በምድረ ግቢው ዙሪያ ዞሩ ። በመ ጨረሻም ኃይለኛ የውሾች ጩኸት ድምፅና የጥቁሩ አውራ ዶሮ ቀጭን ጩኸት ተሰማና ናፖሌዎን ራሱ ፣ በግርማ ሞገስ ቀጥ ብሎ እየተራመደ በኩራት አመለካከት ግራና ቀኝ እየተገላመ ጠና ዙሪያውን በውሾቹ ታጅቦ መጣ ።

በኮቴው አንድ አለንጋ ይዞዋል ።

የሞት ያህል ጸጥታ ሰፈነ ። ዐሣማዎቹ በግቢው ውስጥ ዝግ ብለው እየተራመዱ በሰልፍ ሲዘዋወሩ እንሰሳቱ ተገርመው፣ ደንግጠው ፣ ሰብሰብ ብለው ይመለከቱ ነበር ። ዓለም የተገለባበ ጠች ይመስላል ። ከዚያም ፣ የመጀመሪያው ድንጋጤ ካለፈና

ከዚያ ሁሉ በኋላ — ምንም እንኳን የውሾቹ ፍራቻ የነበረ ቢሆንም ምንም ነገር ቢመጣ ከቶ ላለመነጫነጭ ፣ ላለመንቀፍ ከረዥም ዓመታት ጀምሮ የተለመደውን — የተቃውሞ ድምፅ ሊያሰሙ ነበር ። ነገር ግን ልክ በዚያች ወቅት ፣ አንድ ምልክት የተሰጠ ይመስል ፣ በጎቹ ሁሉ ፣—

«አራት እግሮች ጥሩ ፣ ሁለት እግሮች የተሻሉ! «አራት እግሮች ጥሩ ፣ ሁለት እግሮች የተሻሉ! «አራት እግሮች ጥሩ ፣ ሁለት እግሮች የተሻሉ!» እያሉ ድንገት በመጮኽ አምባረቁ ።

ጩኸቱ ያለ ማቋረጥ ላምስት ደቂቃ ያህል ቀጠለ ። እና በጎቹ ጸጥ እስካሉ ድረስ ፣ ዐሣማዎቹ ተመልሰው ወደ መኖሪያ ቤቱ ውስጥ ተሰልፈው ገብተው ስለ ነበረ ፣ እንዳችም የተቃውሞ ድምፅ ለማሰማት አልቻሉም ።

ቤንጃሚን ትከሻው ላይ ባፍንጫ ሲታከክ ተሰማውና ዞር አለ ። ክሎቨር ነበረች ። ያረጁት ዐይኖችዋ ከመቼውም ይልቅ ጨልመዋል ። እንዳችም ቃል ሳትናገር ቀስ ብላ በጋማው ይዛ ፣ ሰባቱ ትእዛዛት ተጽፈውበት ወደ ነበረው ወደ ትልቁ መጋዘን መጨረሻ ግድግዳ እንዲያመራ ጐተተችው ። በነጭ ቀለም ፊደሎች የተጻፉበትን ግድግዳ ላንድ ሁለት ደቂቃ እየተመለከቱ በዝምታ ቆዩ ።

በመጨረሻም «እይታው እየከዳኝ ነው ፣» አለች ። «ልጅ በነበርኩበትም ጊዜ እዚያ ላይ የተጻፈውን ማንበብ አልችልም ነበር ። ግን ይኸ ግድግዳ የተለወጠ መስሎ ይታየኛል ። ሰባቱ ትእዛዛት እንዳሉ ናቸው ወይ ፣ ቤንጃሚን?» ቤንጃሚን ለመጀመሪያ ጊዜ የገዛ ራሱን ደንብ ለመጣስ ወሰነና ፣ በግድግዳው ላይ ተጽፎ የነበረውን አነበበላት ። ባሁኑ ጊዜ ካንድ ትእዛዝ በስተቀር እዚያ ቦታ ላይ ሌላ ጽሑፍ አልነበረም ። እንዲህ ይነበባል ፤

«እንስሳት ሁሉ እኩል ናቸው ፤
ግን አንዳንድ እንስሳት ከሌሎቹ ይበልጥ እኩል ናቸው ።»

ከዚያ በኋላ በማግሥቱ ፣ ሥራውን የሚቆጣጠሩት ዐሣማዎች ሁሉ በኮቴያቸው አለንጋዎች ይዘው በወጡ ጊዜ ፣ እንግዳ

ነገር መስሎ አልታየም ። አንድ ራድዮን ለግላቸው እንደገዙ ፣ የስልክ መስመር ለማስገባት ማቀዳቸውን ፣ እነ ጆን ቤል ፣ ቲት ቢትስ ፣ እና ዴሊ ሚረርስ ለተሠኙት ጋዜጦች ደንበኝነት መመዝገባቸው በተሰማ ጊዜ ፣ እንግዳ ነገር መስሎ አልታየም ። ናፖሌዎን በመኖሪያ ቤቱ ግቢ አትክልት ውስጥ አንድ ፒፓ ጐርሶ ሲንሸራሸር በታየ ጊዜ ፣— የለም ፣ እንዲያውም ዐሣማ ዎቹ የሚስተር ጆንሰን ልብሶች ከየቁም ሣጥኖቹ እያወጡ ሲለ ብሱ ፣ ናፖሌዎን ራሱም የግብዣ ልብስ ለብሶና ኮፍ ጫማ ተጫ ምቶ ፣ የሚወዳት ወጣቷ ዐሣማም ፣ ወይዘሮ ጆንስ እሑድ እሑድ ትለብሰው የነበረውን አረንጓዴ የሐር ቀሚስ ለብሳ በታየችበ ትም ጊዜ ቢሆን ፣ እንግዳ ነገር መስሎ አልታየም ።

ካንድ ሳምንት በኋላ ፣ በርካታ የቅንጦት መጓጓዣ ጋሪዎች ወደ ዕርሻው ቦታ መጡ ። የጐረቤት ዕርሻዎች ተወካዮች ጉብ ኝት እንዲያደርጉ ተጋብዘው ነበር ። የዕርሻውን ተቋም በሙሉ እየተዘዋወሩ እንዲያዩ ተደረገና ስላዩዋቸው ነገሮች ሁሉ ታላቅ አድናቆታቸውን ገለጹ ፤ በተለይም ስለ ነፋስ ወፍጮው ።

እንስሳቱ የቀይ ሥር አትክልቱን ዕርሻ ቦታ እያረሙ ነበር ። በጥንቃቄ እየሠሩ ፣ ቀና ብለው እንኳን ሳይመለከቱ ፣ ዐሣማዎ ችን ይሁን ወይስ ሰብአዊ ፍጡሮችን የትኞቹን ይበልጥ እንደ ፈሩ አይታወቅም ።

ያን ዕለት ማታ ከፍተኛ የሣቅና የተደጋገመ የዘፈን ጩኸት ከወደ መኖሪያ ቤቱ በኩል ሲሰማ ነበር ። ከዚያ በኋላ ድንገት የተዘበራረቁ ድምፆች በሰሙ ጊዜ ፣ እንስሳቱ ምን እንደ ሆነ የማወቅ ጉጉት ዐደረባቸው ። እንስሳቱና የሰው ልጆች በእኩል ነት ደረጃ በመተያየት ላይ ባሉበት ባሁኑ ወቅት ፣ ምን ተፈጥሮ ይሆን? ሁሉም ባንድ ጊዜ የተስማሙ ይመስል ፣ በተቻለ መጠን ቀስ ብለው ፣ ኮሽታ ሳያሰሙ ፣ እየዳሁ ወደ መኖሪያ ቤቱ ግቢ አመሩ ።

ከቅጥር ግቢው በር ላይ ሲደርሱ ፣ ፈርተው እንደ ማመን ታት ቆም አሉ ፤ ግን ክሎቨር ደፍራ በመግባት መራቻቸው ። እስከ መኖሪያ ቤቱ ድረስ በእግር ጣቶቻቸው እየተራመዱ ሹክክ ብለው ተጠጉና ፣ ረዘም ያሉት እንስሳት በምግብ ቤቱ መስኮት

ወደ ውስጥ እያጨለጉ ተመለከቱ ። እዚያ ውስጥ በረዥሙ ጠረጴዛ ዙሪያ ግማሽ ደርዘን ገበሬዎችና ግማሽ ደርዘን ከዐሣማ ዎቹ ምርጥ ምርጦቹ ከበው ተቀምጠዋል ፤ ናፖሌዎን ራሱ የክ ብር ቦታውን ይዟል ። ዐሣማዎቹ በየወንበሮቻቸው ላይ ተደላ ድለው ተቀምጠዋል ፤ ፍጹም የደላቸው ይመስላሉ ። በዚያ ተሰብስበው የነበሩት በካርታ ጨዋታ እየተዝናኑ ኖሮ ፥ «ለጤ ናችን» ለመጠጣት ጨዋታውን ቆም አድርገው ነበር ። ባንድ ትልቅ ማብረጃ እየታደለ ኩባያዎቻቸው በቢራ እየተሞሉ ናቸው ። በመስኮቱ እያጨለጉ ይመለከቱ የነበሩትን እንስሳት ማንም ልብ ያደረገ አልነበረም ።

ከፎክስውድ የመጣው ሚስተር ፐልኪግተን ኩባያውን እንደ ጨበጠ ቆሞ ይታያል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፥ ተጋባዦች ሁሉ «ለጤናችን» እንዲጠጡ የሚጠይቃቸው መሆኑን ገለጸ ላቸው ። ይህን ከማድረጉ በፊት ግን ፥ አጭር ንግግር ለማድረግ ስሜቱ እንዳነሣሣው ነገራቸው ።

«ለረጅም ጊዜ በመካከላችን ዐድሮ የነበረው የእርስ በርስ አለመተማመንና አለመግባባት መንፈስ ባሁኑ ጊዜ ያከተመ መሆኑ ስለ ተሰማኝ ፥ ይህ ለእኔ — ደግሞም ፥ እርግጠኛ ነኝ እዚህ ለምትገኙት ለሌሎቻችሁም ሁሉ — ያንድ ትልቅ ርካታ ምንጭ ነው ።

«ያኔ ፥ ምንም እንኳን እኔም ሆንኩ እዚህ የምትገኙት ሁሉ የምናምንበት አስተሳሰብ ባይሆንም ፥ የተከበሩት የእንስሳት ዕርሻ ባለቤቶች ባጐራባች ዕርሻዎች ባለቤቶች ዘንድ — እንደ ጠላትነት ለማለት አልደፍርም—በጥርጣሬና በፍርሀት ዐይን ይታዩ በነበረበት ጊዜ ነበር ። አሳዛኝ ድርጊቶች ተፈጽመዋል፤ የተሳሳቱ አስተያየቶች ተሠንዝረዋል ። የዐሣማዎቹ ንብረት የሆነና በዐሣማዎች የሚካኼድ አንድ የዕርሻ ተቋም መኖር እንግዳ ነገር ሆኖ ስለታየና ውሎ ሲያድር ላጐራባች ዕርሻዎች ያለመረጋጋት ጠንቅ ሊያስከትል እንደሚችል ተፈርቶ ነበር ። ብዙዎቹ ገበሬዎች ተገቢ ምርምር ሳያደርጉ ፥ በዚህ መሳዩ የዕ ርሻ ተቋም የብልግናና የሥርዓተ አልባነት መንፈስ እንደሚ ያይል ገምተው ነበር ። በእንስሳዎቻቸው ላይ ፥ ወይ እንዲያውም በዙዎች ሠራተኞቻቸው ላይ ስለሚያሳድረው ተጽዕኖ ሥጋት

አሳድሮባቸው ነበር ። ግን አሁን ይህን የመሳሰሉት ጥርጣሬዎች ሁሉ ተወግደዋል ። ዛሬ እኔና እናንተ ወንድሞቼ የእንስሳትን ዕርሻ ተቋም ጐብኝተን እያንዳንዱን ስንዝር መሬት ተዘዋውረን በገዛ ዐይናችን ተመልክተናል ። ምንድን ነው ያገኘነው፣ እጅግ ዘመናዊ የሆኑ የአሠራር ዘዴዎች ብቻ ሳይሆን ፣ ለአገሪቱ ገበሬዎች ሁሉ እንደ አንድ ምሳሌ መሆን ያለበት ዲሲፕሊንና ሥርዓታዊነት ነው ። በእንስሳቱ ዕርሻ ተቋም ውስጥ የሚገኙት ዝቅተኞቹ እንስሳት ፣ በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት እንስሳት ሁሉ የበለጠ ሥራ እንደሚሠሩና ያነሰ ምግብ እንደሚሰጣቸው የማምን መሆኔን በእውነት እገልጽላችኋለሁ ። በእርግጥ ፣ እኔም ሆንኩ ዛሬ የዕርሻ ተቋሙን አብራችሁኝ የጐበኛችሁት ጓዶቼ በየዕርሻዎቻችን ሳይውል ሳያድር በሥራ ላይ ልናውላቸው የተመኘናቸው ብዙ ያሠራር ስልቶችን ተመልክተናል ።

«ንግግሬን ከማጠቃለሌ በፊት» አለ ፤ «ደግሜ ለማሳሰብ የምፈልገው ፣ በእንስሳት ዕርሻ ተቋምና ባጐራባቾቹ መካከል የኖረውና ወደፊትም ሊቀጥል ስለሚገባው የወዳጅነት ስሜት ነው ። ባሣማዎችና በሰው ልጆች መካከል እንዳችም የጥቅም ግጭት አልነበረም ፤ ሊኖርም አያስፈልግም ። ትግሎቻችንና ችግሮቻችን አንድ ናቸው ። የሠራተኛ ጉዳይ ችግር በየትም ያው አልነበረምን?» ከዚህ ላይ ሚስተር ፒልኪንግተን አንድ በጥንቃቄ ያዘጋጀውን አሽሙር የተቀላቀለበት አሥቂኝ ነገር በዚያ ለተሰበሰቡት ተጋባዦች ሊነግራቸው እንደፈለገ ግልጽ ነበር ፤ ነገር ግን ቃሉን ከመናገሩ በፊት የደስታ ስሜት ላንድ አፍታ ገታው ። ድርብርብ አገጮቹ ወደ ሐምራዊነት እስኪለወጡ ድረስ ብዙ ከተናነቀው በኋላ ፣ ነገሩን ለመናገር ቻለና እንዲህ አለ ፤

«እናንተ ከዝቅተኞቹ እንስሳት ጋር መታገል እንዳለባችሁ ሁሉ ፣ እኛም ዝቅተኛ መደቦች አሉብን!» ይህ ጥሩ አባባል በገበታው ዙሪያ የነበሩትን ሁሉ በሣቅ አስጓራቸው ፤ ሚስተር ፒልኪንግተንም ፣ በእንስሳት እርሻ ስለተመለከተው የመቁነን አነስተኛነት ፣ የሥራ ሰዓቶች መብዛትና ፣ ባጠቃላይ የመንደላቀቅ አልባነት ሁኔታ የምሥራቹን እንደ ገና ለዐሣማዎቹ አቀረበላቸው ።

«አሁን ደግሞ» አለ በመጨረሻ «ሁላችሁም ተነሥታችሁ እንድትቆሙና ዋንጫዎቻችሁ ሙሉ መሆናችሁን እድታረጋግጡ እጠይቃለሁ ። ክቡራን ሆይ» አለ ሚስተር ዊልክንግተን ሲደመድም ፣ «ክቡራን ሆይ ፣ ለእንስሳት ዕርሻ ብልጽግና ዋንጫችንን እንድናነሣ እጠይቃለሁ!»

ከፍተኛ የደስታ ውካታና የእግር ድምድምታ እሰሙ ። ናፖሊዮን በጣም ከመደሰቱ የተነሣ ፣ ዋንጫውን ከመጨለጡ በፊት ፣ ከሚስተር ፒልኪንግተን ጋር ለማጋጨት ተንደርድሮ ጠረጴዛውን ዞሮ መጣ ። የደስታው ውካታ ጋብ ባለ ጊዜ ፣ እንደ ቆመ ቀርቶ የነበረው ናፖሊዮን ፣ እርሱም አንድ አጭር ንግግር ለማድረግ መፈለጉን አስታወቀ ።

ንግግሩም ፣ እንደ ወትሮዎቹ የናፖሊዮን ንግግሮች ሁሉ ፣ አጭርና ፍሬ ነገሩን ያልሳተ ነበር ። «እኔም በበኩሌ» አለ ። «ያለ መግባባቱ ጊዜ ስለተፈጸመ ደስ ብሎኛል ። ለረጅም ጊዜ ወሬዎች ተነዝተው ነበር—የተነዙትም ፣ እኔ እንደማምነው ፣ ባንዳንድ ተንኮለኛ ጠላቶች ነው—በራሴና በጓደኞቼ በኩል የተጸነሰ አንዳች የተቃውሞና እንዲያውም የማመፅ አስተሳሰብ አዝማሚያ እንዳለ ተወርቶ ነበር ። በአጐራባች እንስሳት መካከል ሽፍትነት እንዲቀሰቀስ ለመሞከር የተፈጠሩ ነበሩ ። ከዚህ የበለጠ ከእውነት የራቀ ነገር ሊኖር አይችልም! የእኛ ፍላጐት አሁንም ሆነ ባለፉት ጊዜያት ፣ ከጐረቤቶቻችን ጋር በሰላምና በተገቢው የንግድ ግንኙነት መኖር ብቻ ነው ። ይህ ፣ እኔ የምመራው በመሆኔ የምከራበት ፣ የዕርሻ ተቋም ነው ። በእኔ እጅ የሚገኙት የባለቤትነት ካርታዎች ፣ የዐሣማዎቹ የጋራ ንብረት ናቸው ።

«የቀድሞው የጥርጣሬ መንፈስ አሁንም እያንዣበበ አለ ፣ ብዬ አላምንም» አለ «ዳሩ ግን ፣ ከዚህም በበለጠ እምነት የማሳደር ውጤት ሊኖራቸው የሚችሉ በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንዳንድ የቀድሞ ድርጊት ለውጦች ተደርገዋል ። እስካሁን ድረስ እንስሳቱ «ጓድ» በሚል የሞኝ ቅጽል እርስ በርሳቸው የመጠራራት ልማድ ነበራቸው ። ይህ ልማድ መቅረት አለበት ። ደግሞም አንድ እጅግ እንግዳ የሆነ ልማድ ጭምር ነበረ ፤ ይኸም ልማድ ከየት እንደመነጨ የማይታወቅ ሊሆን ፣ በየእሑድ ጠዋት በአት

ክልቱ ውስጥ ባንድ መሰሶ ላይ በተቸነከረ ባንድ የዐሣማ ኮርማ ራስ ቅል ፊት ለፊት ተሰልፎ የማለፍ ልማድ ነበር።ይኸም ጭምር ይቀራል ፤ የራስ ቅሉም ተቀብሯል ። እንግዶቹ በሰንደቁ አናት ላይ የሚውለበለበውን አረንጓዴ ዓላማ ጭምር ሳትመለከቱ አልቀራችሁም ይሆናል ። ተመልክታችሁት እንደ ሆነ ፣ ቀድሞ በላዩ ላይ በነጭ ቀለም ተመልክተው የነበሩት የኰቴና የቀንድ ምስሎች አሁን ተነሥተዋል ። ከእንግዲህ ወዲያ ዓላማው ባለ አረንጓዴ ቀለም ብቻ ይሆናል ።

ሚስተር ፒልንግተን ካደረጉት ፣ እጅግ ጥዑምና የመልካም ጕርብትና ንግግር አንድ ትችት ብቻ ነው ያለኝ» አለና ንግግሩን በመቀጠል ፣ «በንግግራቸው ሁሉ መኻል ሚስተር ፒልንግተን ሲጠቅሱ «የእንስሳት ዕርሻ» በሚል ስያሜ ነው ። በእርግጥም እርሳቸው ሊያውቁ አይችሉም—ያ «እንስሳት ዕርሻ» የሚለው መጠሪያ ስም የተለወጠ መሆኑን እኔ ራሴ ለመጀመሪያ ጊዜ የማስታውቀው አሁን ብቻ ነው ። ከእንግዲህ ወዲያ የዕርሻ ተቋሙ የሚጠራበት ስም—እኔ እንደማምነው ትክክለኛውና የመጀመሪያ ስሙ በነበረው «የማኖር ዕርሻ ተቋም» በሚል ስያሜ ይሆናል ።

« ክቡራን ሆይ ፡ » አለ ፣ ናፖሊዎን ንግግሩን ሲደመድም ። « እንደ ቅድሙ ለመልካም ምኞታችን መግለጫ እንድንሰጥ ስጠይቅ ፣ በተለየ ቅርፅ ነው ። ዋንጫዎቻችሁን ጢም አረጋችሁ እስከ አፋቸው ሙሉዋቸው ። ክቡራን ሆይ ፣ እነሆ የእኔ መልካም ምኞት ፣ ለማኖር ዕርሻ ተቋም ብልጽግና ! »

እንደ ቅድሙ አሁንም የደስታ ውካታ ተሰማና ዋንጫዎቹ እስከ መጨረሻው ጭላጭ ባንድ ትንፋሽ ተጋቡ ። ነገር ግን ውጭ የነበሩት እንስሳት ትርኢቱን ሲመለቱ ሳሉ ፣ አንድ እንግዳ ነገር እየተፈጠረ የሚኼድ መሰላቸው ። በዐሣማዎቹ ፊቶች ላይ ተለውጦ የነበረው ነገር ምንድን ነው ? የክሎቨር ደብዛዛ ዓይኖቹ ካንዱ ፊት ወደ ሌላው ፊት ተመላለሱ ። አንዳንዶቹ አምስት አገጮች ነበሩዋቸው ፤ አንዳንዶቹ አራት ፤ አንዳንዶቹ ሦስት ነበራቸው ። ግን ይቀልጥና ይለወጥ ይመስል

የነበረው ነገር ምን ኖርዋል ? ከዚያም ጭብጨባው አበቃና በማኅበሩ ተቋርጦ የነበረውን የካርታ ጨዋታ ለመቀጠል ካርታ ዎቻቸውን ያዙ ፤ እንስሳቱ ደግሞ ጸጥ ብለው እየዳሁ ተመለሱ ።

ግን ሃያ ያርድ እንኳን ሳይርቁ ድንገት ቆሙ ። ከወደ መኖ ሪያ ቤቱ የሁከት ድምፆች ይሰማሉ ። በጥድፊያ ወደ ቤቱ ተመ ልሰው ኼደው እንደ ገና በመስኮቱ ተመለከቱ ። አዎ ፤ የከረረ ጠብ እየተካኼደ ነበር ። ውካታ ፤ የጠረጴዛ ድብደባ ፤ የጥርጣሬ ግልምጫ ፤ በቁጣ መካካድ ሁሉ ነበር ። የችግሩ መንስኤ ናፖሌዎንና ሚስተር ፒልኪንግተን ሁለቱም ባንድ ጊዜ «ኤ ጦር» (የሚባለውን መጫወቻ ካርታ) ስለተጫወቱ ይመስላል ።

አሥራ ሁለት ድምፆች በንዴት ይጮኹ ነበር ፤ ደግሞም ድምፆቹ ሁሉ ተመሣሣይ ነበሩ ። የዐሣማዎቹ ፊቶች ምን ደርሶ ባቸው እንደ ነበረ አሁን አጠያያቂ አይደለም ። ውጭ የነበሩት ፍጡሮች ዐይኖቻቸውን ከዐሣማ ወደ ሰው ፤ ከሰው ወደ ዐሣማ ፤ እንደ ገና ከዐሣማ ወደ ሰው አንከራተቱ ፤ ነገር ግን በዚህ ጊዜ የትኛው የቱ መሆኑን ለመለየት ፈጽሞ የማይ ቻል ነበር ።